አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአማርኛ የሳይንስ ልበለድ ሙከራዎች፣ በተመረጡ ልበለዶች ማሳያነት

በ

ብርክታዊት ተክላይ

አዲስ አበባ

2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአማርኛ የሳይንስ ልቦለድ ሙከራዎች፣ በተመረጡ ልቦለዶች ማሳያነት

በ

ብርክታዊት ተክላይ

አዲስ አበባ

2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ብርክታዊት ተክላይ

አማካሪ

አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ

2007 ዓ.ም

# ምስጋና

ዳግም የትምህርት ቤትን ጀጅ እንድረግጥ እና ትምህርቴን እንድቀጥል ዕድሉን ለሰጠኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት በአክብሮት ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

አስተማሪዬ (መምህሬ አላልኩህም) እና አማካሪዬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ፣ ርዕሱ ያሰራታል ብለህ ቃልህን ስለሰጠህልኝ፣ በማቃናትም መንገዱን ስላመላከትከኝ አመሰግንሃለሁ። ለእኔ የመልካም ሰዎች መለኪያ ነህ። በክፉ ቀናት የተከፈተልኝ ልብህ እና የተዘረጋልኝ እጅህ ለልጆቼ ደርሷልና የልጆችህ አባት ያድርግህ!

እማዬ/አያቴ፣ የማንነቴ መሰረት ነሽ። "እንዲህ ሆንኩ ነይ" በማለት ማን እንደ እኔ፣ ፈጥኖ በመድረስ ማን እንደ አንች? ይህ ወረቀት እንድጨርስ ህመምሽን ችለሽ፣ ቤትሽን ከኋላ ዘግተሽ ስትመጭ ጥቃቴ ምን ያህል እንደቆጨሽ ህመምሽ ምስክሬ ነው። ለእኔ የምክስበት ዘመን ይምጣ! ለአንች ደግሞ እርጅናሽን ያለምልምልሽ እንጅ ምን እላለሁ?

ዘሩባቤል፣ሳሮን እና ጳውሎስ ቁጣ እና ንጭንጭ ችላችሁ "እማ! ለመጨረስ ምን ያህል ቀረሽ?" ብላችሁ ስትጠይቁኝ ምን ያህል እንዳጣችሁኝ እረዳ፤ "ስትጨርሽ እንዲህ እና እንዲያ ታደርጊልናለሽ?" ስትሉኝ በዚህ ወረቀት ላይ የጣላችሁትን ተስፋ እገምት ነበር። ፈርጦቼ እወዳችኋለሁ! ይኸው ጨረስኩላችሁ!

ጓደኛዬ ሰሚራ መሃመድ ከእኔ እኩል ለነበረው ቁጭትሽ መልሱ ይኸውልሽ! ላዋሽኝ መጻሕፍት፣ ላደረግሽው ብቻ ሳይሆን ልታደርጊ ትፈልጊ ለነበረው ምኞትሽ ሁሉ አመሰግንሻለሁ።

ቶላ "ሶሻል ወርክ"፣ እውቂያችን የአንድ ቀን ቢሆንም ለዚህ ጥናት ከተገለገልኩባቸው መጻሕፍት ውስጥ የሚበዙት ከአንተ የወሰድኳቸው ናቸውና አመሰግንሃለሁ፣ ቅንነትህ አይወሰድብህ ።

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ........................................ I

ማውጫ ........................................ II

አጠቃሎ ........................................ IV

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........................................ 1

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምንያቶች ........................................ 2

1.2. የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.3. የምርምር ጥያቄዎች ........................................ 3

1.4. የጥናቱ ወሰን ........................................ 4

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 4

1.6. የጥናቱ ዘዴ ........................................ 5

ምዕራፍ ሁለት፤ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........................................ 7

2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ፤ የባህል ጥናት ........................................ 7

2.1.1. የሳይንስ ልቦለድ ምንነት ........................................ 10

2.1.1.1. የታሪካዉያን አተረጓጎም ........................................ 12

2.1.1.1.1. የሳይንስ ልቦለድ ቀደምት ታሪክ ........................................ 13

2.1.1.1.2. የሳይንስ ልቦለድ ወርቃማው ዘመን ........................................ 14

2.1.1.2. የቅርጻውያን አተረጓጎም ........................................ 15

2.1.1.2.1. የሳይንስ ልቦለድ ሳይንሳዊ ገጽታ ........................................ 15

2.1.1.2.2. የሳይንስ ልቦለድ ኪናዊ ገጽታ ........................................ 17

2.1.1.3. ታውቶሎጃውያን ........................................ 19

2.1.1.4. ሳይንስ ልቦለድ እንደ ሚት ........................................ 20

2.1.1.4.1. ማንነቶችና የመፈጠሪያ ስልቶቻቸው ........................................ 22

2.1.1.4.2.1.3. ሁለትዮሽያውያን .......... 26
2.1.2. የሳይንስ ልቦለድ ገጽታዎች .......... 27
2.1.2.1. ዘረመል ምህንድስና .......... 28
2.1.2.2. የኮምፒዩተር መገናኛ ቁጥጥር .......... 29
3.1. የራስ ምታት .......... 40
3.2. የቢሆን ዓለም .......... 49
3.3. የሳይንስ ራዕይ .......... 58
3.4. ኤማንዳ .......... 70
ምዕራፍ አራት፤ ማጠቃለያ .......... 79
ዋቢ ጽሑፎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የአማርኛ የሳይንስ ልቦለድ ሙከራዎች፣ በተመረጡ ልቦለዶች ማሳያነት" በሚል ርዕስ የተደረገ ሲሆን *የቢሆን ዓለም* (1983)፣ *የሳይንስ ራዕይ* (1986)፣ *የራስ ምታት* (2003) *እና ኤማንዳ* (2004) በተሰኙ አራት የሳይንስ ልቦለዶች ላይ የተወሰነ ነው። በአማርኛ የልቦለድ አጻጻፍ ልማድ ውስጥ የሳይንስ ልቦለድን በማመላከት ምን ዓይነት ሙከራዎች መከናወናቸውን መመርመር የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ ነው።

የሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ በመሆኑም በባህል ውጤትነቱ እንዴት ማንነትን ለመፍጠር፣ ለመትከል እና ለመግለጽ እንዳገለገለ ለማወቅ የባህል ጥናትን ዋና አተያይ (approach) አድርጎ ተገልግሏል። የሳይንስ ልቦለድ የዘመኑ ሚት ነው ከሚለው አስተሳሰብ አንጻርም የተነሱትን ሳይንሳዊ ገጽታዎችን ለይቶ በማውጣት ልቦለዶቹን ገምግሟል።

በልቦለዶች ውስጥ የተነሱ ሳይንሳዊ ገጽታዎች ከሳይንስ ጽንሰ ሃሳቦች ጋር ለማስተዋወቅ ብሎም እንደ ዓለም አካልነት ከሌላው ጋር ለማስተሳሰር የጎላ ሚና አላቸው። ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ በተመረጡ የአማርኛ በልቦለዶቹ የተነሱት ሳይንሳዊ ኀልዮት ውስንነት ከህትመት ቁጥራቸው ማነስ ጋር ተዳምሮ የአገራችን የሳይንስ ልቦለድ ደረጃ በሙከራነት የሚቀመጥ ለመሆኑ አመላክቷል ።

የሳይንስ ልቦለዶች ካነሷቸው ሃሳቦች ውጭ ኀልዮቶችን ኢትዮጵያዊ በማድረግ የራስ ማንነትን ከፍ ለማድረግ እና ብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት እንደሚውሉ ለማሳየት ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

የሰው ልጅ ምድራዊ ኑሮውን መልክ ካስያዘበት እና "ደረሰበት" የሚባለውን የስልጣኔ እርካብ ካስረገጡት መካከል አንዱ የማድነቅ ችሎታው እና የአዕምሮው ጠያቂነት እንደሆነ ብዙዎችን ያስማማል። በአካባቢው ያሉትን ፍጥረታት ሲያደንቅ፣ ሲገረም፣ ምላሽ ሲሰጥ፣ ምላሹን ደግሞ ሲመረምር፣ አዕምሮውን እንዲያሰለጥን ብቻ ሳይሆን በተራው የተደነቀበትን ነገር አስመስሎ ወይም ለውጦ እንዲፈጥር፣ አቅሙን እንዲያጎለብት አግዞታል።

በዚህም መሰረታዊ የህልውና ጥያቄዎች የሚባሉትን (ከየት መጣሁ? ለምን መጣሁ? እና እንዴትስ  እሄዳለሁ?) በተረዳው መጠን እየጠየቀና እየመለሰ ዘልቋል። በቴክኖሎጂ[1] በመታገዝ ከእርሱ ይልቅ በጉልበት የበረቱትን ገዝቷል፤ አስደንጋጭ የሚባሉ የተፈጥሮ አደጋዎችን ተቋቁሟል፤ "አይመረመሩም" የሚባሉትን የተፈጥሮንና የልዕለ ሃይላትን ምስጢር ለመመርመር ደፍሯል፤ በጥቅሉም ዓለምን ሰብአዊ በማድረግ  "ዘመነ ሰብዕ"[2]ን አምጥቷል።

ከዘመነ ሰብዕ ምልክቶች ውስጥ አንዱ የአዕምሮው ውጤት የሆኑ የጥበብ ስራዎች መገለጣቸው ነው። እግዚአብሔር በተፈጥሮ ላይ እንደሚሰለጥንና የመፍጠር ሃይሉን እንደሚያሳይ፣ የሰው አዕምሮም በጥበብ ላይ የመለኮትን ያህል እንደሆነ Giambattista Vicoን በመጥቀስ ያስረዳል "We stand in relation to the products of the human mind as God stands to nature: God alone is the maker of nature: the human mind may I be allowed to say, is the god of the Arts" (Storey 19). ስለዚህ በዘመነ ሰብዕ የሰው ድርሻ፣ የተፈጠረን ነገር ማድነቅ ብቻ ሳይሆን የራሱን እውነታ/ አማራጭ ታሪክ በመፍጠር እውነቱም መንገዱም አንድ ብቻ አለመሆኑን ማሳየት ነው። የመፍጠሩ ድርሻ የሁሉም ዕጣ ፋንታ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው ከሚመለከተው፣ ከሚያዳምጠው ነገር ፍች የመፍጠሩን ስራ ያስቀጥላል፤ "Human-ity is a species that lives and can only live in terms of meanings it itself must invent. These meanings and understandings not only

---

[1] የሰው ልጅ፣ እንደ ማህበረሰቡ የስልጣኔ ደረጃ ተፈጥሮን ለመግራት የተጠቀመበትን ዕውቀት፣ መሣሪያ እና ዘዴን ይመለከታል።

[2] የሰው ልጅ ታሪክ ሶስት ደረጃዎች እንደሚያልፍ፣ ዘመነ መለኮት፣ ዘመነ ተጋዳሊ እና ዘመነ ሰብዕ ተብሎ እንደሚከፈል ሲጠቅስ መነሻ ያደረገውም ተፈጥሮን በመግራት ባህልን መፍጠር መቻሉ ላይ ነው። "all societies must pass through three stages: the age of Gods, the age of Heroes and the age of Men" Jenks 14). በተጨማሪም የሰው ልጅ በሙላት "ሰው" መሆን የቻለው ወይም ሰውነትን (humanity) ማግኘት የቻለው ቋንቋን መጠቀም በመጀመሩ ነው ይላል። በቋንቋ አማካይነትም ከሚታየውም ሆነ ከማይታየው ረቂቅ ዓለም እውነታ (reality) ፍችን(meaning ን ) በመፍጠር፣ ለፈጠረው ፍች እሴትን በማበጀት፣ ባበጀው እሴት በመገዛት ከሌላው ሁለንታ (universe) እንዲለይ በዚህም ሰብአዊ እንዲሆን አብቅቶታል፤ "To `explore' these worlds is not simply to discover what is there. It is to create what is there"(Storey 2-5).

reflect or approximate an independently existing world but participate in its very construction” (ዝኒ ከማሁ 8). እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ እንደፈጠረ[3] የሰው ልጅም የእጅ ስራዎቹን፣ የአዕምሮው ውጤቶቹን የራሱ ሌላኛ ምስል በአምሳሉ ይፈጥራል። ስለዚህ ፈጠራውም ሆነ ፍለጋው ራሱን ማግኘት ላይ ይሆናል።

በመሆኑም የሰው ልጅ ከህውስታ የራቁ ረቂቅ ሃሳቦችን ለመረዳት፣ ተጨባጩን ዓለም (ራሱንም ጨምሮ) ለመምራት፣ ለመግራት እና ለመግዛት ከተገለገለባቸው መሣሪያዎች ውስጥ ሳይንስ እና ኪነ ጥበብ ተጠቃሾች ሲሆኑ ሰብአዊነቱንም አስመስክሮባቸዋል። ሁለቱ ዲሲፕሊኖች በመተጋገዝም ሆነ በመለያየት ምላሽ እየሰጡ አብረው ዘልቀዋል። የተደጋገፎው ምክንያት በአንድ ባህላዊ ተቋም ስር በመገኘታቸው እንደሆነ የነገረ ማኅበረሰብ አጥኚ የሆኑትን እነ Abercrombie ጠቅሶ ቴዎድሮስ ገብሬ ያስረዳል (ገጽ 78) ።

ኪነት የሰውን ልጅ የማሰልጠን፣ ታላቅነቱን የማጉላት ሚናውን የቀጠለ ሲሆን (ዮናስ 306) ዘመነኛው ሳይንስም ሚታዊ ተረኮቹን በማስረገጥ ይሁን በማስተባበል ተከትሏል። አማራጭ ታሪኮችን አቅርቧል። በሚያደርጋቸው ጥናቶች ውስጥ መላምቶችን አቅርቦ ካስረዳ በኋላ ከመላምቶቹ በትንተና የሚደርስባቸውን ውጤቶች በምልከታ እና በልምምድ ይፈትሻል የሚለውን ጠንካራ አስተሳሰብን በከፊል ሽሮ በእሳቦት አርቅቆት (thought experiment)፣ ምናብን መጠቀም ከዘዴዎቹ አንዱ አድርጓል። ይህ ደግሞ ሳይንስ አዕምሯዊ ብቻ ሳይሆን ልቡናዊም እየሆነ መምጣቱን አመላካች ነው። ስለዚህ ሁለቱ ዲሲፕሊኖች ተዋህደው ሲቀርቡ ያልተዳሰሱ የህይወት መልኮችን ይገልጣሉ፤ ለሰውነትም ፍች ይሰጣሉ። እንዲህ በመሆኑም ሳይንስ ስለ ገቢር (fact) የሚጨነቅ ልቦለድ ደግሞ ከገቢር የተፋታ ሆኖ መታየቱን እንዲቀር ለማሰብ ያግዛሉ ማለት ነው ።

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የአማርኛ ዝርው “ልቦለድ” (prose fiction) “ተጀምሮበታል” ተብሎ የሚጠቀሰውን ዘመን 1900ን መነሻ አድገው ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ፣ ዮናስ አድማሱ 127፤ Teodros Kiros 162፤ አስፋው ዳምጤ 107) አሉ። ነገር ግን ባደረኩት ንባብ በእዚህ ተመራማሪዎች ስራዎች ውስጥም ሆነ በመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፎች በአገራችን ሳይንስ ልቦለድ “አለ” ወይም “የለም” የሚል ዳሰሳ ከአንድ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ በስተቀር ሌላ ጥናት

---

[3] ዘፍ1፣ 26

አልገጠመኝም። በመሆኑም የሳይንስ ልቦለዶችስ ለምን ተዘነጉ? እንዲጠኑ የሚያሳስብ ሥነጽሑፋዊ ሙያ ስለሌላቸው ነው? የሚለው ጥያቄዬ የመጀመሪያው ምክንያቴ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያን የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ለመቃኘት የሞከሩት ተመራማሪዎች ጥናታቸውን ባቀረቡበት ወቅት የሳይንስ ልቦለዶቹ በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም እንኳ ነበሩና ነው። በፍለጋዬ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም የሳይንስ ልቦለድ የሆኑ ስራዎችን አግኝቻለሁ። በልቦለዶቹ ምን አይነት ሳይንሳዊ እውነታዎች ተነስተዋል? በሳይንሳዊ እውነታዎች አማካይነት ምን አይነት ሥነ ጽሑፋዊ እሴት ተፈጥሯል? የሚለውን ለመፈተሽ መውደዴ ሌላው ምክንያት ነው።

ምን አልባትም በዘውጉ ላይ የተደረጉ ጥናቶች አነስተኛ መሆናቸው በአገራችን የሳይንስ ልቦለድ ስራዎች “አሉ?” “የሉም!” የሚል ሁለት ፊት አመለካከት ኖሮም ከሆነ ይህ ጥናት “አሉ” የሚለውን ፍንጭ ለመስጠት እና ባሉት ላይ ለመነጋገር በር ይከፍት ይሆናል። እንዲሁም በመንቀፍም ይሁን በመደገፍ በዘውጉ ዙሪያ ሥነ ጽሑፋዊ ክርክር ለመክፈት፣ እንዲህ አይነት ጥናቶች መደረጋቸው ለፀሃፊዎች፣ ለሃያስያንና ለተመራማሪዎች መድረኩን ባያሟሽ እንኳ ሊያነቃቃ ይችላል ብዬ አስባለሁ።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

### የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

በአማርኛ የልቦለድ አጻጻፍ ልማድ ውስጥ የሳይንስ ልቦለድን በማመላከት ሰብዓዊ ጉዳዮችን መመርመር የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ ይሆናል።

### ዝርዝር ዓላማዎች

“የሳይንስ ልቦለድ የዘመኑ ሚት ነው” ከሚለው አስተሳሰብ አንጻር የልቦለዶቹን ይዘት መገምገም፣ የተነሱት ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች ማንነትን ለመፍጠር እንዴት እንደዋሉ ባህላዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ መነሻቸውን ማሳየት፣ የማንነት መፍጠሪያ ስልቶቹን ልቦለዶቹ ከተዋቀሩበት ፍልስፍናዊ አተያይ ጋር በማዛመድ ትእምርታቸውን መፈከር፣ ዓለም አቀፋዊ የሳይንስ ልቦለድን ገጽታ መነሻ በማድረግ የአገራችን የሳይንስ ልቦለድ ፀሐፊዎች ምን አይነት ሳይንሳዊ ኀልዮት እንዳነሱ መጠቆምና ደረጃቸውን መገምገም ይሆናል።

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ሳይንስ ልቦለዶች እንዴት “ሳይንስ ልቦለድ” ሊባሉ ይችላሉ? እንዴትስ ማወቅ ይቻላል? የሚለውን መመለስ ቀዳሚው ተግባሬ ነው። ይህን ሃሳብ John, Rieder (ገጽ 3)፣ ኬትሊ

ስፔንሰርን በመጥቀስ እንዲህ ያስረዳል፤ "'What is SF?' is not the right place to start if we want to define the genre. Instead, she says, we should ask,"How do readers identify a text as SF?" I think that is a very good question". ስለዚህ በልቦለዶቹ ውስጥ የታዩት ሳይንሳዊ ገጽታዎች (features) የትኞቹ ናቸው? ረቂቅ ጉዳዮች እንዴት ተጓጓዙ? በሚት እና ሳይንስ ልቦለድ መካከል ያለው ዝምድና እስከምን ድረስ ነው? በተመረጡት አራት ልቦለዶች ውስጥ የተነሱት ሳይንሳዊ እውነታዎች ሰብአዊ ጉዳዮችን ለማንጸባረቅ የትኛውን ኀልዮ ተጠቅመዋል? የትኛው ኀልዮ ተደጋግሞ ታይቷል? በመጨረሻም የአገራችን የሳይንስ ልቦለዶች ደረጃ ምን ላይ እንዳለ ምላሽ ይሰጣል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ላይ በተጻፉ አራት ልቦለዶች፤ *የቢሆን ዓለም* (1983)፣ *የሳይንስ ራዕይ* (1986)፣ *የራስ ምታት* (2003) *እና ኤማንዳ* (2004) ላይ ብቻ ተወስኖ ተደርጓል። ለትንተና የተመረጡት አራቱም ረዥም ልቦለዶች "የሳይንስ ልቦለድ" መሆናቸው በደራሲዎቹ ስለተመለከቱ እንደ መነሻ መስፈርት ተገልግየበታለሁ። በክፍል ሁለት "የሳይንስ ልቦለድ ምንነት" በሚለው ርዕስ "ታውቶሎጇውያን" (tautologiest) የሳይንስ ልቦለዶችን ለመለየት መስፈርት አድርገው ከሚያገለገሉባቸው አቅጣጫዎች መካከል ሻጩ (ደራሲው) "ነው" ብሎ ማስራጨቱ አንደኛው እንደሆነ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል። በተጨማሪም ቅርጻውያን "የሳይንስ ልቦለዶች ማሟላት አለባቸው" ብለው ያነሷቸውን ሳይንሳዊ ኀልዮት ስላካተቱ ለመመረጥ በቅተዋል። በትንተና ወቅት በልቦለዶቹ የተነሱ ሳይንሳዊ ርዕሰ ጉዳዮች ማንነትን ለመፍጠር እና ለመትከል እንዴት እንደዋሉም ያሳያል።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ሳይንስ ልቦለድ እንደሌሎቹ የሥነ ጽሑፍ ዘውጎች እሴትን በመፍጠር፣ የማህበረሰቡን ማንነት በመግለጥ፣ በማሳየት ብሎም በመፍጠር የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል። በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥም ይህን እውነታ በማሳየት ተመራማሪዎች ፊታቸውን ወደ ዘውጉ መለስ እንዲያደርጉ ዕድሉን ይፈጥራል። በዚህ ዘውግ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች ሃሳብ በማቀበል የመረጃ ምንጭም ሆኖ ያገለግላል።

በተጨማሪ አገራዊ ጥቅምም ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል። የትኛውም አገር የማደግ ፍላጎት አለው። ለማደግ ከሚቻልባቸው መንገዶች ውስጥ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂን አቅም እና ዕውቀትን ማዳበር አንደኛው ነው። በእኛም አገር ይህን እውነታ የሚያሳይ የተግባር እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ይህን ምኞት (Ambition) የሚያመለክቱ ሁለት ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛው በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ በሚያደርጓቸው ሙከራዎች እና ምርምሮች በየደረጃው ላሉ ተማሪዎች፣ የማበረታቻ ሽልማት እየተሰጠ መሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ የትምህርት ስርዓቱ ሰባ ሰላሳ እንዲሆን መደረጉ ናቸው። ለሳይንስ እና ለኢንጂነሪንግ ትምህርቶች የተሰጠው አብላጫ ኮታ (70%) የዚህ እውነታ አመላካች ነው። የእነዚህ ጥረቶች ተግባር ሳይንስን በማላማድ ለውጥን ለመቀበል የለዘበ ወይም የቀረበ አዕምሮ መፍጠር፣ ለመስራት እና ለመለወጥ የተነቃቃን መንፈስ ማዘጋጀት እና በእችላለሁ ወኔ መሙላት ነው። መነቃቃቱ ደግሞ ለተግባራዊ ስራ ያደፋፍራል።

ሥነጽሑፍ በባህሪው ለማሰብ፣ ለመረዳት እና ለማድረግ እጅግ የራቁ እና የረቀቁ ጉዳዮችን አቅርቦ እና አቅልሎ ቤተኛ የማድረግ ጉልበት አለው። ከሳይንስ ልቦለድ ተግባራት መካከል አንዱ ማህበራዊ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ የሚሆኑ ሳይንሳዊ መፍትሄዎችን መፍጠር እና አማራጭ እውነታዎችን ማሳየት ነው። ስለዚህ ሳይንሳዊ አስተሳሰብን ለመፍጠር የተለያዩ የሳይንስ ልቦለዶች በአይነት እና በብዛት እንዲጻፉ፣ ስለ ሳይንስ ልቦለድ ምንነት፣ ባህሪ እና ፋይዳ ማሳወቅ ያስፈልጋል። ይህን ተግባር በመወጣት ረገድም እንዲህ ያሉ ምርምሮች ወሳኝ ሚና አላቸው ብዬ አምናለሁ።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ሥነጽሑፍ በውስጣዊ (intrinsic method ) እና በአፋዊ (extrinsic method ) ዘዴ ሊጠና እንደሚችል እነ Wellek ይገልጻሉ። ልዩነታቸው ለቅርጽ እና ለይዘት በሚሰጡት ትርጉም ላይ ይመሰረታል። በውስጣዊ መንገድ ማጥናት ያስፈልጋል የሚሉ አጥኝዎች፣ ሥነ ጽሑፍ ያለ ማንም ጥገኛነት መቆም የሚችል ራሱን የቻለ ዘርፍ ነው የሚል መነሻ አላቸው። ትንተናውም ቋንቋ ማዕከል በማድረግ በስነጽሑፋዊ ስልት ላይ ያተኩራሉ። ሁለተኛው መንገድ (አፋዊው ዘዴው) ደግሞ ከቅርጽ ይልቅ ፍች (meaning) ላይ በማተኮር ይዘትን መነሻ ያደርጋል ይላሉ (73)። ነገር ግን ከድህረ መዋቅራውያን (post structuralism) መነሳት በኋላ አፋዊ/ውስጣዊ፣ አውድ/ቴክስት በሚሉ ተቃርኖዎች መካከል ያለ ድንበር ተፋልሷል። ትኩረታቸውን ፍች ላይ በማድረጋቸው ማንኛውም ፍች ማስገኘት ለሚችል ጉዳይ ቅድሚያ

መስጠት አለብን ይላሉ። ይህን ፍች ማስገኘት የሚቻልበትን መንገድ ደግሞ ጠቅልለው ቴክስት በማለት ይጠሩታል፤ “A text is something that we make meaning from” (McKee 4). በመሆኑም ቴክስታዊ ንባብ ሲደረግ የላቀ/ ያነሰ (high/low) ጥበባዊ ስራ ተብሎ የተቀመጠ መስፈርት ይጠፋል። አንደኛ የተጻፉም ሆኑ ያተጻፉ ነገሮች ሁሉ ቴክስት ናቸው ማለቱ ለሁሉም ፈጠራዎች እኩል ድርሻ ከመስጠቱም በላይ ፍች የማስገኘቱም ተግባር የጋራ መሆኑን ያመላክታል። እንዲህ መሆኑ ደግሞ በተዛማች ዘውግ ውስጥ ለሚጠቃለሉት ሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች የእኩል ሃላፊነት ቦታ ይሰጣል። ሁለተኛ ተዛማች ዘውጎች በይነዲስፕሊናዊ ንባብ ስለሚቀሰቅሱ ቴክቶቹ ወደሚጠሩት ዲስፕሊን ወጣ ገባ ለማለት ሰፊ ዕድል ይሰጣል።

በመሆኑም የባህል ጥናት (cultural studies) ለሳይንስ ልቦለዶች የማጥኛ አተያይ (approach) ሆኖ ሲመረጥ ታሳቢ የተደረገው ሁሉም ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች የባህል ውጤት ናቸው የሚል መነሻ ስላለው ነው። በሌላ መልኩም ቴክስቶች ናቸው ማለት ነው። ሌላው የሳይንስ ልቦለዶች የተሰጣቸው ድርሻ አነስተኛ ለመሆኑ መጠሪያው (Popular የሚለው) ከማመላከቱም በላይ በእኛም አገር የተነፈገው ቦታ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

በተለይም የሚፈለግን ማንነትን ለመፍጠርና ለመትከል ሳይንሳዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣... ተረኮችን ከራስ ማንነት ጋር አያይዞ ማቅረብ አንደኛው የባህል ጥናት ዓላማ ነው። እንዲህ አይነቱን ዘዴ Lévi-Strauss “bricolage” በማለት ይጠራዋል (Edgar 43)። ይህ ጥናት የባህል ጥናትን እንደ አተያይ፣ “bricolage” እንደ ዘዴ ሲገለገልበት አንደኛ ጥናቱ ከሰብአዊ ጉዳዮች ውስጥ ማንነት ፈጠራ ላይ ስለሚያተኩር፣ የባህል ጥናት ማንነት ተሰርቶ ያለቀ ጉዳይ ሳይሆን ሂደት ነው፤ ይህን ማንነት ለመስራትም የቴክስቶች ዝምድና አንደኛው መንገድ ነው ብሎ ስለሚቀበልም ነው። ስለዚህ “በሳይንስ ዕድገት” ስማቸው ብዙም የማይጠራ አገሮች ሳይንሳዊ ተረኮችን የራሳቸው አድርገው ሲቀበሉ ሳይንሳዊ ኀልዮትን ብቻ ሳይሆን ሳይንሳዊ ተረኮችንም ከሌሎች (ለሳይንስ ቅርብ ናቸው ከሚባሉት) በመውሰድም ነው። በመሆኑም በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ የተነሱና ከሳይንሳዊ አስተሳሰቡ ጋር ተሸምነው የቀረቡ ሃይማኖታዊም ሆኑ ሳይንሳዊ ተረኮች የዚህ ማሳያ ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት፤ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ይህ ክፍል፣ የሳይንስ ልቦለድ ምንነት፣ የሳይንስ ልቦለድ ታሪክ፣ የሚት ተግባር፣ የጎልዮት ምንነት ይብራራበታል። በተጨማሪም ልቦለዶች የሳይንስ ልቦለድ ለመባል የሚያበቃቸውን ሳይንሳዊ ገጽታዎች ምን ምን እንደሆኑ ይቀርብበታል። ከዚያም በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር ከጥናቱ ጋር ቅርብ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ከይዘት እና ከንድፈ ሃሳብ ምርጫ አንጻር ይተነተንበታል።

## 2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ፤ የባህል ጥናት

ጥናቱ መረጃዎችን ለመተንተን የባህል ጥናቶች (cultural studies) ተብሎ የሚታወቀውን አቀራረብ ይከተላል። አቀራረቡ ከዚህ ጥናት ጋር በሁለት መልኩ ይሳሳባል። አንደኛ የባህል ጥናት ሁሉም ነገሮች የባህል ውጤቶች ናቸው ብሎ ይነሳል። በዚህም የትኛውም የሥነ ጽሑፍ ስራ የባህል ጥሬ ሃብት ነው። እንደ አንባቢው የንቃተ ህሊና ደረጃ ሊተረጎም፣ ፍች ሊሰጠው የሚችል ኪን ነው። በመሆኑም ተዛማች ሥነ ጽሁፍን (Popular literature) ተዛማች ባህል (Popular culture) በሚለው ስያሜ ተለውጦ ቢቀመጥ የተለያዩ ጉዳዮች መሆናቸውን ሳይሆን ሥነጽሑፍ የባህል ውጤት መሆኑን ያመላክታል። የሳይንስ ልቦለድም የባህል ውጤት በመሆኑ በሳይንሳዊ ጎልዮት አማካይነት የተላለፈን የባህል መልክ ለማውጣት ዓላማ ተደርጓል።

ሁለተኛ የባህል ጥናት በስነጽሑፍ ጥናት ውስጥ "የላቀ ሥነ ጽሑፋዊ እሴት አላቸው" ተብለው በሚጠሩ ጽሑፎች (literary canon) እና "ሥነ ጽሑፋዊ ውበታቸው ያነሰ" ተብለው በሚታወቁ ጽሑፎች (Popular literature) መካከል የተበጀ (high/low የሚለውን) መስመር ያፈርሳል። ስለ የሳይንስ ልቦለድ ምንነት እና ከየትኑት ከሰፈሩት ትርጓሜዎች ውስጥ አንደኛው የሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ መሆኑ ነው። አከፋፈሉ መሰረት የሚያደርገው አንደኛውን የሥነ ጽሑፍ ዘር ከሌላው ለመለየት ሲባል የተደረገ መለያ ብቻ ሳይሆን የሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ ደረጃ ማውጫም ነው። (Roberts 11) ይህን ሃሳብ እንዲህ ያስረዳል "SF is popular because it is populist, that it panders to the lowest common denominator, that it is an adolescent mode of writing, that it is not 'serious' or 'high art'"።

ከላይ የቀረቡት የባህል ጥናት አገልግሎቶች በተለይም ለሥነጽሑፍ ጥናት መቼ? እና በእነማን አማካይነት? እንደተዋወቀ Culler (43) እ.ኤ.አ. 1960ን መነሻ ዘመን በማድረግ ሁለት ምንጮችን ዋቢ አድርጎ ያስረዳል። አንደኛው የፈረንሳይ መዋቅራውያን (French structuralist) በመቃወም የተነሳውን የሮናልድ ባርቴዝን ስራ ይጠቅሳል። መዋቅራውያን ባህልም ሆነ ሌሎች የሥነጽሑፍ ዘሮች ህጋቸው መገለጽ ወይም መታወቅ ይችላሉ ማለታቸውን ባርቴዝ እንደሚተች ጠቁሟል፤ “Barthes is especially interested in demystifying what in culture comes to seem natural by showing that it is based on contingent, historical constructions”.

የባህል ውጤት የሆኑ ስራዎች የረጋ ሳይሆን የሚቀያየር ፍች ያስገኛሉ። ፍች የሚገኘውም ከአንባቢው ጋር በሚደረግ ንክኪ ነው፤ ይህ ደግሞ የባህል ውጤት የሆነ ስራ ቋሚ ህግ የሚቀመጥለት ሳይሆን እየተሰራ የሚቀጥል ተግባር እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በሌላ መልኩም ቀኖናዊ እና ዘውጋዊ ስራዎችን ለመበየን የሚውሉ መስፈርቶች ውጫዊ መሆናቸውን ይጠቁማል። መስፈርቶቹ የሚወጡት ከቴክስቱ ውጭ ባሉ ነገሮች እንጂ ቴክስቱ ራሱ የሚሰጠው ፍች እንዳልሆነ ይገልጻል። አንድን ቴክስት የተለያየ ሰው አይደለም፣ አንዱ ሰው በተለያየ ጊዜ እና ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ቢያነበው የተለያየ ፍች ሊያገኝ እንደሚችል ያመላክታል። ይህ የሚሆነውም የቴክስቱ ባህሪ ስለሆነ ሳይሆን አንባቢው ወደ ቴክስቱ ይዞት የሚጠጋው እውቀት እና ልምድ የሚፈጥረው ልዩነት መሆኑን ያስረዳል።

እንዲሁም በእንግሊዝ የተነሳው የባህል ጥናት ማርክሲስታዊ እይታ ያለው እንደሆነም ጆናታን ኩለር ራይሞንድ ዊልያምን እና ሪቻርት ሆገርትን ጠቅሶ ይተነትናል። ድምጽ አልባ ሆነው ተጨቁነው እና ተገልለው የነበሩትንና የተርታውን ህዝብ ማንነት መስማት የሚቻለው ተዛማች ዘውጎችን በማጥናት ነው። በዚህም የባህል ጥናት ባህላቸውን ለማወቅም ብሎም ማንነታቸውን ለመረዳት ይግዛል፤ “the point of studying popular culture is to get in touch with what is important for the lives of ordinary people —their culture” (ዝኒ ከማሁ 45)።

የባህል ጥናት በሁለቱም ምንጮች የባህል ውጤት የሆኑ ስራዎች እንዴት እንደሚከየኑ (እንደሚታተሙ፣ እንደሚሰራጩ እና እንደሚነበቡ) እንዲሁም ማንነት እንዴት እንደሚሰራ እና እንደሚገለጽ መፈተሽን ዓላማ ያደርጋል። ባህል ረግቶ የቆመ ሳይሆን በየጊዜው እየተለዋወጠ የሚሄድ በመሆኑ ማንነትም እየተሰራ የሚቀጥል ሂደት ይሆናል። በመሆኑም የባህል ጥናት የባህልን ሁለት የተግባር ጫፍ በመከተል ፍተሻውን ያስኬዳል። አንድም ባህል

የሚወክለውን ማህበረሰብ እንዴት ይገልጻል? ስለ ማህበሩ ወይም ለማህበሩ ምንድን ነው? ማህበሩ፣ "ለእኔ/ለእኛ ባህላችን እንዲህ ነው "ብሎ ቁሳዊ፣ መንፈሳዊና ቃላዊ ሃብቱን እንዴት ያሳያል? የሚለውን ይመለከታል። አንድም ባህሉ በማህበሩ ላይ ያሳረፈውን ጫናና ማህበሩ፣ "በእኛ ላይ" እንዲህ ነው የሚለውን አሉታዊ ትርጉም ያሳደረበትን ሂደት መፈተሽ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለዘርፉ እድገት አስተዋጽኦ አድረጓል፤ “culture as an expression *of* the people and culture as imposition *on* the people — has been crucial to the development of cultural studies” (ዝኒ ከማሁ 44) ።

በባህል ጥናት አማካይነት ለመተንተን ሲታቀድ ዘዴው ምን አይነት መሆን አለበት? ለሚለው ጥያቄ በዘርፉ ላይ ጥናት ያደረጉ የተለያዩ ባለሙያዎች ምላሽ ይሰጣሉ። እነ Johnson (26) ዳግላስ ኬልነርን (Douglas Kellner) በመጥቀስ በበርካታ አንጻሮች ሊጠና እንደሚችል ይጠቁማሉ። ከእነዚህ መካከል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ (political economy)፣ ቴክስታዊ ዘዴዎች (textual methods)፣ እና የተደራሲያን አቀባበል (audience reception) የተባሉት ዘዴዎች እንዳሉ ጠቅሷል። ነገር ግን በዚህ ጥናት Pertti Alasuutar የባህል ጥናት በአንድ አንጻር ሊጠና ይችላል ብለው ያቀረቡትን ዘዴ የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን እገለገልበታለሁ “cultural studies has a single perspective, taking culture seriously in connection with questions of power” (ዝኒ ከማሁ 26)። ፐሪቲ አላሱታር ባህል የሃይል ሚዛን ማስጠበቂያ መሳሪያ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የመረጡት ዘዴ ተረክ (narrative) የመምረጥ ነጻነት እንደሚሰጥም ይጠቅሳሉ። ዘዴው “bricolage”[4] ብለው ሲጠሩት ተግባሩም የሚፈለግን ማንነት ለመትከል ሲባል ከአንድ ከታወቀ ታሪካዊ ይሁን ሃይማኖታዊ ተረክ ጋር የራስን ማንነት ማገናኘት ነው።

Storeyም ይህን ሃሳብ በመደገፍ የሚመረጠው ተረክ የታሪክ ማጀቢያ (background) ሆኖ ሳይሆን ከቴክስቱ ጋር ተሸምኖ (forground ሆኖ) የሚቀርብ መሆኑን ኮሊንስን በመጥቀስ ያስረዳል። ምንአልባትም አስቀድሞ የነበረን ማንነት ለማስተው፣ አዲሱንና የሚፈለገውን ማንነት ለማልበስ ብቻም ሳይሆን ወደ ነበረው ለመመለስም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የማንነት መስራት ሂደት መነሻ እና መድረሻው የማይለይ አዙሪት ይሆናል፤ “the old is not simply replaced by the new, but is recycled for circulation together with the new” (71-72). ስለዚህ የነበረውን ማንነት ላለመተው እና አዲሱን ማንነት ላለመቀበል ጽንፈኛ አቋም

---

[4] በአማርኛ ንቡር ጠቃሽ ተብሎ ከሚታወቀው የአጻጻፍ ስልት ጋር የሚሰምር ፍች ያስገኛል።

የሚይዝ አካል ቢኖር በተረኩ አማካይነት አቋሙ እንዲሽረሽር እና በሂደቱ አዲሱን ማንነት እንዲቀበል የተረኩ አቅም ያስገድደዋል።

ቃሉን ያስተዋወቀው ሌቬስቱረስ ከሚት ተግባር ጋር ሲያመሳስለው አንዳንዶችም ከህልም ጋር ያዛምዱታል፤ “Myths have been analyzed as if they were the dreams of a culture. Moreover, as myth for Lévi-Strauss is a form of bricolage” (Edgar 43). ስለዚህ ባህል ሃይል ነው ሲባል ዋነኛ ተግባሩ ማንነትን መስራት እና መግለጽ መቻሉ ነው። ህልም፣ ሚት ብሎም ባህል የሚወጣ'ው ተግባር ይህንኑ በመሆኑ ለተመረጡት ቴክስቶችም ሆነ ለአቀራረቡ ምቹ በመሆኑ ዘዴው ለመመረጥ በቅቷል።

## 2.1.1. የሳይንስ ልቦለድ ምንነት

የሳይንስ ልቦለድ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ ምላሽ ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ Roberts ይገልጻል። ለዚህም ምክንያቱ የሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ (popular genre) በመሆኑ የተለያዩ ዘውጎችን ባህርያት አጣምሮ በመያዙ ከእዚህ እስከዚያ ብሎ ለመከለል አስቸጋሪ በመሆኑ ነው፤ “SF as a popular genre, one that shares many features with other ‘pulp’ fictions and popular modes” (11)። “popular” የሚለውን ቃል በ18ተኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፖ ተከስቶ የነበረውን የኢንዱስትሪው አብዮትን ተከትሎ የተደረገውን የፎክሎር ጥናት ጋር ተያይዞ ይነሳል። ከተሜነት እና ኢንዱስትሪያላዊነት “ሰውን ከባህል ነጥሎታል” የሚለው አስተሳሰብ የአውሮፓ እና የአሜሪካ የስነ ሰብ ተመራማሪዎች በተፈጠረባቸው ስጋት ምክንያት ችግሩን ለመቅረፍ ያደረጉት እንቅስቃሴ ይመለከታል። ወደ ኋላ በመሄድ ከከተሜነት በፊት የነበረውን ህይወት እንዲናፍቁ የሚያደርጉ ተረኮችን እና ግጥሞችን በመሰብሰብ ማንነትን መፈለግ፣ ማንነትን መገንባት ላይ አትኩረው ነበር። በዚህ የተነሳም ብሔራዊ ማንነትን አጋኖ ማየት ተጀመሯል፤ ”The first concept of popular culture was invented with the “discovery” of the folk in the late eighteenth century and in the folklore and folk-song movements of the nineteenth and early twentieth centuries. Over a period of about 140 years the idea of popular culture as folk culture was developed by intellectuals across Europe and the USA” (Storey 14).

ምንም እንኳ ሰብሳቢዎቹ ምሁራን ቢሆኑም የተሰበሰቡት ከህዝቡ (the people) መሆናቸው ቃሉን የሚያሻማ አድርጎታል። በኋላም በሃያኛው ክፍለ ዘመን አሜሪካውያን የላቀ (high) እና ተዛማች (popular) ባህሎች ብለው ሲከፍሉ ለጥበብ ሳይሆን ለተዝናኖት፣ ለሙያ ክብር ሳይሆን ለገንዘብ ተብለው የሚጻፉ ስራዎች ደረጃቸው ዝቅ ያሉን "popular" በማለት ይጠሯቸው ነበር (ዝኒ ከማሁ፣ 33)።

ከዚህ በተጨማሪም ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ይገልጻል ሲባል ይህን ማንነት ለማስተላለፍ የሚያገለግለውን የባህል መተላለፊያ ይኸው ተዛማች ቅርጽ ነው። ዘውጉ በባህል ውጤትነቱ የሚያነሳቸውን የፈጠራ ታሪኮች አንባቢው እንዲያምነውና ተስማምቶ እንዲያቀጥል የሚያበቃው ቀመራዊ (formulaic) የሆነው ተስተላልፎ አለው፤ "Cultural products contain both inventions and conventions. Conventions are elements, which are known to both the creator and his audience beforehand" (Muthukumaraswamy 28). ስለዚህ "Popular" የሚለውን "ተዛማች" በሚል ቃል ተክቼ ስገለገልበት መነሻ ያደረኩት ቅርጹ ተጠብቆ እንዲቀጥል የሚያደርገው ቀመራዊ አቅጣጫ ተከትሎ የሚሄድ በመሆኑ ነው። ቀመሩም ከቦታ ቦታ የማይቀያየር ሁሉም ጋር የሚገኝ ተመሳሳይ ባህሪን ተከትሎ እንዲጻፍ ያደርገዋል። በእኛ አገር የተጻፉ የሳይንስ፣ የስለላ፣ የወንጀል፣...ልቦለዶች በሌላ አካባቢ ከተጻፉ የሳይንስ ልቦለዶች ጋር ተመሳሳይ ቀመር የሚከተሉ መሆናቸው ማሳያ ይሆናል።

በዚህ የተነሳ የተለያዩ ፀሃፊዎች ስለምንነቱ የተለያየ ሃሳብ ይሰነዝራሉ። በዋናነት ሁለት አቅጣጫዎችን በመከተል መልስ መስጠት እንደሚቻልም ያስገነዝባሉ። አቅጣጫዎቹ፤ ታሪካውያን (historian) እና ቅርጻውያን (Formalist) እና ተብለው ይታወቃሉ (Roberts 1፤ John, Rieder 6፤ Raman 29) ።

ከእነዚህ በተጨማሪም Tautological አቀራረብ እንደ ሶስተኛ አማራጭ ሆኖ እንደሚያገለግል አዳም ሮበርት ይጠቁማል። ይሕ ሦስተኛ አቅጣጫ ሁሉንም ሊያስማማ ባይችል እንኳ በርካታ ሃያስያንን ሊያቀራርብ እንደሚችልም ጠቁሟል። ይህን ሃሳብ እንደ ሦስተኛ አቅጣጫ በዚህ ጥናት የተለዩ ልቦለዶችን ለመምረጥ የዋለ ሲሆን ለራሱ በተሰጠው ክፍል ስር ይብራራል። ከዚህ በተጨማሪም ሳይንስ ልቦለድ የዘመናዊ ሚት መፍጠሪያ መንገድ ሆኖ ያገለግላል ብለው የሚያምኑም ፀሃፊዎች አሉ (Chernyshova 345)። እነዚህ አራት አቅጣጫዎች በዝርዝር የሚቀርቡ ሲሆን ዘውጉ ተዛማች (popular genre) ከመሆኑ የተነሳም ማንነቶችን ለማበጀት እና ለመግለጽ ስለሚውል በዚህ ጥናት ውስጥ የባህል ጥናት በጽንሰ ሃሳባዊ መሣሪያነት ያገለግላል ።

#### 2.1.1.1. የታሪካውያን አተረጓጎም

Broderick ሁለተኛውን አቅጣጫ /የታሪካውያንን/ ተከትሎ የሳይንስ ልቦለድን ምንነት ገልጿል፡፡ መዋቅራውያን ሳይንስ ልቦለድ “እንዲህ ማለት ነው” ሲሉ “እንዲህ ማለት አይደለም” ብለው ድንበር ማበጀታቸውን ይቃወማል፡፡ ይልቁንም የሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ በመሆኑ በንዑስ ዘውግነት የሚጎራበታቸውም እንደ ስለላ፣ ወንጀል ምርመራ፣ አስፈሪ (Horror) ታሪኮች፣ ጎይቲክ ስራዎች፣… አሉ፡፡ ዘውጎቹ በግጥሞች፣ በአጭር እና ረጅም ልቦለዶች፣ በመጽሔቶች፣ በፊልም እና በቴሌቪዥን ይቀርቡ የነበሩ ታሪኮችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ዘውጎች ጋር የሚጋራቸውን መለያዎች በማጥናት ያመጣውን ለውጥ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

ታሪካውያን፣ የዘውጉን ጥንተ ምንጭ እና አሁን ላይ ያለውን ታሪካዊ አዝማሚያ በማቅረብ ምንነቱን ከአነሳስ ታሪኩ እስከደረሰበት ድረስ ማቅረብ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ታሪካዊ አቅጣጫ ገላጭ አቀራረብ የሚከተል በመሆኑ “እንዲህ መሆን አለበት” ወይም “እንዲህ መሆን የለበትም” ከሚለው አዛዥ (prescriptive) አቀራረብ ይልቅ የሚመረጥ ብቻ ሳይሆን በተሟላ መንገድ የሳይንስ ልቦለድን ምንነት ማወቂያ አቅጣጫ ነው (John, Rieder 10)፡፡ በተጨማሪም ታሪኩ፣ የመምረጫ መስፈርቱን ለማወቅ ከማስቻሉም በላይ “መቼ?”፣ “በእንዴት ባለ ሁኔታ?”፣ “በእነማን?” ወይም “በየት አገር?” ተጀመረ የሚለውንም ለማወቅ ያግዛል፡፡ በመሆኑም “የሳይንስ ልቦለድ መቼ ተጀመረ?” ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምላሾች ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶች ገና አንድ መቶ ዓመት ያልደፈነ ወጣት ዘውግ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የሳይንስ ልቦለድ ባህርያት የሚታይባቸውን ፋንታሲ ስራዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጅማሬውን ሁለት እና ሦስት ክፍለ ዘመን የተሻገረ አዛውንት የፈጠራ ስራ ያደርጉታል፡፡

(Roberts 38) የሳይንስ ልቦለድ ታሪክ በሶስት መድቧቸዋል፡፡ ሦስቱ የታሪክ ምድቦች የተለያዩ፣ ነገርግን ደግሞ አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚደራረቡ ናቸው፡፡ ረዥም ዘመን ያስቆጠሩ ፋንታሲ ስራዎችን የመጀመሪያው የታሪክ ምዕራፍ ከፋቾች፣ ጎይቲክ ስራዎች የሁለተኛው ዘመን ማሳያዎች እና የአሜሪካ የሳይንስ ልቦለዶች መጽሔት መታተም አሁን ላይ ላሉት ጽሑፎች መሰረት ጣይ በመሆናቸው ሦስተኛው የታሪክ አካል አድርጓቸዋል፡፡ ጎይቲክ ስራዎች በፋንታሲ ስር ስለሚመደቡ በአንድ ተዋግነው ቀደምት ታሪክ በሚለው ስር ተደልድለዋል (Rose 13)፡፡ አብዛኛው የሳይንስ ልቦለድ ጸሃፊ የሚስማመበት እና “እውነተኛው” ሳይንስ ልቦለድ ተጀምሮበታል የሚባለውን የኢንዱስትሪው አብዮት ያቆጠቆጠበትን ዘመን ተከትለው የተጻፉ ስራዎች በአንድ ወገን የሚታዩ ሲሆን ለውጡ ከቴክኖሎጂ ዕድገት መዘመን ጋር

ይያያዛል። በመሆኑም በዚህ ዘመን አካባቢ የተጻፉ ስራዎችን የሁለተኛው የታሪክ ክፍል በማድረግ እንደሚከተለው ይቀርባል ።

> True science fiction…could not have been written prior to the nineteenth century then, because it was only with the coming of the Industrial Revolution in the last few decades of the eighteenth century that the rate of technological change became great enough to notice in a single lifetime (Broderick 5).

## 2.1.1.1.1. የሳይንስ ልቦለድ ቀደምት ታሪክ

በሳይንስ ልቦለድ አጀማመር ታሪክ የፋንታሲ ንዑስ ዘውጎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሚታዊ ተረኮች፣ ተረቶች፣ አስማታዊ እና ሐይማኖታዊ ጽሑፎች የሩቅ ዘመን መነሻዎች ሆነው ይጠቀሳሉ። ስራዎቹ በዘመን ሲገለጹ እስከ አስራ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፉ ሲሆኑ የጥንታዊ ሜሶፖታሚያን መወድስ ግጥሞችን *Sumerian Epic of Gilgamesh*ን አንድ ብሎ ያነሳል። ከዚያም የቶማስ ሞር (1516) "Utopia" እና የባኮን (1627) "New Atlantis" የወቅቱ ተጠቃሽ ስራዎች ናቸው (Broderick 4) ።

በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ከኮፐርኒከስ[5] መነሳት በኋላ በርካታ የስነ ክዋክብት ሳይንስ ጥናቶች ተደርገዋል፤ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያም ልቦለዶች ተጽፈዋል። ከእነዚህ ውስጥ የጆሃን ኬፕለር *Somnium* (1634) አጭር ልቦለድ የዘመኑ ተጠቃሽ ስራ ነው። አስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን፤ የስነ ክዋክብት ሳይንስ የተሻሻለበት፣ ስለ ስርዓተ ፀሃይ የተሻለ ግንዛቤ የተያዘበት፣ ለ ሁለንታ የነበረው ግንዛቤ የዳበረበት፣ የህክምና ሳይንስ በተለይም ደግሞ የኬሚስትሪ ዕውቀት የተስፋፋበት ነው። ሊቀ ጳጳስ William Godwin (1638) *The Man in the Moon*፣ እና ሌሎች የዘመኑ ማሳያዎች ናቸው (Roberts 40) ።

አስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን Eberhard Christian (1744) *The rapid journey by Airship to the upper world, recently taken by five people*፣ Ludvig Holberg *Nikolai Klimi iter subterraneum*፣ Marie-Anne de Roumier (1765) *The Voyages of Lord*

---

[5] "መሬት ያለምንም ቅስቃሴ (motion)ረግታ ስትቆይ ፀሃይ እና ሌሎች ፈለኮች በምድር ዙሪያ ይዞራሉ" ያለውን ሳይንሳዊ አመለካከት በማፍረስ መሬት በምህዋሯ ላይ እንደምትሽከረከር፣ የስርዓቱ ማዕከል ፀሃይ እንደሆነች፤ መሬትን ጨምሮ ሌሎች ፈለኮችም በዙሪያዋ እንደሚሽከረከሩ የተለያዩ ጸሃፊዎች ገልጸዋል። አስተሳሰቡ በወቅቱ የነበረውን ሃይማኖታዊ አመለካከት የሚቃረን ቢሆንም ለሳይንሳዊ ስራዎች እና ልቦለዶች መጻፍ አቢዮት በመቀስቀስ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ዘመኑ፤ በሳይንሱ ዓለም ተሃድሶን የከፈተ፤ የሃይማኖት መጽሐፍት ብቸኛ የእውነታ ማረጋገጫ መሆናቸው እንዲያበቃ ያደረገ፤ በተቃራኒው ሳይንስ የእውነታ ማረጋገጫ እንዲሆን ተጽዕኖ የፈጠረም ነበር (Grayling 40፤ Joe 154)።

*Ceton in the Seven Planets*፣ Jonathan Swif (1726) *Gulliver's Travels* በሚል ርዕስ የጻፏቸው ስራዎች የዘመኑን ሳይንስና የሳይንስ ልቦለድን የትኩረት አቅጣጫ ይጠቁማሉ።

አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዛዊቷን ደራሲ Mary Shelley ይዞ ብቅ ብሏል። ሜሪ ሽሊ፣ *Frankenstein* (1818) ጽፋለች። የሳይንስ ልቦለድን ማን አስተዋወቀ? ወይም ማን ጀመረው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ቢሆንም በዚህ ስራዋ አማካይነት (Roberts 42) ሜሪ ሽሊን የመጀመሪያዋ የሳይንስ ልቦለድ ፀሃፊ ሲላት Berman (ገጽ 14) ደግሞ "የሳይንስ ልቦለድ አያት ነች" ይላታል። በዚሁ ክፍለ ዘመን Jules Verne እና H. G. Wells በሳይንስ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጸሃፊዎች ቀዳሚዎች ሲሆኑ የሳይንስ ልቦለድ አባቶች በመባልም ይታወቃሉ (Berman 14) ።

ዌልስ፣ ሳይንስ ልቦለድ የሚለው ዘውግ ከመታወቁ በፊት ሳይንሳዊ ሮማንስ በሚል ስም የተለያዩ ልቦለዶችን ጽፏል። ከእነዚህ ውስጥ *20,000 Leagues Under the Sea* (1870)፣ *The Time Machine* (1895)፣ *War of the Worlds* (1898)፣ *The First Men in the Moon* (1901) የሚሉት ከቀዳሚ ስራዎቹ ውስጥ ተጠቃሾች ሲሆኑ ጁሊየስ ቬርኔ *Voyage to the Centre of the Earth* (1864)፣ *From the Earth to the Moon* (1865 ) በሚሉት ስራዎቹ ይታወቃል (Roberts 37-44)።

### 2.1.1.1.2. የሳይንስ ልቦለድ ወርቃማው ዘመን

ሳይንስ ልቦለድ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳጣመረ የሚታመነው እንግሊዛዊው ባለቅኔ ዊልያም ዊልሰን ሲሆን ዘመኑም እ.ኤ.አ. 1851 ነው (Brian 462 )። በዚህ ዘመን ለሳይንስ ልቦለድ መታወቅ አስተዋጽኦ ካደረጉት መጽሔቶች ውስጥ አስደናቂ ታሪኮች "Amazing Stories" በሚል ርዕስ በ1926 ይታተም የነበረው መጽሔት ቀዳሚ ነው። የመጽሔቱ መስራች፣ አርታኢ እና ነጋሲ ሁጎ ገርንስባክ ሲሆን "እውነተኛው" ሳይንስ ልቦለድ መጣ የተባለውም በዚህ ወቅት ነበር።

ከዚያም በ1932 የመጽሔቱ ስያሜ *science fiction* በሚለው ተቀይሯል። ሳይንስ ልቦለድ ፊቱን ወደ ማህበራዊ ሳይንስ እንዲመልስ ከቀሰቀሱ ውስጥ ከ1937 ጀምሮ ይታተም የነበረው "Astounding science fiction" የተባለው መጽሔት ሲሆን ከሃያስያን Isaac Asimov፣ Damon Knight፣ Donald A. Wollheim፣ James Blish፣ Frederik Pohl፣ Judith Merril ይጠቀሳሉ። የአልዶስ *Brave New World* (1932) ረዥምም ልቦለድም ተጠቃሽ ሲሆን ጃክ ፊኒ በ1955 *Body Snatchers* ብሎ የጻፈው ረዥም ልቦለድ ሳይንስ ወደ ማህበራዊ

ጉዳይ ለመመለሱ ማሳያ ስራዎች ናቸው። በተለይ 1960ዎቹ ለሳይንስ ልቦለድ አዲስ ንቅናቄ ያመጣ ዘመን ሲሆን ሳይንስ ልቦለድ የህዋ፣ የሁለንታ፣ የፈለኮች…ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ነገርን የሚመለከት፣ ጥቁሮችና ሴቶችም የሚሳተፉበት መሆኑን አሳይቷል (Roberts 37-65)።

ታሪክ መለስ ተብሎ ሲዳሰስ የሳይንስ ልቦለድ አቀራረብ ሦስት ዘለላዎችን (strands) ይከተላል (Broderick 280 )። አንደኛው ሳይንሳዊ ፈጠራ (Extrapolative) ላይ የሚያተኩር ሲሆን እንዲህ አይነቱ አጻጻፍ "ቤርኔያን" ተብሎ ከሚታወቅው አጻጻፍ ጋር ይመሳሰላል። ልቦለዶቹ "የአሜሪካውያን የሳይንስ ልቦለድ አጻጻፍ ተጽዕኖ አለባቸው" ተብለው ሲታወቁ ስለሳይንስ ባላቸው አዎንታዊ አመለካከት የተነሳም ቀኝ ዘመም ርዕዮት ተከታይ ናቸው። ሌላኛው ግምታዊ (Speculative) አቅጣጫ ሲሆን "ዌልስያውያን" ተብለው የሚመደቡ ፀሃፊዎች ስራዎች በዚህ ስር ይካተታሉ። የአጻጻፍ ስልቱ "የእንግሊዛውያን ሮማንስ" በመባል ከሚጠራው ዘውግ ጋር ሲመሳሰል ጨለምተኝነት አቀራረብ አለው። ፀሐፊዎቹም ግራ ዘመም ርዕዮት ያራምዳሉ። ሦስተኛው ዘለላ ሁለቱም ቀይጦ የሚይዝ ነው (Brian 565) ።

## 2.1.1.2. የቅርጻውያን አተረጓጎም

ቅርጻውያን፣ ሳይንስ ልቦለድ ከሌሎች ልቦለዳዊ ከሆኑ እና ካልሆኑ ስራዎች የሚለይበትን መስመር በማስመር ከዚህ ወዲህ ሳይንስ ልቦለድ ነው፤ ከዚያ ወዲያ ያለው ደግሞ አይደለም የሚል ዘውጋዊ አቅጣጫን ይከተላሉ። (Roberts 7) ሦስት ያህል ሃያስያንን በመጥቀስ እያንዳንዳቸው ሳይንስ ልቦለድን ከሚመለከቱበት አተያይ አንጻር ምንነቱን ይገልጻል። ሁለቱ Darko Suvin) እና Robert Scholes ቅርፃዉያን ሲሆኑ Damien Broderick ደግሞ ከታሪካውያን ምድብ ነው። በዚህ ክፍል የዳርኮ ሱቨንን እና የሮበርት ስኮልስን ሃሳብ መሰረት በማድረግ የሳይንስ ልቦለድን ምንነት አብራራለሁ።

### 2.1.1.2.1. የሳይንስ ልቦለድ ሳይንሳዊ ገጽታ

እንደ ዳርኮ ሱቨን አገላለጽ የሳይንስ ልቦለድ ሳይንሳዊ የሆነና ተጠየቃዊ አስተሳሰብ ያለው ሃቲት ነው። ተጠየቃዊ አስተሳቡን የሚያገኘውም ሁለት አይቀሬ ባህርያት በአንድ ጊዜ ሲገኙ ነው። አንደኛው ባህርይ፣ "estrangement" ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "cognition" ነው፤ "a literary genre whose necessary and sufficient conditions are the presence and interaction of estrangement and cognition, and whose main formal device is an imaginative framework alternative to the author's empirical environment" (ዝኒ

ከማሁ 7). እኔም Estrangement የሚለውን እንግዳ /ያልተለመደን ነገር እና cognition የሚለውን ደግሞ ምክንያታዊነት በሚል አቻ ትርጉም እገለገላለሁ።

ሳይንስ ልቦለድ እንግዳ እና ያልተለመደን ነገር ማንሳቱ የሳይንስ ልቦለድ ለመባል ከሚያበቃው መስፈርት ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ ከፍ ሲል በቀረበው ጥቅስ ላይ ተመልክቷል። እንግዳነቱን የሚያመጣው ደግሞ መቼቱ ነው። መቼቱ ደራሲው እና ተደራሲዎቹ የሚኖሩበትን የጋራ ዓለም ይመለከታል። ደራሲው ከሚኖሩበት ዓለም የተለየ፣ ያልታወቀን እና ያልተዳሰሰን ኣካባቢ አማራጭ አድርጎ ያቀርባል። ለምሳሌ ጠፈር፣ በባህር ውስጥ፣ ከምድር በታች ያለን ኀታ፣... ሊመርጥ ይችላል። የጊዜ አቆጣጠሩን ከእውናዊ ዓለም የተለየ ሊያደርግ ይችላል። ኣማራጭ ታሪክ በመፍጠር ጊዜያትን ወደ ፊት ወይም ወደ ኋላ በመሳብ ሊያቀርብ ይችላል። ወይም የተለየ የዕውቀት ስርዓት መኖሩን በመፈተሽ ሊያነሳ ይችላል። ይህ ባህሪው ሚመነጨው ደግሞ ከራሱ ከሳይንስ ዓላማ ነው። በዚህ የተነሳም እንግዳነቱ ከእውናዊ ልቦለድ ተለየ እንዲሆን ያደርገዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ ይህን ባህሪ ከሌሎች ፋንታሲ ስራዎች ጋር ጋራዋል። ነገር ግን ፋንታሲዎች ውስጣዊ ፍላጎትን ለማሟላት የተፈጥሮን ህግ በመሻር ተረካዎችን እንደሚያቀርቡ ይታወቃል። ለምሳሌ እንደ “ተናጋሪው ወፍ”፣ “በራሪው ምንጣፍ” ሉትን ትረካዎች ማስታወስ ይቻላል።

ስለዚህ በፋንታሲዎች እና በሳይንስ ልቦለድ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ዳርኮ ቨን እንግዳ የሆኑት ሃሳቦች ከሚለው በተጨማሪ ሌላ ጽንሰ ሃሳብ ያክላል። nova በማለት ጠራዋል። ይህ ጽንሰ ሃሳብ የሳይንስ ልቦለድ ከፋንታሲዎች እና ከሌሎች ምናባዊ ልቦለዶች ተለየ ያደርገዋል ይላል፤ “these nova are grounded in a discourse of possibility, hich is usually science or technology and which renders the difference a aterial rather than just a conceptual or imaginative one” (ዝኒ ከማሁ፣ 7). ይህ ህሪው አማራጭ የይቻላል ዓለምን ለመፍጠር ከማስቻሉም በላይ የሚነሱ ሃሳቦች የመፈጸም ድል እንዳላቸው በሃቲት ደረጃ አብራርቶ ያሳያል። ይህን እውን ለማድረግም በጽንሰ ሃሳብ ረጃ ያነሳውን ጉዳይ ቴክኖሎጂን መጠቀም ያሳስባል። እንዲህ ሆነ ብሎ ከመንገር በላይ ንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ያሳያል። ይህን ባህሪውን የወረሰው ደግሞ ከራሱ ከሳይንስ ነው ማለት ያስረዳል፤ “science is, after all, one of the dominant materialist discourses f the present day” (ዝኒ ከማሁ 5).

ሁለተኛው አይቀሬ ባህሪ ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነ ምክንያታዊነት ላይ መመስረቱ ነው። እንደ ሱቨን አተያይ በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ ያለው ሳይንስ በተወሰነ ተጠየቃዊ መርህ ላይ የተመሰረተ ሃቲት ነው። መነሻ የሚያደርገውም የሳይንስን ፍልስፍና ነው። የሳይንስ ፍልስፍና መስራች Karl Popper “ሳይንስ በሙከራ እና በምልከታ ተረጋግጦ የሚቀመጥ ሳይሆን ለመስተባበል ዕድል የሚሰጥ መሆን አለበት” ያለው ላይ ይመሰረታል። ስለዚህ ሳይንስን ሳይንስ የሚያስብለው ምክንያታዊ አቀራረቡን በተጠይቅ ላይ መመስረቱ እና ዘዴውን መከተሉ እንጅ የሚይዘው እውነት አይደለም።

> One goal of the philosophy of science [...] is an account of scientific practice, broadly understood. This is an account of how scientists develop and investigate ideas, which representational tools they employ, and how choices for one view over another are made (Godfrey 2).

ስለዚህ በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ ያለው እውነታ ሳይንሱ ሳይሆን ሳይንሳዊ ሃቲቱ እና ሳይንሱን ተጨባጭ የሚያደርጉ ከሃሳብ የዘለሉት ቁሶች /የምርምር ጣቢያ፣ መሳሪያዎች፣.../ መኖራቸው ነው፤ “In science fiction it is not that the use of science gives the texts a particular, privileged access to truth ... it is not the ‘truth’ of science that is important to SF; it is the scientific method, the logical working through of a particular premise” (Roberts 9-10). በመሆኑም እነዚህ ሁለቱ ባህርያት በልቦለዱ ውስጥ እኩል መገኘት ብቻ ሳይሆን መዋሃድም ይጠበቅባቸዋል። ይህን በተሟላ መንገድ ለማቅረብ ደግሞ ምናብን መጠቀም ያስፈልጋል።

## 2.1.1.2.2. የሳይንስ ልቦለድ ኪናዊ ገጽታ

የሳይንስ ልቦለድን፣ ከልቦለዳዊ ገጽታ አንጻር ትርጓሜውን ያስፈረው ሃያሲ ደግሞ ሮበርት ስኮልስ ነው። ስኮልስ የሳይንስ ልቦለድ ከሳይንሳዊነቱ ይልቅ ኪናዊ ምንነት ያለው መሆኑን አመልክቷል። ከሱቫን ጋር ያላቸው ልዩነት የሚነሳውም እዚህ ላይ ነው። የሳይንስ ልቦለድ ሳይንሳዊ ዘዴዎችን እንደመነሻ ሊያነሳ ቢችል እንጅ ግቡ አያደርጋቸውም። ትኩረቱም በልቦለዱ ውስጥ የተነሱ ሳይንሳዊ ጉዳዮችን እንዴት ልቦለዳዊ ሆኑ? የሚለውን መመልከት ነው።

ሁለቱ ሃያስያን ሳይንስ እና ሳይንሳዊ ዘዴ በሚሉ ጉዳዮች ላይ ልዩነት አላቸው። ዳርኮ ሱቨን የሳይንስ ልቦለድ በሳይንስነቱ በገቢር እንደማይጠየቅ ነገር ግን ደግሞ ሳይንሳዊ ዘዴን የተከተለ መሆን እንዳለበት ይቀበላል። ስኮልስ በበኩሉ ሳይንስ ልቦለድ ሳይንሳዊ እውነት አይዝም፤ መነሻ ሃሳቡም በሳይንሳዊ ዘዴ ላይ አይመሰርትም ይላል። ከዚህ ይልቅ ሳይንስ ልቦለድ የሚያስኘው ከምልከታ ውጭ ሳይንሳዊ ልቦለዳዊ ፈጠራ (exploration) ላይ በማትኮር የተለየነትን (difference) መፍጠር መቻሉ ነው፤ "science, which is an observational method, is only the starting point for Scholes's Sf. He is more interested in the fictionalization of the premise" (Roberts 10).

በዚህም ስኮልስ ልቦለድ ለሚለው "fabulation" ሳይንስ የሚለው  ደግሞ "Structural" በሚል አቻ ቃል ተክቶ ይገለገላል። "fabulation" ከምናባዊ፣ ከፋንታሲ ታሪኮች እና ሳይንሳዊ ካልሆኑ  ልቦለዶች ጋር የሚጋራው ባህሪ ሲሆን "Structural" ግን ከእነዚህ የተለየ እንዲሆን ያስችለዋል፤ "Structural fabulation is neither scientific in its methods, nor a substitute for actual science. It is a fictional exploration of human situations made perceptible by the implications of recent science" (ዝኒ ከማሁ 10).

በመሆኑም የሳይንስ ልቦለድ የሚጻፈው ለማዝናናት እና ፋንታሲን ለማጋባት፤ የሚነበበውም ከዚህ ለመቋደስ ነው (Rose 127)። በውስጡ የሚገኝ ፋንታሲ ከሁሉም ሥነጽሑፋዊ ስራዎች ጋር የሚያመሳስለው ባህሪው ቢሆንም ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች ላይ መመስረቱ ደግሞ የተለየ ያደርገዋል። የፋንታሲ ተግባሩን የሚወጣውም ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን መፈተሻ "thought experiment" ሆኖ በማገልገል፤ በእነዚህ አስተሳሰቦች ሳይንሳዊ አማራጭ በመፍጠር፣ የሚነሱ ሃሳቦቹን በመሞገት እና ሌላነትን በማሳየት የይቻላል ዓለምን በመመስረት ነው። ይህ ሌላነት በእውኑ ዓለም በሌሉ እና ከዕውቀት ስርዓቱ ውጭ በማፈንገጥ እንደሚያቀርብ የሳይንስ ልቦለዶች ጸሐፊው Broderick (53) ይህን ሃሳብ እንዲህ ይገልጸዋል፤ "I don't consider that any of these have predictive value; they weren't intended for that. I was just trying to write entertaining stories about the might be, not at all necessarily about the would be". ስለዚህ የሳይንስ ልቦለድን ከፋንታሲ ውጭ ማሰብ ልቦለዳዊ ባህሪውን መርሳት ይሆናል "Significant modern SF, with deeper and more lasting sources of enjoyment" (Rose 70).

ስለዚህ (Roberts 98) የሳይንስ ልቦለድ ቀዳሚ ዓላማ መተንበይም ሆነ ማህበራዊ ሂስ መስጠት ሳይሆን በልቦለዱ ውስጥ የሚነሱ ሃሳቦችን መሞገት እንደሆነ በተከታዩ መንገድ

ያስረዳል፤ "SF novel needs to aim not at political correctness, or at an unspoken decency regarding race; instead it should make us think about these issues, confront us with them, as only a literature of ideas can". በመሆኑም በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ "አለ" የሚባል እውነታ ቢኖር ሳይንሳዊ ሃሳቡ ሳይሆን ልቦለዳዊ ጎልዮ ነው። በጥቅሉ አንድን ልቦለድ "የሳይንስ ልቦለድ" የሚያስብሉ ሶስት ጉዳዮች ታሪክ፣ ሳይንስ እና ሳይንሳዊ ግምቱ ሲሆኑ ቁሳዊ ጉዳዮችን ከሳይንስ፤ የታሪኩን አወራረዱን ከልቦለድ፤ በመውሰድ ሳይንሳዊ ግምቱን ይከይናል (Broderick 15)።

### 2.1.1.3. ታውቶሎጃዉያን

ከላይ የሳይንስ ልቦለድን በተመለከተ የቀረቡ ብያኔዎች ብዙዎችን ያከራክራሉ። በተለይም ከፋንታሲ፣ ከምናባዊ ስራዎች እና ከሌሎችም ሥነጽሑፋዊ ከሆኑ ሥራዎች እንዴት ይለያል የሚለው ሃሳብ ብዙ ሃያስያንን አያስማማም። (Roberts 1) አከያየናቸውን መሰረት በማድረግ ከደራሲው፣ ከአንባቢው፣ ከአታሚ ድርጅቶች እንዲሁም ከገበያ አንጻር የሚተረጉሙ ሃያስያን ኤድዋርጅ ጀምስ፣ ዳይመን ናይትን እና ኖርመን ስፒናራይድ በመጥቀስ ያስረዳል። ሳይንስ ልቦለድ ባህላዊ ክስተት በመሆኑ አመራረቱን፣ ስርጭቱን፣ አቀባበሉን፣... እና እንዲህ አይነቱን ታሪክ ለመፍጠር የተቻለበትን ባህላዊ አውድ መግለጽ አለበት። ኤድዋርድ ጀምስ፣ "በገበያ ላይ ሳይንስ ልቦለድ ናቸው" ተብለው የሚቀርቡ ስራዎችን "የሳይንስ ልቦለዶች ናቸው"፣ ብሎ ሲመድባቸው መስፈርት የሚያደርገው ገበያው የሚሰጣቸውን ትርጉም ነው።

በሌላ በኩል ዳመን ናይት፣ "አንባቢው ሳይንስ ልቦለድ ናቸው"፣ ብሎ የሚጠራቸው ሁሉ "ሳይንስ ልቦለድ ናቸው" በማለት ማዕከሉን አንባቢውን ወይም ሸማቹን ያደርጋል። ኖርመን ስፒናራይድ በበኩሉ "ሳይንስ ልቦለድ" ተብለው የሚታተሙ ማናቸውም አይነት ስራዎች ሳይንስ ልቦለድ" ይባላሉ ሲል መስፈርት የሚያደርገው ደራሲውን ወይም አታሚ ድርጅቱን ነው። እነዚህ ሦስት ድንጋጌዎች ሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች የባህል ውጤቶች በመሆናቸው የአተረጓጎም መንገዳቸውን ገበያውን በሚወስኑ አካላት ላይ መስርተዋል። እነዚህ አካላት አምራቹ፤ ደራሲው ወይም አታሚ ድርጅቱ እና ሸማቹ አንባቢው ሲሆኑ ሁሉም የገበያ ምርጫ አላቸው፤ "Sf is that species of storytelling native to a culture undergoing the epistemic changes implicated in the rise and super cession of technical-industrial modes of production, distribution, consumption and disposal" (ዝኒ ከማሁ 12).

በመሆኑም ገበያው ለሁለቱ (ለአምራቹም ሆነ ለሸማቹ) የምርጫ ነጻነት ይሰጣል። የገበያ ስርዓቱ የሚመራው በፍች ፈጣሪዎች (producer) እንጅ በፍዝ ተቀባዮች (consumer) ላይ አይሆንም። እንዲህ ሲሆን ደግሞ ተደራሲያን ስለ ባህላዊ ምርቱ ያላቸው አቀባበል እንደሚኖራቸው ኪናዊ ንቃት የሚወሰን ይሆናል። ስለዚህ ፍች የመስራቱም፣ የመገምገሙ ተግባር የሁሉም ይሆናል ማለት ነው።

## 2.1.1.4. ሳይንስ ልቦለድ እንደ ሚት

ቴዎድሮስ ገብሬ፣ ሚት "የሰው ልጅ፣ የነገረ ፍጥረትን እና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት፣ እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ስርዓት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊ እና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው" በማለት በጽሑፉ መግቢያ ላይ ያስተዋውቃል (ገጽ xii)። ሚት ትኩረቱን በልዕለ ተፈጥሮ ሃይል ላይ ሲያደርግ ሰውን የሚመለከተው፣ ትርጉም የሚሰጠው፣ መሠረታዊ የሚባሉትን የማንነት ጥያቄዎችን የሚመልሰው ከልዕለ ተፈጥሮ አንጻር ይሆናል። ሰማያዊ ጉዳዮችን በሰው አማካይነት ያቀርባል። ይህን አይነት ትርጓሜ የሚያስገኙ ሚቶችን "ብሉይ ሚቶሎጅ" ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። በሌላ መልኩ ሚት ከልዕለ ተፈጥሮ ይልቅ በሰው ልቡና ላይ በማትኮር በባህል እና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር እና ለመግለጽም ያገለግላል። እንዲህ አይነቱን የሚት ልማድ 'ሐዲስ ሚቶሎጅ" ልንለው ስንችል ሚታዊ ተረኮች በየትኛውም ዘመን የሚከሰቱበት አዲስ ቅርጽም ነው (ዝኒ ከማሁ 256)።

በዚህ ልማድ ከዘመናዊ ሳይንስ መነሳት በኋላ "ሚት አብቅቶለታል፣ አገልግሎቱን ጨርሷል፣" የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት አይኖረውም። ይልቁንም "ያለ ሚት የሚኖር ባህል እና ትውልድ የለም" የሚለው አቋም በጥብቅ ይቀነቀናል። ነባሩ ሚት በአዳዲስ ቅርጾች መተካቱን ማሳሰቡ ሌላው የልማዱ ገጽታ ነው። ለሐዲስ ሚቶሎጅ መከሰት ምቹ ከሆኑ ዲሲፕሊኖች ውስጥ ፊዚካዊ ሳይንስ፣ ስነ ልቡና እና ኪነጥበብ ተጠቃሾች ናቸው። ቴዎድሮስ ገብሬ፣ ዘመናዊ ሳይንቲስቶች፣ ፈላሪያን ልቡና እና ከያንያን የዚህ ዘመን ሚት ፈጣሪዎች መሆናቸውን የተለያዩ አስረጅዎችን በማምጣት ያስረግጣል (ገጽ 78-88)። በመሆኑም የዘመኑን አስተሳሰብ የሚገልጡ የተለያዩ ሚት ፈጣሪዎች ተከስተዋል።

የሚትን ኑረት ከሚያሳዩ የኪነጥበብ ቅርፆች ውስጥ አንዱ ሳይንስ ልቦለድ ነው። (Tatiana Chernyshova 345) ይህን ሃሳብ እንዲህ ይገልጹታል "The notion that sf is a orm of myth is not a new one". ስለዚህ ሳይንስ ልቦለድ ሚትዊ ነው ሲባልም በሚት

ልማድ መሰረት ይቀርባል፣ ሚትን የሚያሳስቡት ጉዳዮች ይመለከቱታል ማለት ነው። በዚህ የተነሳ ሳይንስ ልቦለድ ተፈጥሮን፣ ባህልን እና ልቦናን አስተሳስሮ ይመለከታል ማለት ነው።

ሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ በመሆኑ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ይቀበላል። አዲሶቹ አስተሳሰቦችም በተቀባዩ ባህል ላይ የሚፈጥሩት የተለየ እሴት ይኖራቸዋል። በነባሩ እና በአዲሱ ባህል መካከል በሚፈጠር ግንኙነት አዳዲስ እውነታዎችን ይሰራሉ። ማንነቶች[6] ይፈጠራሉ፣ ይተከላሉ፣ ይገነባሉ፣ ይተላለፋሉም፤ "Making popular culture can be empowering to subordinate and resistant to dominant understandings of the world" (Storey 52)። በዚህ ተግባር የጠፋ ራስ ተፈልጎ ይገኛል። ይህን ሰብአዊ ጥረት ቴዎድሮስ ገብሬ(91) "አስተርፅዮ-ርዕስ" በማለት ሲጠራው የሐዲስ ሚቶሎጅ ተጋዳሊን ለዕጩ ተጋዳሊነት ሲያበቃው ሂደቱን የዘመናዊ ሚት ልማድ ነውም ይለዋል ። ይህን የሚት ልማድ (Coupe 14)፤ (Brian 318) "Mythopoeia" በማለት ይጠሩታል። Coupe የሚት ልማድን ተረክ መፍጠር ማለት ነው ሲለው ተረክን በመፍጠር ሚት እና ሥነጽሑፍ  አቻ ደረጃ እንዳላቸውም ይገልጻል፤ "literary works may be regarded as 'mythopoeic', tending to create or re-create certain narratives which human beings take to be crucial to their understanding of their world" (ገጽ 4) ።

ስለዚህ የሚት ልማድ፣ ሚት በሥነጽሑፍ፣ ሥነ ጽሑፍ በፋንታው በሚት ላይ በሚያሳርፉት የእርስ በእርስ በጎ ተጽዕኖ አማካይነት ታሪክ የመፍጠር ሂደት ማለት ነው፤ "Mythopoeia might discuss the influence of myth on literature and confluence of myth and literature" (Tewodros Gebre 145)። ሚትን ሚት ከሚያሰኙት ጉዳዮች ውስጥ አንደኛው የሚያነሳቸው ጉዳዮች ሲሆኑ ሌላኛው ደግሞ ጉዳዮቹን የሚያቀርብበት መንገድ ነው። ከሚት ልማዶች መሃል አንዱ ሥነጽሑፍን በሚት አማካይነት መስራት ነው። ሐዲሱ ሚትም በነባሩ ሚት አቀራረብ ይሁን በርዕሰ ጉዳይ ምርጫ ላይ በመመስረት አዳዲስ እውነታዎችን ይፈጥራል ማለት ነው። በዚህ የፈጠራ ሂደቱ ነባር አስተሳሰቦች ይሻራሉ። አዳዲስ እውነታዎች ይፈጠራሉ። የእነዚህ እውነታዎች መፈጠር እና መገለጽም የሚት ፈጠራ ያሰኙታል።

---

ማንነት የሚለው ሃሳብ በብዙ ቁጥር ማንነቶች ተብሎ ሲመለከት አንድም በተፈጥሮ የሚገኝ አለመሆኑን እና ሚፈጠር መሆኑን አንድም ባለቤቱ እንደገባበት ሁኔታ የሚቀያየር መሆኑን ለመግለጽ ነው (Storey 72)

### 2.1.1.4.1 ማንነቶችና የመፈጠሪያ ስልቶቻቸው

ማንነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ እንደሚጠጋው የዕውቀት እና የጥናት መስክ የተለያየ ፍች ሊኖረው ይችላል። ለዚህም መንስዔው ሰው ግላዊና ማህበራዊ ማንነት ስላለው ሲሆን ግላዊ ማንነቱን ከስነ ልቦናው፣ ማህበራዊ ማንነቱን ከመሰሉ ጋር ባለው ግንኙነት ይመሰረታል። የማንነት ምስረታው የሚቆመው በተቃርኖ ነው። ተቃርኖው ተፈጥሯዊ ወይም ማህበራዊ መሰረት ሊኖረው ይችላል። ተፈጥሯዊ ተቃርኖ የማይቀየር ሲሆን እንደ ፆታ (ስለ ፆታ ወጣ ያለውን አስተሳሰብ አይወክልም)፣ የቆዳ ቀለም፣...ያሉትን ሲያካትት ማህበራዊ ተቃርኖ ደግሞ የፖለቲካ አመለካከት፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ፣....ይይዛል። ተቃርኖዎቹ እንደሚገቡበት ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ አጋጣሚዎች ፍችዎቻቸው ሊለያይ ይችላል። በዚህ ጊዜ ማንነት ትርጉሙ ይሰፋና ከአንድ በላይ ይሆንና ማንነቶች ይሆናል። ስለዚህ ግለሰቡ "እንዲህ ነኝ" የሚለው እና ማህረሰቡ ደግሞ "እንዲህ ነህ" የሚለው ትርጉም አንድ ላይ መጥቶ የሚሰጠውን ፍች ማንነት እንለዋለን። ስለዚህ የማንነቶች ትርጉሙ እንዲቀጥልና ተቀባይነት እንዲያገኝ "እንዲህ ነኝ"/"አይደለሁም" በሚለው እና "እንዲህ ነህ"/ "እንዲህ አይደለህም" በሚሉት መካከል ስምምነት መፈጠር አለበት (De Fina 24) ።

በስምምነቱ አንደኛው የሌላኛው ሌላ (other) ይሆናል፤ "identity is formed according to constructions of 'difference' between 'self' and 'others'" (McGuigan 244). የራስን ማንነትም በሌላኛው ኑረት ላይ ይመሰርታል። በዚህ የተነሳም ያለ ሌላኛው፣ ራስ የሆነ ማንነት አይኖርም። በአንዱ ኑረት ሌላው ይሰራል። በዚህም እኛ / እነሱ ይፈጠራል፤ የእኛ /የእነሱ ማንነት ይረቃል፤ ለእኛ የተሻለ ለእነሱ ዝቅተኛ ስፍራ መስጠቱ ይቀጥላል። "እኛ ከእነሱ ይልቅ እንበረታለን፤ እነሱ ያንሳሉ" የሚሉ ፍችዎች በተደጋጋሚ በተረኮች አማካይነት ይተላለፋሉ፤ መሰረት እንዲይዙ ይደረጋል። ማንነት የባህል ውጤት በመሆኑ ትርጉሙ እንደገባበት ሁኔታ እየተቀያየረ ይቀጥላል። ከአንድነቱ ይልቅ ልዩነቱን እያጠነከረ እና አጥሩን እያጠበቀ ሲሄድ የግጭት መንስዔ ሊሆንም ይችላል። በመሆኑም የግጭት አይነቱ በተለያየ መንገድ ሊጠና ይችላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን እና የማህበሩን ማንነት እየፈጠረ ይቀጥላል። ፈጠራው ሁለት መንገዶችን መሰረት ያደርጋል። በጋራ ዕውቀቱ አማካይነት የሚፈጠር ማንነት ምንጩ የነደደ ፍላጎት (desire) ወይም ትውስታ (memory) ሊሆን ይችላል (Storey 78) ።

ትውስታ፣ ያለፈን ታሪክ መሰረት በማድረግ "እንዲህ ነበርን እኮ" በሚል በትዝታ፣ በቁጭት ወደ ኋላ በመመለስ ማስታዎስ ላይ ያተኩራል። "ትልቅ ነበርን ትልቅ እንሆናለን" የሚል መንፈስ ያለው ነው፤ "Memory seems to be at the very core of identity; it

connects who we are to who we once were" (ዝኒ ከማሁ 81). በትውስታ ትናንት እና ዛሬ ይጋባሉ። የትናንት እውነት ዛሬን ይሰራል፤ ነገር ግን ደግሞ የሚታወሰው ነገር የግድ የነበረ ወይም የተደረገ እንዲሆን አይጠበቅበትም። በማስታዎስ ላይ ስለሚመሰረት የመዘንጋት የመዛነፍ ዕድል ሊገጥመው ስለሚችል እውነቱን ተጨባጭ ለማድረግ በወቅቱ የነበሩ መረጃዎችን /የጦርነት ታሪኮች፣ ደብዳቤዎች፣ ሐውልቶች፣ ሰነዶችን፣.../ ሊያነሳ ይችላል፤ "what signifies is not the "facts" but how the "facts" are interpreted, how they are articulated to make meaning in the present. Therefore, the profound interaction between memory and identity formation does not necessarily depend on the truth of what is remembered" (ገጽ 83) ።

የነደደ ፍላጎት፣ ወደ ፊት እንዲኖር ወይም እንዲመጣ በሚፈለገው ምኞት ላይ ይመሰረታል። በሁለቱ መንገዶች አማካይነት የሚፈጠረው ማንነት እንደማህበር ለመቆም የሚያስችል እና ክፍተትን የሚሞላ እውነታ ነው። በእነዚህ መንገዶች አማካይነት እኔ/እኛ ማን ነኝ/ነን? ከየት መጣሁ/መጣን? እና ወዴት እሄዳለሁ/ እንሄዳለን? የሚሉትን መሰረታዊ የማንነቶች ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ። እያንዳንዱ የማህበር አባል "እኔ እንዲህ ነኝ" የሚለውን በሚፈጥራቸው ታሪኮች አማካይነት ያስተላልፋል። እንደገባበት እና እንደሚገኝበት ሁኔታ ማንነቱን እየሰራ ይቀጥላል፤ "identities are clearly about "who we think we are" and "where we think we came from," they are also about "where we are going" (ዝኒ ከማሁ፣ 80)። ስለዚህ ማንነት ሂደት እንጅ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ እንደማያልቅ መገንዘብ ይቻላል። ለእነዚህ የማንነት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ የተነሳበትን የፍልስፍና እውቀት መሰረት ይጠቁማል። በልቦለዱ ውስጥ የሚጠቀሱ ኀልዮት[7]ም እንደ መነሻ ሆነው ያገለግላሉ።

## 2.1.1.4.2. የኀልዮት ምንነት

ኀልዮ (idea) ወይም ኀልዮት (ideas) እያንዳንዱ ግለሰብ በግሉ ወይም እንደማህበር አባልነቱ በጋራ ስለ ዓለም እና በውስጧ ስላሉት ነገሮች ያለውን ዝንባሌ (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣... ሊሆን ይችላል)፣ ዕውቀት፣ ለህይወት የሚሰጠውን ትርጉም እና የማንጸሪያ መስፈርቱ፣ በጥቅሉም ስለ ማንነት ያለውን ፍች ለማወቅ እና ለመግለጽ ያስችላሉ።

---

[7]ኀልዮት፣ "ማሰብ፤ ከልብ ማንቃት፤ ነገርን፣ ሥራን፤ ከነቢብ፣ ከገቢር በፊት፤ በሃሳብ በልብ መፍጠር ማስገኘት፣ ማሰናዳት፣ መመርመር፣ መፈለግ፣ ማውጣት፣ ማውረድ" ነው ይላሉ( ደስታ ተክለወልድ 477) ።

ኀልዮት፤ የሁሉም ዲስፕሊኖች ፍልስፍናዊ ዕውቀት መጠየቂያ፣ ማወቂያ፣ መፈተሻ፣… ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው (Bunnin 322)። መነሻቸው የግለሰብ አዕምሮ ቢሆንም ህልው ሆነው እንዲቆሙ የሚያደርጋቸው ግን የወል የሆነው ተመሳሳይ ጉዳያቸው ነው። በዚህ የተነሳም ሁሉንም ዘመን መግለጽ የሚችል ዓለም አቀፋዊ ገጽታ አላቸው። በአንድ ዘመን የነበሩ በሌላ ዘመን፣ አንድ ቦታ ላይ የተነሱትን በሌላ ቦታ ልናገኛቸው እንችላለን፤ "ideas are the most migratory things in the world" (Lovejoy 4). ስለዚህ ጸሃፊው በልቦለዱ "አሉ" ብሎ የሚያምንባቸውንና "ሊኖሩ ይችላሉ" ብሎ የሚገምታቸውን ኀልዮት መዝግቦ የፈጠረውን ማንነት ያስተላልፍበታል፤ ያዘልቅበታል (Wellek and Austin 111) ።

በጥቅሉ ስለ ኀልዮት ምንነት የሚሰጠው ምላሽ ሁለት ፊት ነው። አንደኛው ትኩረቱ የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው። ይህም ስለሁለንታ (Universe) ባለ አመለካከት ላይ ይወሰናል። ሁለንታ የሚታየውን እና የማይታየውን ዓለም፤ ሰውን እና ከሰው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግዙፍ አካላት እና ረቂቅ ጉዳዮችን የሚመለከትን ጽንሰ ሃሳብ ይወክላል። የሚታየው ዓለም የቆመው፤ በአይን በሚታዩ ተጨባጭ አካላት እና በአይን በማይታዩ ነገር ግን በስሜት ሊደረስባቸው በሚችሉ ረቂቅ ነገሮች ግንኙነት ነው። ስለዚህ በኑባሬ ደረጃ ከሁለቱ (ከአካላት እና ከኀልዮት) ቀዳሚው የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ ስለ ግለሰብም ይሁን ስለዓለም አቀፋዊ እውቀት ከየትነት እና የማንጸሪያ መስፈርቱን (point of reference) በሌላ መልኩም ስለ ማንነቱ ማወቂያ ሆኖ ያገለግላል። ሁለተኛው ትኩረቱ ደግሞ ኀልዮት ከቁስ ጋር ያላቸውን የእርስ በርስ ግንኙነት እና ደረጃቸውን ይመለከታል። ግንኙነቱ የዕውቀት ምንጩን ፣ የእውነታ መመዘኛ እና ደረጃ ማውጫ መስፈርቱን መለያም ይወስናል።

## 2.1.1.4.2.1. የኀልዮት ቅደም ተከተላዊ አሰላለፍ

አሰላለፉ፣ በመፈጠር/ በመገኘት ቀዳሚው ኀልዮት ወይስ አካላት ናቸው? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ይመለከታል። ለቅደም ተከተሉ የሚሰጠው ምላሽ የአጠቃላዩን የሰው ልጅ ዓለምን የመመልከቻ መስፈርት፤ ርዕዮተ ዓለማዊ መነጽሩን ማወቂያም ነው። የትናንት የጋራ እውነቱን የመሰረተበትን፣ የዛሬውን እውነቱን ያረቀቀበትን እና የነገ ተስፋውን የሚያመላክትበትን አቅጣጫ ይነግራል። በዚህ የተነሳም "ተጨባጭ አካላት/ቁስ ቀዳሚ ናቸው" የሚሉት ቁስ አካላውያን (materialist) እና "የማይታየውን ዓለም የሚወክሉት፣ ኀልዮት፣ ቀዳሚ ናቸው" የሚሉት ሃሳባውያን (idealist) ተብለው በሁለት አበይት ክፍሎች ይመደባሉ።

The crux of the debate between idealism and materialism in the social sciences thus centres on the question of whether it is 'ideal elements' (i.e. the attitudes, norms, values, beliefs, etc. of individuals or communities of individuals) or 'material elements' (i.e. the structures of the sensuous environment, human biology or 'species-being', and socioeconomic relations) which should rightly enjoy explanatory primacy in social analysis (Creaven 20).

በሌላ ወገን ደግሞ አንዱ ከአንዱ አይቀድምም። ወይም የአንዱ ህልውና በሌላው ላይ ጥገኛ ሲሆን አይገባል የሚል አማራጭ የሚያቀርቡ ደግሞ ሁለትዮሻውያን (Dualist) ይባላሉ። ምንም እንኳን እንደ አማራጭ ሆነው ቢቀርቡም ስለ ኀልዮት ባላቸው አመለካከት በሃሳባውያን ስር ይካተታሉ። በእነዚህ አስተሳሰቦች ላይ በመመስረት የተለያዩ የዓለም አመለካከቶች ይቀዳሉ።

## 2.1.1.4.2.1.1. ቁሳካላውያን

ዓለም የተመሰረተችው በተጨባጭ አካላት አማካይነት ነው፤ "the material universe existed before there was organic life, and ... living organisms can only exist as composed of and surrounded by matter" (Creaven 29)። እነዚህ ተጨባጭ አካላት የሚያድጉ እና የሚለወጡ ነገር ግን የማይጠፉ ናቸው። በተግባሩ ሂደት ውስጥ ኀልዮ ሲከሰት በደረጃ ቅደም ተከተሉም ሁለተኛ ሆኖ ይመጣል ይላሉ። ተጨባጭ አካላት ቀድመው በመምጣታቸው የተነሳ ኀልዮ የቁስ ውጤት ይሆናል ። በዚህም ኀልዮ የመጀመሪያው (የቁስ) ነጸብራቅ ሲሆን ቀድሞ የመጣው ደግሞ ነባራዊ እውነታ ይሆናል (Bunnin 413) ።

## 2.1.1.4.2.1.2. ሃሳባውያን

ሃሳባውያን፣ ኀልዮ ቀዳሚ የዕውቀት ምንጭ ሲሆን ለነገሮች ካለ መሆን ወደ መሆን ከለመኖር ወደ መኖር መምጣት ሰበብ ነው ይላሉ። በዚህም ኀልዮ ስለ ውጫዊው ዓለም ለማወቅም እንደ ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል። በገሃዱ ዓለም ያሉ ተጨባጭ እውነታዎች አስቀድመው የሚፈጠሩት የሚታወቀውን ነገር በሚያውቀው ግለሰብ አዕምሮ ውስጥ ነው ይላሉ። ስለ ዓለም የሚኖር እውቀት የሚወሰነውም ከግለሰቡ አዕምሮ አንጻር ሲሆን በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያሉ እውነታዎችም የአዕምሮው ነጸብራቆች ናቸው ይላሉ። እንደ ተጨባጭ ሃሳባዉያን (objective idealism) አመለካከት በገሃዱ ዓለም ውስጥ ኑረቱን ጠብቆ የሚቆይ

ኀልዮ አለ። ይህ ኀልዮ ደግሞ የራሱ የሆነ ነጻ ህልውና ያለው ሲሆን በህልውና ቀዳሚም ነው። ዕውቀት የሚገኘውም በውስጠኛ ክፍል፣ በነፍስ (soul) አማካይነት ነው። ኀልዮ ቁጥጥር በማድረግ ሌላ ተጨባጭ እውነታ ይፈጥራል (ዝኒ ከማሁ 322)።

## 2.1.1.4.2.1.3. ሁለትዮሽያውያን

የዚህ ኀልዮ አራማጆች ከሆኑት ውስጥ Descartes አንዱ ነው (Creaven 22) ። ዴካርት ቁስ ሆነ ኀልዮ የራሱ ማንነት ያለው እና አንዱ የሌላው ጥገኛ ያልሆነ፤ ሁለቱም እኩልነት የሚገኙ ናቸው ይላል። በሂደት ውስጥ ሁለቱም የእርስበርስ ግንኙት ያደርጋሉ ይላል። ለምሳሌ አዕምሮ (mind) እና አካል (body) የተለያዩ ቢሆኑም በህይወት ውስጥ በሚኖራቸው ድርሻ ግን የሚገናኙ ናቸው። እዚህ ላይ አዕምሮ መንፈስን፣ ሃሳብን፤ አካል ደግሞ ኑባሬያዊ ተፈጥሮን ወይም ቁስን ይወክላል (Bunnin 193)።

## 2.1.1.4.2.2. የኀልዮት ግንኙነት

ኀልዮት ህይወትን እና ዓለምን በትክክል መግለጽ ስለመቻላቸውን እና ለመታመን ባለመብቃታቸው የተለያዩ አስተሳሰቦች ይንጸባረቃሉ። ይህ የአስተሳሰብ ልዩነት ስለ ዕውቀት እና የዕውቀት ምንጭ (የስህተትንም ምንጭ)፣ የእውነታ ማረጋገጫ መስፈርቶች፣... እንዲለያዩ ያደርጋቸዋል። ንጽጽሩ በኀልዮት ብቻ የሚያቆም ሳይሆን ከተጨባጩ ቁስ አንጻር የሚለካ ነው። ስለዚህ በሚታወቀው ነገርና በዕውቀቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ በተለያዩ ዘመናት፣ የተለያየ አቅጣጫ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል። ለጥያቄዎቹ የሚሰጡ ምላሾችም ሁለት የተለያዩ የፍልስፍና ጎራዎች እንዲፈጠሩ ሰበብ ሆኗል (Creaven 80)።

ነገሮች እና ሁነቶች ሊታወቁ የሚችሉት በአመክንዮ (reason) አማካይነት በአዕምሮ ነዋኔ ነው የሚሉት ምክንያታውያን (Rationalist) ይባላሉ። በአመክንዮ አማካይነትም ወደ እውነተኛው ዕውቀት መድረስ ይቻላል እንጅ የስሜት ህዋሳት የሚያደርሱት መረጃ እንደ እውነተኛ የዕውቀት ምንጭ ሆነው ሊያገለግሉ አይችሉም ይላሉ። በሌላኛው ምድብ ስር የሚከተቱ ደግሞ ስሜታውያን (empiricists) ይባላሉ። ዕውቀት የሚገኘው በስሜት አማካይነት የሚገኝ ልምድ ወይም ገጠመኝ ሲሆን፤ ስሜት ብቸኛው የዕውቀት ምንጭ ነው ይላሉ። በዚህ የተነሳም ስለዕውቀት ምንጭ የሚሰነዝሩትን ሃሳብ የተለያየ ሲሆን ችሏል።

## 2.1.2. የሳይንስ ልቦለድ ገጽታዎች

አዳም ሮበርትስ፣ Gary Westfahl በመጥቀስ ሳይንሳዊ ልቦለድ ተብለው የሚጠሩ ስራዎች ሶስት ባህርያትን ማሟላት አለባቸው ይላል:: የመጀመሪያው መስፈርት በዝርዋዊ ትረካ መልክ የቀረበ መሆን አለበት:: ሁለተኛ ሳይንሳዊ ጭብጦችን እና አስተሳሰቦችን ማንሳት አለበት:: በሶስተኛ ደረጃም አዲስ የሆነን ጉዳይ ያሳያሉ (ገጽ 23) ::

> A/ It is a prose narrative. B. It includes language which either describes scientific facts, or explains or reflects the processes of scientific thought; and C. It describes or depicts some aspect or development which does not exist at the time of writing."

ከላይ ያለው ሃሳብ ምንም እንኳ የሳይንስ ልቦለዶችን ለመለየት የሚያስችል ቢሆንም የመጀመሪያው እና ሦስተኛው መስፈርት ሳይንስ ልቦለድ ከሌላው ዝርዋዊ ጽሑፎች እንዲለይ ኣያደርገውም:: ነገር ግን የተለያዩ ጸሃፍት ልቦለዶች ሳይንሳዊ ለመባል ሳይንሳዊ ርዕስ ጉዳዮች ኣና መርሆዎች እንዳሉት ይጠቁማሉ (Roberts 12)፣ (Brian 462):: እነሱም ስለጠፈር ነይንስ (spaceships)፣ ስለፈለኮች የእርስ በርስ ግንኙነት እና ወደ እነሱም ስለሚደረግ ጉዞ ሚያነሱ (interplanetary or interstellar travel)፣ ስለእንግዳ ፍጡራን እና ከእነሱ ጋር ነለሚደረግ ተጋድሎ የሚያወሩ (aliens and the encounter with aliens)፣ ስለማሽኖች እና ሮቦቶች/ሐለተብርት (mechanical robots)፣ ስለዘረመል ምህንድስና እና ስለአፈጣጠር ቴክኖሎጂዎች የሚተነትኑ (genetic engineering)፣ ስለመገናኛ ቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች እና ነለ ኮምፒዩተሮች ዘመናዊ አሰራር (computers, advanced technology)፣ ስለ ጊዜ ጥርመሳ time travel)፣ አማራጭ ታሪክ በጊዜ ውስጥ ስለመፍጠር የሚያነሱ (alternative history)፣ ነለምናባዊ ዓለም ታሪክ (futuristic utopias and dystopias)፣ የሚያቀርቡ ርዕስ ጉዳዮችን ሚያነሱ ስራዎች ሳይንሳዊ ልቦለድ ለመባል እንደ መስፈርት ሆነው ያገለግላሉ:: በትንተና ዑቅትም ምናባዊ ዓለም (utopia and dystopia) ተብለው የተቀመጡትን የሳይንስ ልቦለድ ነህርያት ራሳቸውን ችለው ሳይሆን ሳይንሳዊ ተግባራቱ ለምን ዓላማ እንደዋሉ የመግለጽ ሚና ትሰጥቷቸው ይቀርባሉ:: በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ የታዩት ሳይንሳዊ ገጽታዎች የዘረመል ምህንድስና (genetic engineering) እና የኮምፒዩተር ቁጥጥር (Cybernetics) ናቸው::

### 2.1.2.1. ዘረመል ምህንድስና

የዘረመል ቴክኖሎጂ በስነ ህይወታዊ ቴክኖሎጂ (biotechnology) ስር የሚመደብ ሲሆን አካላትን ከማቀያየር እስከ ህዋሶችን በመውሰድ አዲስ ፍጥረት በቤተ ሙከራ እስከ መስራት እና ማሻሻል የሚዘልቅ ቴክኖሎጂ ነው፤ “Biotechnology plays an important part in restructuring bodies, in endowing them with protective and aggressive mechanisms and even in enabling survival against all odds” (Cavallaro 201) . ምርምሩ በሰው፣ በዕፅዋት አሊያም በእንስሳት ላይ ሊፈጸም ይችላል፡፡ የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ የሚመሰረተው በዳርዊናዊ ንድፈሃሳብ[8]ላይ ነው፡፡ ትኩረቱም የነበሩትን ተፈጥሯዊ ነገሮች ከሰው ልጅ እና ከአካባቢው አንጻር በመመዘን ማሻሻል ወይም ማዘመን እንዲሁም ይጎላሉ ወይም ጎሉም የሚላቸውን ክፍተቶች ለመሙላት መፍጠር ላይ ነው፡፡ መነሻው የተፈጠሩ ነባራዊ ሁድለቶችን በመመልከት አሊያም ወደፊትን አርቆ በማየት የተሻለችን እና ለሰው ልጅ ምቹ የሆነችን ዓለም መፍጠርን መናፈቅ ነው፡፡ ግቡም እንከን ያለባቸውን ዝርያዎች በማሻሻል፣ የተበላሹትን በማስወገድ እንከን አልባ እና ፍጹም ዝርያዎችን መፍጠር ነው፡፡ ተግባሩን ለመወጣት ከሰው ልጅ የሚቀድም ለመፍትሄውም የሚተጋ አለመኖሩን በሚከተለው መንገድ ያስረዳል (Bxter 158)፡፡

> Darwinian processes to prophesy that we human beings will shortly be in a position to take control of those processes, particularly at the genetic level. We will then be able to deal with those personal and social problems that derive from the unplanned nature of the natural world by the application of biotechnology, perfecting ourselves and our societies.

በዚህ መሰረትም የራስ ምታት እና የቢሆን ዓለም በሰው ላይ የተደረገን ስነ ህይወታዊ ቴክኖሎጂ ያሳያሉ፡፡ በዋናነትም የአዕምሮን ንቅለ ተከላ (Brain transplantation) መሰረት አድርገዋል፡፡

---

[8] ለሰው ዘር ጥንተ ምንጭ መነሻ የሆነው የጋራ ምንጭ “Homo sapiens” ነው የሚለው ቻርለስ ዳርዊን፤ ዝግመተ ሂደት ለውጥ እየተሻሻለ ዛሬ ላይ ሲደርስ በበርካታ ዘመን ውስጥ በበርካታ ለውጦች ታጅቦ እንዳለፈ ያስገነዝባል፡፡ አክሎም ተፈጥሮም ምርጥ የምትላቸውን እየለየች እንደምትቀበል እና በ “natural selection” ሂደት ልተመረጡትም በተሻሉት ስለሚዋጡ ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ራሳቸውን ለሁኔታዎች በማመቻቸት ማብቃት ግዴታ አለበት (Bxter 1).

## 2.1.2.2. የኮምፒዩተር መገናኛ ቁጥጥር

እንደ ስነሰብ አጥኚዎች አመለካከት የሰው ልጅ ከተፈጥሮ እና ከአካባቢው ጋር ጥብቅ ትስስር አለው። ግንኙትንም የሚመራውም በመስጠት እና በመቀበል ነው። ሁለትዮሻዊ ሆነውን ግንኙነት ቀጣይ እንዲሆን የመጠበቅ እና የማስጠበቅ ግዴታ እንዳለበትም ጠቁማሉ። ይህን መሰሉን ግንኙነት የሚመራበትን ሳይንስ ደግሞ በተፈጥሮ ሳይንስ አጠራሩ ኮምፒዩተር መገናኛ ቁጥጥር ቴክኖሎጂ (Cybernetics) ይባላል። ዐቢይ ግቡ የተለያዩ አካላት (organisms) በማሰባሰብ እንደ አንድ ሆነው እንዲቆሙ በማድረግ የልዩነትን ድንበር ማጥፋት ነው። የድንበር ውሉ በአካል መገኘትን ሳይጠይቅ በመረጃ ልውውጥ ይተሳሰራል።

በተፈጥሮ ሳይንስ አተረጓጎም፣ ቀደም ሲል ነበረው ኮምፒዩተር እና በዘመኑ ኮምፒውተር መካከል ያለውን ግንኙነት ዕድገት የሚያጠና ሳይንስ ነው። የሰው ልጅ እና የእንስሳትን ተለይም የሰውን ልጅ) የአዕምሮ መዋቅር እንዲሁም የመልዕክት ቅብብል ስርዓቱ ኮምፒዩተር ጋር መመሳሰሉን መነሻ ያደርጋሉ። የሰው ልጅ በመረጃ ቅብብል ሂደት ውስጥ መልዕክቶችን ያሻሽላል፣ እንደገና ይፈጥራል። ቀደም ሲልም ኮምፒዩተሮች በጦር አውድማ ላይ ሚሳየል በመተኮስ ሰዎችን ተክተው ያገለግሉ ነበር። ስለዚህ የአዕምሮ ተግባር ተክቶ ስለሚሰራ ማሰብ ይችላል" ብለን መነሳት እንችላለን የሚለውን ሃሳብ ይይዛሉ። እናም ኮምፒዩተሮች ምፒዩተሮችን መፍጠር ይችላሉ ወደሚል መደምደሚያ ይደርሳሉ። በዚህም ወሳኙ ሰው ነው? ምፒዩተር? በሚል መነሻ ሰው/ማሽን የሚሉ ተዋረዳዊ ግንኙነት እንዲፈጠር ምክንያት ንደሆነ መገንዘብ እንችላለን (Barnard 800) ።

ማህበራዊ ሳይንስ በበኩሉ በዘአካላት መካከል ባለው ግንኙነቱ አንዱ ለአንዱ የሚሰጠው ላውም የሚያቀበለው ነገር ይኖራል ይላል። በቅብብል ሂደቱም የመጀመሪያው ማንነታቸው ጠፋ ወይም አዲስ ማንነት ሊያገኝ ወይም እንደገና ሊሰራ ይችላል። የጋራ የሚያደርጋቸውም ሳቦት፣ ቋንቋ ወይም ሌሎችን አዕምሯዊ ተግባራት ይኖራል። እነ ራፓፖርት ከተፈጥሮ ይንስም ይሁን ከሌሎች የፍልስፍና ዘርፎች ላይ ስለ ነጻ ኑረት (independent existence) ሚሰጠውን ሃሳብ ይቃወማሉ። በተፈጥሮ፣ በቁሶች፣ በእንስሳት መካከል የማይነጣጠል የጋራ ላጎት ግንኙነት አለ ይላሉ። የመረጃ ተለዋዋጮቹ የግንኙነት ደረጃም አንዱ የአንዱ አጋር ኖ ሳይሆን የማይነጣጠል አምሳል ሆኖ የሚቆምበት ስርዓትን የሚያሳይ ጽንሰ ሃሳብ ነው። ንኙነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚፈስ ሳይሆን በቅብብሎሽ በግብረ-መልስ እየተረጋገጠ በመቀጠል ሁለቱ ወገን የጋራ ጥምረት የሚመሰረት ነው። ውህደት የሚፈጥሩ ዘአካላትም የጋራ ሐሳብ፣

ፍላጎት፣ ቋንቋ ወይል ሌሎች አዕምሯዊ ተግባራትን ይለዋወጣሉ። (Cavallaro 200) ይህን የህብረተሰብ ሳይንስ አስተሳሰብ በመደገፍ በእንዲህ መልክ አስረድታለች።

> Cybernetics, or Control and Communication in the Animal and the Machine, argues that control and communication should be based on steersmanship, not on dictatorship. Both organisms and machines are viewed as self regulating Systems based on control and communication".

## 2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ከእኔ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ሲቃኙ አካሄዱ ሁለት አቅጣጫ ተከተለ ነበር። አንደኛው በተመረጡት ልቦለዶች ላይ የተደረገ ጥናት እንዳለ መቃኘት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሳይንስን እና ልቦለድን አስተሳስረው የተጻፉ ስራዎች መኖራቸውን በመፈተሽ ነበር። ከበርካታ ጥናቶች ውስጥ ለዚህ ጥናት የሚቀርቡ አራት ያህል ስራዎች ብቻ ተገኝተዋል፤ ነገር ግን ታዬ አሰፋ፣ "Psedo-science/Technology and Politics in *Dertogada* and *Ramatohara*" ብለው የጻፉትን መጣጥፍ አጠቃሎውን ባገኝም ሙሉ ጥናው ጽሑፍ ለመታተም ወደ አሜሪካ በመላኩ" (ዶር.ታዬ እንዳሉት) ለመቃኘት አልቻልኩም። በመሆኑም ቅኝቱ በአንድ የጉባዔ መጣጥፍ እንዲሁም በሁለት የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ላይ በመወሰን በጥቅሉ በሶስት ጥናቶች ላይ ተደርጓል።

በሳይንስ ልቦለድ ላይ ትኩረት አድርጎ የተፃፈው አንድ ጥናት ብቻ ነው። ለምን ሌላ ጥናት አልተደገመም? የሚለው መላምታዊ ሃሳቦችን ማቅረብ ይቻል ይሆናል። አንደኛው እንደ ሌሎች ረዥም ልቦለዶች ሁሉ "ሳይንሳዊ ልቦለዶች" ተብለው የተጻፉ ስራዎች በንጽጽር ሲታዩ ቁጥር ጥቂት መሆናቸው ለዚህ ጥናት ባደረኩት አሰሳ መረዳት ችያለሁ። ከዚህ በተጨማሪም ተመረጥኲቸው መጽሐፎች ከሁለቱ ልቦለዶች *የቢሆን ዓለም* (1983) እና *የሳይንስ ራዕይ* (1986) ውጭ ያሉት ሁለቱ ስራዎች *የራስ ምታት* (2003) እና *ኤማንዳ* (2004) የቅርብ ጊዜ ስራዎች በመሆናቸው ላይቃኙ ይችላሉ። በነበሩት ላይ ጥናት አለመደረጉ፣ የተደረገውም አንድ ብቻ መሆኑ የሳይንስ ልቦለድ የተሰጠው አናሳ ትኩረት ማሳያም ነው ።

ቅኝቱን ከእኔ ጥናት ጋር ካለው ቀረቤታ አንጻር በመለካት እጅግ የሚቀርበውን ወደ ኋላ ማድረግ እተነትናለሁ። በዚህም ኤፍሬም አሰፋ (1994) "በዳኛቸው ወርቁ *አደፍርስ* ውስጥ የሚታዩ ሣይንሳዊ አገላለጾች ሂሳዊ ምልከታ" በሚል ርዕስ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም አስራ

ᎋስተኛ ጉባዔ ያቀረበውን መጣጥፍ ሳስቀድም። የጥናቱ ዋና ትኩረት በአደፍርስ ውስጥ የታዩ ሳይንሳዊ አገላለጾች ለይቶ በማውጣት ሥነጽሑፋዊ ስራዎች ለሳይንሳዊ ፈጠራ የማነሳሳት አቅም እንዳላቸው ማሳየት ነው። የጥናቱ ኣላማ ሥነጽሑፍ ከማዝናናት ባለፈ ለሳይንስ ዕድገት ኣና ስርጸት የጎላ ሚና ስላለው የሁለቱን መስኮች ትስስር ማሳየት ነው። ጥናቱን ለማድረግም የነሳሳው ህብረተሰባችን ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ጀርባውን ሰጥቶ "አትድረስብኝ"፣ "አልደርስብህም" ነማለቱ፣ የትምህርት ቤትን ደጅ የረገጠና የሳይንስን ትምህርት ያገኘውም ቢሆን ሳይንሳዊ ነስተሳሰቡ ከዘመኑ ጋር የማይራመድ በመሆኑ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ሳይንስ በትምህርትነት ሊሰጥም አስተሳሰባቸውን የመለወጥ እና በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የመሳተፍ አቅማቸውን ነማጎልበት የማያበቃ መሆኑ ነው። ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ለማስረዳ የሚውሉት ምሳሌዎች ነዕድ እና ከኢትዮጵያ አውድ የራቁ መሆናቸውን እንደ ምክንያት አንስቷል። ይህ መሆኑም ነው ከሳይንስ እየራቀ እንዲሄድ አድርጎታል። የመራራቁ ደረጃ ደግሞ ከራስ ሽሽት ጋር 'ሚነጻጸር ነው። ምክንያቱም ሳይንስ ከሰው ማንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑም ው። ስለዚህ የማቀራረቡን ሃላፊነት መወጣት የሚችለው ደግሞ ሥነጽሑፍ ነው። ሥነጽሁፍ ሳይንስ ፊቱን ያዞረውን እና የተራራቀውን ለማቀራረብ ያገለግላል።

ሥነጽሑፍ፣ ሳይንሳዊ ሃቆችን እና ደረቅ እውነታዎችን ከማቅረብ ባለፈ የማዝናናቱን ·ግባር ደርቦ በተለይም የፊዚክስን ትምህርት ለማስተማር (pedagogical ተግባር ለመወጣት) ·ገቢ ስለሆነ ለመመርመር መውደዱን ጠቅሷል። ኤፍሬም ባደረገው ንባብ አደፍርስ "ሳይንሳዊ ነገላለጾች የታጨቁበት" ልቦለድ ሆኖ እንዳገኘው እና ፊዚክስን ያለ ቁጥር ለማስተማር፣ ተፍታታ መንገድ ዕውቀትን ለማስጨበጥ እንደሚያገለግል ጠቁሟል (ገጽ፣ 63) ።

እንደ ኤፍሬም ጥናት ሥነጽሑፍ ድንቅ የሆኑ ሳይንሳዊ አገላለጾችን በመሰነድ እንደ ፃህደር ሆኖ ያገለግላል። የሳይንስንና የሥነ ጽሑፍን አይቀሬ ትስስር ለማሳየትም *በአደፍርስ* ውስጥ ከቀረቡት ሃቲቶች ውስጥ ሳይንሳዊ ህጎችን ለይቷል። በዚህም *አደፍርስ* "የእንቅስቃሴ ነግ"፣ "አቅም"፣ "ሥራና ጉልበት"፣ "ብርሃን"፣ "ሞገድ" እና "ድምጽ"፣ "ሥነግለት"፣ ነንፃራዊነት"፣ "ካልኩለስ" የሚባሉትን የፊዚካል ሳይንስ ህጎች በታሪኩ ውስጥ እንዳንጸባረቀ ልጿል (ገጽ 66)።

የእኔ ጥናት ከአፍሬም ጥናት ጋር በአነሳሽ ምክንያቱ ይመሳሰላል። ሁለቱም አዳዲስ ይንሳዊ ሃሳቦችን በማስተዋወቅ እና በማላመድ ደረጃ ሥነ ጽሑፍ ትልቅ ድርሻ እንዳለው

ያምናሉ። የእኔ ጥናት ሥነጽፍን ሳይንስን ለማስተማር ተግባር ይውላል የሚለውን አስተሳሰብ በቀጥታ ባያነሳም ከሳይንሳዊ አስተሳሰቦች ጋር የማላመድ አቅም እንዳለው ግን ያምናል። ነገር ግን በሚያነሷቸው ጉዳዮች እና በመረጃ ማውጫ መንገዳቸው ይለያያሉ። ኤፍሬም ያነሳቸው ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች ተፈትነው ተግባራዊ የሚሆኑ ሃቆች ናቸው። ከዚያም “ሳይንሳዊ እውነታዎች ሊያሳዩልኝ ይቻላሉ” ያላቸውን ሃሳቦች ከህጎቹ ጋር በማዛመድ ኑረታቸውንም አስረድቷል። የእኔ ጥናት ግን ልቦለዳዊ ሳይንሳዊ ኀልዮት በሃቅ በማይጠየቁ፣ በማይፈተሹ በዕለት ተዕለት ህይወት በቀጥታ በማይገጥሙ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች ላይ ያተኩራል። ኀልዮቱ ከተፈጥሮ ህጎች ውጭ የሆኑና በራስ ስርዓት የሚተዳደሩ ናቸው። ሌላው የኤፍሬም ጥናት በፊዚካል ሳይንስ ላይ ብቻ ሲያተኩር የእኔ ጥናት ደግሞ በሳይንሳዊ አስተሳሰቡ አማካይነት የተላለፈውን ሰብዓዊ ጉዳይ ምንነት መፈከር ላይ ያተኩራል።

ቀጣዩ ቅኝት ጳውሎስ ዘማርያም (2006) "የኹለት ዓለማት ጉዞ በ*ዜና እስክንድር* እና *ገድለ ዞሲማስ* ውስጥ" በሚል ርዕስ ያቀረበው የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ነው። ጳውሎስ በ *ዜና እስክንድር* እና *ገድለ ዞሲማስ* ላይ ጥናቱን ሲያደርግ በባህል ጥናት አንጻርነት ከፎክሎር፣ ከስነጽሑፍ፣ ከታሪክ፣ ከፍልስፍና፣ አፈታሪክ፣ ሚት፣ ሮማንስ የመነጩ ሃሳቦች ጋር በማዛመድ ተገልግሏል። መረጃዎችን በቴክስታዊ ዘዴ ተንትኗል።

የእኔ እና የጳውሎስ ጥናት ሚት፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ በሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች እና ተረኮች አማካይነት የማንነት ምስል እንዴት ይፈጠራል? የሚሉት ጉዳዮች ላይ ማትኮራችን ያመሳስለናል። ነገር ግን ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት በሚለው ክፍል ሚትን “አምኖ በሚቀበለው ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ፍጹም እውነት ይታሰባል። በማይቀበለው ማህበረሰብ ዘንድ ፍጹም ውሸት እና ባዶ ፈጠራ እንደሆነም አስፍሯል (ገጽ 20)፤ ነገር ግን እንደ ተመራማሪ ሐሰት ናቸው ብሎ መደምደም ባይጠበቅበትም ምናባዊ መሆናቸውን መግለጽ ግን ነበረት። ምክንያቱም በማጠቃለያው ላይ “እውነተኛ ታሪክ” መሰረት አድርገው በኪን ተሸምነው ተጽፈዋል” ብሎ አይደመድምም ነበር። ተረኮቹን እንዲፈክር ነጻነት የሰጠው ውስጣቸው ያለው ፈጠራ ነው። ፈጠራው ተረኮቹን በፍካሬ ሂደት የሚታወቅ የማህበረሰቡን እውነት የሚገልጡ ልቦለዶች ያደርጋቸዋል እንጅ ውሸት አያደርጋቸውም፤ በቁማቸው የሚይታዩ እውነታዎች ያስብላቸውም፤ "myth is invention, a fiction....(Chernyshova 347) ።

ሌላው ጳውሎስ ለትንተና ከተገለገለባቸው ጽንሰ ሃሳቦች አንዱ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ው። በትንተናው ማጠቃለያም ሁለቱ የመረጣቸው ቴክስቶች ከሳይንስ ልቦለድ ጋር ንደሚመሳሰሉ እንዲያውም "የሳይንስ ልቦለድ" እንደሆኑም ደምድሟል። ለማሳያነትም ሁለት ብነቶችን ገልጿል።

ዜና እስክንድር የተጻፈበትን 13ተኛ ክፍለ ዘመን እና የዘመናዊ ሳይንስ አብዮት ተቀሰቀሰበትን 16ተኛውን ክፍለ ዘመን አነጻጽሯል። ሁለቱን ክፍለ ዘመኖች በህልም ስተሳስሮ በህልሙ ፍች ሳይንስ እና ሚትን አዛምዷል። ፊሊጶስ በህልሙ "ወፏ እንቁላል ጭኑ ላይ ትጥላለች። እንቁላሉ ወድቆ ሲሰበር ከውስጡ እባብ ይወጣል። እባቡ እንቁላሉን ዞሮ መግባት ሲሞክር ይታያል" (ገጽ 73)። በፍካሬውም ምድር ጠፍጣፋ ተደርጋ ትታሰብ በረችበትን አሮጌ ሳይንስ ሽሮ የእንቁላል ቅርጽ እንዳላት አድርጎ መፈከሩ ከዘመናዊው ሳይንስ ተሳሰብ ጋር ስለሚስምር "ከሳይንስ ልቦለድ ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖረው የሚያደርገው መስለኛል" ብሏል።

ሁለተኛው ማሳያ የሐለይተብርት ቴክኖሎጂ ነው። በተለየ ጥበብ ስለተሰራች ከተማ እና ተዘጋው በር ትረካ አቅርቧል። በከተማዋ በወንድ እና በሴት ምስል የተሰሩ ሐለይተብርት እና ሌሊት ይዘፍናሉ። ይህን ቅጥር አልፎ መሄድ ይከብድ ስለነበር ተጋዳሊው በልዕለ ፈጥሮ ኀይል ይሻገራል። ሮቦቶቹ የተሰሩት ከሞተር ከተሽከርካሪ ማሽን፣ ከነጣቂ ማሽን እና ሚደግፍ ማሽን ነው። "እነዚህ በሃሳብ የተቀረጹት የቴክኖሎጂ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው" ብሏልም ፡ 77) ። ይህን ትረካ መዞ ያወጣው ከደቂቀ ያፌት ውስጥ ሲሆን ስለ አስማታዊ ጥበብ ቱምም ይገልጻል። "ከንቱ እና ውሸት ነው ተብሎ ከሚታሰበው አስማታዊ ጥበብ አንዳች ውቀት መኖሩን መጠርጠር ተገቢ ነው" ይላል (ገጽ፣ 76)።

እንግዲህ ሁለቱ ሳይንሳዊ ሃሳቦች በሃሳብ የተቀረጹ ናቸው ያለውን፣ የልዕለ ተፈጥሮ ዛ የሚለውን እና የአስማታዊ ጥበብን ይዘን "ሳይንሳዊ ልቦለድ ናቸው" ብሎ የደመደመበትን ንገድ ማስታረቅ ይከብዳል። እርግጥ ነው ሳይንስ ልቦለድ እና አስማታዊ ጽሑፎች አይታመኔ ዎችን በማንሳት በተዛማች ዘውግነታቸው ይጎራበታሉ። እንደውም ለሳይንስ ልቦለድ መነሳት ተዋጽኦ አድርገዋል ተብለው ከሚገመቱ የፈጠራ ስራዎች መካከል አስማታዊ ጽሑፍ በቀሳል። ከዚህ በተጨማሪም በሳይንስ ልቦለድም ሆነ በአስማታዊ ጽሑፍ የሰው ልጅ ሞልሳቸው የማይችላቸውን መረጃዎች ኢ-ንቁ ከሆነው የአዕምሮ ክፍል በማውጣት ክፍተቱን ሞሉላቱ የጋራ የዕውቀት ምንጭ እንዳላቸው ከዚህ በታች ያለው ጥቅስ ሃሳቡን

የጠናክረዋል፤ "When there is not enough information about a given phenomenon, or people are for some reason incapable of acquiring it, they will take information from some other domain and supply the missing links" (Chernyshova, 348).

ነገር ግን የሳይንስ ልቦለድ እና አስማታዊ ጽሑፍ ከኢንቁው የአዕምሮ ክፍል የተገኘውን መረጃ እንዴት ያስተላልፉታል? ወይም እንዴት ያስረዱታል? የሚለው ላይ ልዩነት አላቸው። ነ Bassett (ገጽ 19) ሳይንስ ልቦለድ ከአስማታዊ እና ከሌሎች አይታመኔ እና ግምታዊ ጽሑፎች ጋር ያለውን ልዩነት ሶስት ነጥቦችን በመዘርዘር ያብራራሉ። አንደኛ ሳይንስ ልቦለድ ስለሳይንስ የሚገልጽ እና የሚያብራራ ሳይሆን ሳይንስ እንዴት በተግባር እንደሚሰራ የሚያሳይ ው፤ ("SF in terms not of 'what it is', nor of 'what science it refers to', but rather in terms of 'how it works'").

ሁለተኛ በልቦለዱ ውስጥ የሚነሳው ቴክኖሎጂ፣ መሳሪያ ይሁን ዕውቀት ከዘመኑ ሳይንስ ጋር የሚሰምር ነው፤ ("SF and its sub-genres relate to, rely on, and make connections with, 'real world' science or technology") ። ሦስተኛው ነጥብ የፈጠራ ራዎቹ ሳይንሳዊ ፈጠራን የተከተሉ ናቸው፤ ("They might come to be influential in the circuits of scientific and technical innovation") ።

እነዚህን መስፈርቶች መነሻ በማድረግ ወደ ጳውሎስ ትንታኔ ሳመራ አንደኛ "ሳይንሳዊ" ዳዮችን ማንሳት ብቻ አንድን ጽሑፍ ሳይንስ ልቦለድ አያደርገውም። የሳይንስ ልቦለድ መባልም የተነሱት ሳይንሳዊ ኀልዮት መስራት አለመስራታቸውን በሙከራ ይረጋገጣሉ ወይም ስተባበላሉ። ከዚህ ውጭም የሚያነሷቸው ሳይንሳዊ ፈጠራዎች ሳይንሳዊ አመክንዮ ሚቀርብባቸው እንጅ በእምነት የምንቀበላቸው "እውነት" አይሆኑም። በአስማታዊ ጽሑፎች ንደሚቀርቡት "የበራሪው ምንጣፍ" አይነት ትረካዎች ከዘመኑ ሳይንስ የራቁ አይሆኑም። ሳይንስ ልቦለድ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ ለመመለስ "የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ" ሚል ምላሽ በማስገኘት እንዴት እና ለምንን ማስተንተን የማያስችል ምላሽ አያቀርብባቸውም science replacing supernatural machinery" (ዝኒ ከማሁ፣ 18) ።

የመጨረሻው ቅኝት መሳይ ፅጌ (1993) *"የሳይንስ ራዕይ እና የቢሆን ዓለም* ልቦለዶች ሳይንስ ልቦለድ ባህርያት አንፃር ትንታኔ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ነው። የሁለቱ ናቶች ጉዳይ ሳይንስ ልቦለድ ከመሆኑ በላይ *የሳይንስ ራዕይ* እና *የቢሆን ዓለም* የተባሉትን ቦለዶች ለግምገማ ብንመርጥም ስለሳይንስ ልቦለድ ምንነት፣ በልቦለዶቹ ላይ ባለን አተያይም ነ በአጠናን ስልታችን እንለያያለን።

መሳይ፣ የሳይንስ ልቦለድ ባህርያትን ከገጸ ባህሪ፣ ከመቼት፣ ከታሪክና ከሚጻፉበት ተግባር ንጻር ተመልክቷል። ግቡም የሳይንስ ልቦለዶቹን ባህርያት በመመዘን "ሳይንሳዊ ልቦለድ ቸው"፣ "አይደሉም" የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ነው። ብቸኛ የመበየኛ መስፈርቱም ህርያቱ ብቻ ናቸው። የእኔ ጥናት ደግሞ ከሳይንሳዊ ገጽታዎች ባሻገር ሳይንሳዊ ጉዳዮች ነንትን ለመፍጠር ያላቸውን ሚና ይመለከታል። ልቦለዶቹ ምን አይነት ሳይንሳዊ ኀልዮት ንስተዋል? የተነሱት ኀልዮት ሰብአዊ ትዕምርት ምንድን ነው? የሚለውን ይፈክራል። ›ረጃዎቹንም ከባህል ጥናትን አንጻር ይተነትናል።

እንደ መሳይ በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ ጉዳዮች በሙሉ በእውኑ ዓለም ሚፈጸሙና ሊፈጸሙ የሚጠበቁ "እውነታዎች" ናቸው። በእርግጥ እነዚህ ትንቢቶች ቅዠት ና ህልም ሊሆኑ የሚችሉ ከንቱ ራዕይ ሊመስሉ ቢችሉም ቅዠትም አይደሉም፣  ህልምም ይደሉም። በዛሬ በዓለማችን የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዕድገት ደረጃ ላይ ተመርኩዘው የተለያዩ ይንቲስቶች የተለሟቸው የወደፊት እውነታዎች [ናቸው] (ገጽ 1)። "በገሃዱ ዓለም ሊከሰት ሚችል ነገር ላይ የተመሰረተ … ታሪክ ነው" (ገጽ 15፣ 17፣ 25፤ 31) ።

ከላይ የቀረበው ሃሳብ የሳይንስ ልቦለድን ሳይንሳዊ ፊት እንጅ ኪናዊ ባህሪውን አያሳይም። ቦለዱ፣ ሳይንስን የሚቀድም እና የሚመራ ሳይንሱም፣ ልቦለዱ በተለመለት መንገድ የሚጓዝ ከታይ አድርጎ አቅርቦታል። ስለዚህ "በሰማይ ላይ የሚበሩ መኪናዎች"፣ "በማርስ ውስጥ ሚኖረው ህይወት"፣… በልቦለዶቹ ውስጥ የተነሱ ተረኮች ሁሉ እርግጥ ናቸው። የልቦለዱም ራሲ በዛሬ ላይ ቆሞ ነገን ማየት የሚችል "ነቢይ" ነው። በዚህም የሳይንስ ልቦለድ በአጠቃላይ ሚጻፈው ስለወደፊቱ ለመተንበይና ሂስ ለመስጠት እንደሚጻፍ ተግባሩን ሲገልጽ ጠቁሟል።

በእርግጥ የሳይንስ ልቦለድ ለሳይንስ ቀስቃሽ ወይም መነሻ ሃሳብ ሊያቀብል ይችላል። ነይንስ እውነታዎችም ለሳይንስ ልቦለድ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የጠፈር ጉዞ መደረጉ በፊት የሳይንስ ልቦለዶችም ሆኑ አይታመኔዎች ጉዳያቸው አድርገው ጽፈውበታል። ነንደኛው ዕድገት ለሌላኛው በኀ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል። ነገር ግን ሳይንስ ዛሬ ነደረጋቸውና ያልደረሰባቸው ጭብጦች በሳይንስ ልቦለዶች ተነስተዋል። በሌላ መልኩም ሳይንስ ቀበላቸው የማይችላቸው እንደ ጊዜን መጠርመስ (time travel) ፣ እንግዳ ፍጡራን ምድርን ነኀብኘት፣ አማራጭ ታሪክ መፍጠርን፣… የመሰሉ ታሪኮች በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ ተካተው ገኛሉ። The world-models created by sf have not remotely passed the tests of xact knowledge in all cases. They are often naive, simplistic, and sometimes

imply false" (Chernyshova, 354). ስለዚህ ሳይንስም ሆነ የሳይንስ ልቦለድ ነገሮችን ሚቀበሉበት እና የሚያስተናግዱበት የተለያየ ዐይን እንዳላቸው መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ እንኳን "ልቦለድ" ተብሎ የቀረበ ሥራ ይቅርና ሳይንሳዊ ምርምር ላይ መርኩዘው የሚደረጉ ጥናቶችም በእርግጠኛነት ይሆናሉ ተብለው ሊደመደሙ እንደማይችሉ 3roderick 53) "How could sf be predictive? On the effective case argued by opper, the main reason for the future's cloudiness is the absolute npredictability of scientific research itself. Who can tell what will emerge next om the lab?" በማለት ይጠይቃል። በመሆኑም በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ ታሪኮች ተፈጸሙ እና ሊፈጸሙ የሚጠበቁ ተጨባጭ ዕውነታዎች ናቸው ብሎ ለመደምደም በቅድሚያ ሚነሱት /የተነሱት ጉዳዮች ከዚህ ቀደም የሚታወቁ መነሻዎች ያሏቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ሊያም የነበሩ ከሆኑ ቀጣይ ሊሆኑ ይገባል። ከትንቢቱ በፊት የሚታወቅ ተመሳሳይ እውነታ፣ ውጥ ይሁን ተግዳሮት አስቀድሞ መኖር አለበት። ነገር ግን ሳይንስ ልቦለድ የሚጻፈው ዛሬ ሪ በሌለ እና በእውነታ በማይታወቅ ታሪክ እና ጉዳይ ላይ ነው። ስለዚህ እውን የሚሆን "ነገ" ነ እውን የሆነው በራዕይነቱ ሳይሆን በሳይንስነቱ ነው።

በመሆኑም "ትንቢትነታቸው" መገለጽ ካለባቸው "በራዕይነት" ሳይሆን በግምትነታቸው ው። በግምታዊነቱ እውን ሆነው የተፈጸሙ ነገሮች ቢኖሩ፣ አንደኛ የተጻፉ ነገሮች ሁሉ ትጥታ ይፈጸማሉ ብሎ ለመደምደም መነሻ ሊሆኑ አይችሉም፤ ዘውጉን የነብይነት ሚና ንዲኖረው አያበቁትም። ይህ ማለት ሳይንሳዊ ልቦለድ የግድ "ወደ ፊት ያለውን ይናገራል" ሎ መደምደም ሆነ አዝማሚያዎችን አይቶ አጠቃላይ ባህርይው አድርጎ ማስቀመጥ ከባህሪው ጭ ባህሪ መጫን ነው። እንግዲህ መሳይ የሳይንስ ልቦለድን ትንቢት አከል አድርጎ ገልጸውም፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ላይ ሊመሰረት ይችላል ያስብለዋል እንጅ ሳይንሳዊ ሃቅ ንደማያደርገው የተለያዩ ፀሃፊዎች ያስረግጣሉ (John, Rieder 14፤ Rose 155)።

መሳይ (ገጽ 1) "በዛሬ መስታወት የወደፊቱን በማየት በብዕራቸው ነገን የቀረጹት የሳይንስ ቦለድ ፀሃፊዎች ለአዳዲስ ግኝቶችና ለውጦች መከሰት ከማንም በላይ አስተዋጽኦቸው ጠቀሳል" ብሏል። ከ1950ዎቹ ጀምሮ ዓለማችን በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ ላመጣችው ለውጥ ጋውን የሚወስደው የሳይንስ ልቦለድ እንደሆነም ገልጿል። እዚህ ላይ ሁለት ጉዳዮችን ንሳት ይቻላል። አንደኛው የጊዜ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የለውጡን አይነት ነው። ለምን የሳይንስ ዕድገት ለመለካት 1950 ለምን ተመረጠ? በምን መስፈርት? የታዩትስ

ለውጦች ምንድን ናቸው? የመሳይ ጥናት እንደምን መለሳቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሻሉ። የሳይንስ ልቦለዶች በተጠቀሰው ዘመን "ይፈጸማሉ" ብለው የተነበዩአቸውን ጉዳዮች መሰረት አድርጓል። በዚህ ዘመን ምን ምን ተተንብየው ምን ያህሉቹስ ተፈጸሙ? የሚሉት ጥያቄዎች ጉዳይ ደግሞ ሌላኛው የገቢር ችግር ነው።

በተጨማሪም "ሳይንሳዊ ዕድገት መመዝገብ ጀምሮበታል"፣ ብሎ ያነሳው ዘመን የሳይንስ ልቦለዶች "በ1950 ይፈጸማሉ" ብለው ያነሷቸውን ጭብጦች እና ትንቢቶች ይፈጸማሉ ብለው ካነሱበት ጊዜ ይጀምራል። የለውጦቹ ምንጭም የታዩት ራዕዮች ናቸው። ስለዚህ እንደ መሳይ አገላለጽ የሳይንስ ልቦለድ ምናባዊ ልቦለድ ሳይሆን ለሳይንሳዊ ተግባር ሲባል የሚጻፍ የደራሲው መገለጥ (revelation) ነው። እንግዲህ ስለ ሥነጽሑፍ ተግባርም ሆነ ስለ ሳይንስ ልቦለድ ያለን አተያይ ይለያያል ያልኩትም ለዚህ ነው።

በቅድሚያ የመሳይ ጥናት ጉድለት የሚጀምረው ያለ ምንጭ ሃሳቦቹን "አስተያየት እሰጣለሁ" በሚል አቀራረብ መቃኘቱ ላይ ነው። በመሆኑም በእሱ አስተያየት እና በገቢሩ መካከል የሚጋጩ ሃሳቦች እንዲቀርቡ ምክንያት ሆኗል። ዓለማችን በሳይንስ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለውጥ መቼ አመጣች? ለሚሉት ጥያቄዎች የተለያዩ ጸሃፊዎች ምላሽ ይሰጣሉ። በ1880ዎቹ የተጻፉት የሳይንስ ልቦለዶቹ በ1950 "ሳይንስ ይደርስበታል" ብለው ከሰጧቸው ግምቶች ይልቅ የዘመኑ ሳይንስ የራቀ እንደሆነ ገልጸዋል (Rose 43) ። ከዚህ በተጨማሪም ከተጻፉ በርካታ ልቦለዶች ውስጥ የተፈጸሙ እና ጥቂት የመፈጸም ዕድል የሚያገኙት ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ (Broderick 53) እንዲህ በማለት ያረጋግጣል፤ "Isaac Asimov confessed, 'Actually, there is very little in the vast output of science fiction, year after year, which comes true, or which is ever likely to come true'". ስለዚህ ሳይንሳዊ ልቦለዶች እና ፊልሞች የሰጡትን ግምት ይዞ 1950 የሳይንስ ዕድገት መለኪያ ዘመን ሆኖ ለመቆጠር አያበቃውም። እንደገናም "ትንቢትነታቸው" ለሁሉም ተፈጻሚ አለመሆኑ ልቦለዳዊ ደረጃቸውን ባያወርደውም የእውነት ተነጻጻሪ አድርጎ ማስቀመጥ ተገቢ እንዳልሆነ ማየት ይቻላል።

ሌላው "አስተያየት" የሳይንስ ልቦለድን ባህሪ በንድፈ ሃሳቦች ላይ ከመመስረት ይልቅ በመረጣቸው ልቦለዶች ውስጥ በታዩ ባህርያት ለማሳየት መሞከሩ ነው። ለምሳሌ፣ በገጽ (14) ላይ የሳይንስ ልቦለድ፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች የሚንጸባረቁበት እና ታሪኩ [እውናዊ እንዲሆን] እውነተኛ ምትሃት እንዲኖረው የሚያደርገውን የሰው ልጅ የህይወት ገጠመኝ የሚይዝ ሁለት

የታሪክ ክፍል እንዳለው ይገልጻል። አክሎም በመጀመሪያ እውናዊ ታሪኩ ከዚያም ሳይንሳዊ ትረካው ይጻፋል ይላል (ገጽ 15) ። ነገር ግን ትረካ እንደ እውናዊ ልቦለድ ሁሉ የታሪክ ሂደቱን ተከትሎ የሚፈስ እንጅ መጀመሪያ እውናዊ ታሪኩን ተጽፎ በኋላም ታሪኩን ሳይንሳዊ ለማድረግ ሳይንሱ የሚቀላቀልበት ጽሑፍ አይደለም። ከዚህ እስከ እዚህ ሳይንሳዊ ከዚያ እስከዚያ እውናዊ ተብሎም ሊለይ አይችልም። ይህ የስልት ጣጣ ነው። በታሪክ አወራረዱም አንዱ ከአንዱ የማይገናኝ ወይም ከተለያየ ቦታ መጥተው የሚገናኙ (coexist የሚያደርጉ) ሳይሆን አብረው የሚሸመኑ (coalesce የሚያደርጉ) እና የሚዋሃዱ ናቸው።

ሌላው በምዕራፍ ሦስት *"የሳይንስ ራዕይን* የሳይንስ ልቦለድ ነው፤ *የቢሆን ዓለምን* የሳይንስ ልቦለድ አይደለም" በማለት አጠቃሏል (ገጽ 45)። በተለይም *የቢሆን ዓለም* ን "የሳይንስ ልቦለድ አይደለም" ለማለት ያቀረባቸው ምክንያቶች መስፈርት ብሎ ካስቀመጣቸው ነጥቦች ውጭ በመሆናቸው ማጠቃለያው አሳማኝ እንዳይሆን አድጎታል። ከመስፈርቶቹ ይልቅ *የሳይንስ ራዕይን* ያህል ባለመሆኑ "*የቢሆን ዓለምን* የሳይንስ ልቦለድ አይደለም" በማለት ደምድሟል። አንደኛ እነዚህን መስፈርቶች እንዴት ሊመርጣቸው እንደቻለ ያቀረበው የንድፈ ሃሳብ መነሻ የለም። ሁለተኛ እነዚህ መስፈርቶች በምን ያህል መጠን ሲገኙ ነው "ሳይንስ ልቦለድ ነው" "አይለም" የሚባለው የሚለውን አስቀድሞ ለይቶ አላሳወቀም። ነገር ግን *የቢሆን ዓለም*፣ የሳይንስ ልቦለድን ለመለየት ያገለግላሉ ብሎ ያስፈራቸውን መለያ ባህርያት (ታሪክ፣ መቼት አቀራረጽ፣ ገጸ ባህሪ እና ከሚጻፍበት ተግባር) በሙሉ ያሟላል። የሳይንስ ልቦለድ አይደለም ሲልም አሳማኝ ነጥብ ሳያቀርብ መደምደሙ የጥናቱ ትልቅ ድክመት ይመስለኛል። ሦስተኛ በየልቦለዶቹ ውስጥ ያሉትን ሳይንሳዊ ባህርያት በውል ሳይቀመጡ፣ "የሳይንስ ራዕይ" ደራሲው "40 ያህል ሳይንሳዊ እውነታዎች" አሉ ስላሉ ብቻ "አሉ" ብሎ ቁጥር ከመግለጽ ባለፈ ያቀረበው መረጃ የለም። እንዲሁም *የቢሆን ዓለምን* አንድ ብቻ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ይዟል በማለት እርስ በእርስ የሚጋጩ ሃሳቦችን አቅርቦ " የሳይንስ ልቦለድ አይደለም" ብሏል። አንድን የሳይንስ ልቦለድ የሳይንስ ልቦለድ ነው ለማለትስ በቁጥር የበረከተ ሳይንሳዊ ኀልዮት መኖር ነየት የመጣ መለኪያ ነው? ጥናቱ ለዚህ መልስ የለውም። በጥቅሉ የመሳይ ጥናት ከተጠናበት ጊዜ መርዘም፣ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ከመሰራቱ እንዲሁም የመጀመሪያው ጥናት ከመሆኑ አንጻር የሚጣጣል አይሆንም። ነገር ግን ስለ ሳይንስ ልቦለድ እና ስለልቦለድ ያቀረበው መረጃ ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት ስላጣ ከዝንባሌ ባለፈ ጠንካራ ሃሳብ እንዳያቀርብ አድርጎታል።

## ምዕራፍ ሦስት፤ ትንተና

ቀደም ብዬ እንዳስተዋወቅሁት በዚህ ክፍል ለትንተና የመረጥኳቸውን ልቦለዶች የራስ ምታት፣ የቢሆን ዓለም፣ ኤማንዳ እና የሳይንስ ራዕይ ናቸው። ሳይንሳዊ ኀልዮት መሰረት በማድረግ በሳይንስ ልቦለድ ልማድ መሰረት በባህል ጥናት አቀራረብ አንጻር እተነትናለሁ፤እገመግማለሁ። እዚህ ላይ ደራሲዎቹ "የሳይንስ ልቦለድ ናቸው" ብለው ማሳተማቸውን እንደ መነሻ ቢያዝ፣ ምንም እንኳ የሳይንስ ልቦለድን ባህርያት ቢያሟሉም ምን ጉድለት አላቸው የሚለውም የሚገመገም ይሆናል። በተጨማሪም የልቦለዶቹ ጸሃፊዎች ልቦለድ ለመጻፍ ከሚጠይቀው የሥነ ጽሁፍ ችሎታ ባሻገር ጉዳያቸው ሳይንስ በመሆኑ ያላቸው ሳይንሳዊ ዕውቀት ምን ያክል ነው? ሳይንሳዊ እውቀት አላቸው? የላቸውም? ብለንስ መጠየቅ እንችላለን? እንዲሁም ይህን ዕውቀታቸውንስ በምን ያህል ልክ እና እንዴት ልንገመግመው እንችላለን? የሚሉት እና መሰል ጉዳዮች አብረው ይታያሉ።

በእርግጠኛነት የሳይንስ ልቦለድ ጸሃፊዎች ሳይንሳዊ ዕውቀት አያስፈልጋቸውም ብለን መደምደም አንችልም። ስለዚህ የሳይንስ ልቦለድ ደራሲዎች ሳይንሳዊ ዕውቀት ያስፈልጋቸዋል። ልዩነቱ ግን በምን ያህል መጠን የሚለው ይሆናል። እንደ ተፈጥሮ ሳይንስ ጸሃፊዎች ሳይንሱን ብቻ መዘን በማውጣት "ለምን?" እያልን ግድፈቶቹን በገቢር ሳንጠይቅ እንችላለን። በተፈጥሮ ሳይንስ የአንድ ሲደመር አንድን ሁለትነት የሁልጊዜ መርህ በህይወት ውስጥ ብሎም በስነጽሑፍ ውስጥ ላናገኝ እንችላለን። በመሆኑም ደራሲውንም ለምን ሁለት አላልክም? ብለን ልንጠይቀው አንችልም። ነገር ግን መርሁን ከጣሰና ለአንድ ሥነጽሁፋዊ ፋይዳ ሲል እንዳደረገው በታሪኩ ውስጥ ካላሳየ ግጼታውን እንዳልተወጣ ብቻ ሳይሆን መርሁንም እንዳላወቀ ያስቆጥረዋል።

በመሆኑም አንድ ጸሃፊ ቢያንስ ሊጽፍበት ስለተነሳው ጉዳይ በቂ የሆነ መረጃ እንዲኖረው ምርምር ሊያደርግ ይገባዋል። ምርምር ያደረገበትን ሳይንሳዊ ኀልዮም ታሪካዊ፣ ስነልቦናዊ፣…መልክ እየሰጠ ልቦለዳዊ ቀለም እየቀባ ከሳይንሱ ጋር አዋህዶ ሊያቀርብ ሊጠቀምበታል። ይህንንም በታሪኩ ውስጥ ሊያሳይ ይፈለግበታል እንጂ የሳይንሳዊ አስተሳሰቡን መርህ ሊጥስ አይገባም።

በመቀጠልም ልቦለዶቹ ማንትን ለመፍጠር፣ ለመገንባት ብሎም ለማስቀጠል ያላቸው ትዕምርቶችን በመፈከር አሳያለሁ። በልቦለዶቹ ውስጥ በርካታ ሳይንሳዊ ኀልዮት ተነስተዋል።

ነገር ግን ጎላ ያሉትን ወይም ሌሎችንም ጠቅልለው ሊገልጹ ይችላሉ ያልኳቸውን ሁለት ሳይንሳዊ ሃሳቦች በማብራራት ልቦለዶቹን በመተንተን አቀርባለሁ። በዚህም የዘረመል ምህንድስና (genetic engineering) የሚባለው ሳይንሳዊ ገጽታ የያዙትን *የራስ ምታትን* እና *የቢሆን ዓለምን* አስቀድሜ የኮምፒዩተር መገናኛ ቁጥጥር (cybernetics) የተቃኙትን *የሳይንስ ራዕይንና ኤማንዳን* በመቀጠል አቀርባለሁ። በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ የሚነሱት ሳይንሳዊ ጉዳዮች ትኩረት ሰው በመሆኑ ሳይንሳዊ ገጽታዎችን ነቅሼ በማውጣት ከማንነት አንጻር እተነትናለሁ።

## 3.1. *የራስ ምታት*

የራስ ምታት ዋነኛ ሳይንሳዊ ጉዳዩ የአዕምሮ ንቅለ ተከላ ሲሆን በአራት ሰዎች ላይ ተሞክሯል። የመጀመሪያው የአዕምሮ ንቅለ ተከላ የተደረገው ከኢትዮጵያ ለትምህርት ወደ አሜሪካ በሄዱ ሁለት የህክምና ሳይንስ ተማሪዎች ላይ ነው። ተማሪዎቹ ዳዊት እና ዓብዱል ይባላሉ። ዳዊት የክርስትና፣ ዓብዱል ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ ናቸው። በዳዊት አሽከርካሪት ከሚኖሩበት ቦስተን ከተማ ለመዝናናት እንደወጡ መኪናቸው ይገለበጥ እና ገደል ይገባሉ። በአደጋውም የዳዊት ደረቱ፣ ሆዱ እና እግሮቹ ከጥቅም ውጭ ሲሆኑ ዓብዱል ደግሞ አካሉ ባይጎዳም ደም ወደ አዕምሮው በመፍሰሱ ለሞት ይቃረባል። በዚህም ይማሩበት በነበረው ሆስፒታል ምርምር በማድረግ የሚታወቁ ፕሮፌሰር ማርዶካይ “የተሻለ መፍትሄ ነው“ እና ሰብአዊ” እርምጃ ነው ብለው ያመኑበትን አማራጭ ይወስዳሉ። የማይጠቅመውን አካል በማስወገድ ያልተጎዳውን አካል ላልተጎዳው አንጎል ማስቀመጫ ያደርጉታል። በዚህም የዳዊት አካልና የዓብዱልን አዕምሮ ሲሞት፣ የዓብዱል አካል እና የዳዊት አዕምሮ እድሜ ይራዘማል።

በዚሁ ተመሳሳይ ወቅት በመኪና አደጋ ለሞት የሚያደርስ የአካል ጉዳት የደረሰባትን ሳንድራ የምትባል ጥቁር አሜሪካዊት ህፃን እና በአዕምሮ ዕጢ ህመም የምትሰቃይ እና ሞቷን የምትጠባበቅ ቲና የምትባል ከነጭ አሜሪካዊ ዘር የምትመዘዝ ህጻን ልጅ ላይ የአዕምሮ ቅይይር ያደርጋሉ። በዚህም የሳንድራ አካል እና የቲና አዕምሮ እንዲሞት ይወሰንበታል። የ”ሳንድራ”ን አዕምሮ በ”ቲና” አካል ውስጥ በማድረግ የህክምናው ውጤት ይጠናቀቃል። ውጤቱ ግን “ጎሽ” የሚያሰኝ አልሆነም። ምክንያቱም ሳይንሳዊ ውጤቱ የተዘራበትን ማህበራዊ ባህላዊ መሰረት የሚነቀንቅ ብሎም የሚያፈርስ በመሆኑም ነበር። በዚህ የተነሳም ግጭት ይፈጠራል። የመጀመሪያው ግጭት “እኔ ማን ነኝ?”፣ “እኔ ማን አይደለሁም” የሚለው ሲሆን “እሱ/እሷ”

"እሱ አይደለም/እሷ አይደለችም" የሚለውም ሌላ መልኩ ነው። በ"ዓብዱል" አካል የሚንቀሳቀሰው "ዳዊት" ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ እና በ"ቲና" አካል የሚንቀሳቀሰው የ"ሳንድራ" አዕምሮ አሜሪካ ውስጥ መሆኑ ማህበራዊ ፖለቲካዊ መልክ በመያዙ ግጭቱን ያባብሰዋል።

የአካል እና የአዕምሮ ልውውጡ "ሃይማኖት" እና "ዘር" በሚሉ ርዕዮተ ዓለማዊ ጽንሰ ሃሳቦች ታስሯል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖት፣ አሜሪካ ውስጥ የቆዳ ቀለም የማንነት መግለጫ ብቻ ሳይሆኑ የርዕዮተ-ዓለም ማቀንቀኛ፣ የኀይል መጠበቂያና ማስጠበቂያ መሳሪያም ናቸው። እንግዲህ ሳይንስ ልቦለድ ትኩረቱ ሳይንሳዊ ጉዳዮች ናቸው ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም በፍካሬ ሂደቱ ሰዋዊ ጉዳዮች ላይ እንደሚደርስ መነሳቱ ይታወሳል። በተለይም በተዛማች ውጎች አማካይነት ማንነት እንዴት እንደሚፈጠር፣ እንደሚተከል እና እንደሚገለጽ ከሳይንሳዊ ኙቱ ጋር አያይዘን መመልከቱን እንቀጥል።

ልቦለዱ በዋነኛነት የሚያጠነጥነው "ሰው ማን ነው?" በሚለው ጉዳይ ላይ ነው። የሰው ግንነቱ ያለው እምኑ ላይ ነው? እና እስከ ምን ድረስ ነው? የሚለው ሃሳብ የታሪኩ ማስኬጃ ው። ማንነቱን የሚወክለው አካሉ (body)፣ አዕምሮው (mind) ወይስ ነፍሱ (soul) ነው? ሚለውን መነሻ ሃሳቡ አድርጓል። በዚህ የተነሳም የቲና/ሳንድራ ጉዳይ ፍርድ ቤት ይደርሳል። ሁለቱም ወገን ያሉት የህግ ባለሙያዎች ጥብቅና እንደቆሙለት ሃሳብ ቲና ወይም ሳንድራ ነች" በማለት ይከራከራሉ። በኋላም የፍርድ ሂደቱ እንዲዘገይ ይደረጋል፤ ነገር ግን ማህበራዊ ውሱ አልበርድ ይላል። ውጤቱ ኢትዮጵያም ውስጥ ሆነ አሜሪካ ማህበራዊ ህይወት ናግቷል፤ ደም አፋሷል፤ ህይወት አስከፍሏል (ገጽ 63-64)።

የዳዊት/ዓብዱል ጉዳይም እንደ ቲና/ሳንድራ ፍርድ ቤት ደርሶ ባያወዛግብም ማህበራዊ ውሱ በሁለቱም ወገን ቀጥሏል። ልዩነቱ በዓብዱል ቤት የከፋ ቢሆንም በዳዊት ቤተሰብም ግር ይፈጠራል። የዳዊት እህት ሄለን ወንድሟን ታፈቅረዋለች፤ ሳሮን "ወዳዋለች" ብላ ማሰብ ታኮርፋታለች። በዓብዱል ቤት ግን የማይበርድ እሳት ይለኮሳል። ዓብዱል ስለሞተ ላቅ ወንድሙ መሐመድ ባለቤቱን ወርሶ አግብቷል። ዘይነብም አርግዛለች። "ዳዊት" ኢትዮጵያ ገባ በኋላ ልጆቹ እና ባለቤቱ መንገድ ላይ ያዩታል፤ ልጆቹ በአባታቸው ፍቅር ይሳቀቃሉ፤ ለቤቱ በድንጋጤ ራሷን ትስታለች። ስትነቃ የሁለቱም ልትሆን እንደማትችል ታስባለች። ቷን፣ ሁለት ልጆቿን፣ ወላጅ እናቷን እና ቀዬዋን ትታ ትሰደዳለች። ከዚያም ቤተሰብ

የሚባለው ነገር ይፈርሳል፤ ማህበራዊ ተቋሙ ይናጋል። ሐይማኖታዊ እሴቱ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

የዓብዱል አባት እና እናት፣ ሁለት ወንድሞቹ፣ የዘይነብ እናት፣ የመሐመድ ሁለት ሚስቶችና ዘጠኝ ልጆች፣ እንዲሁም የኣብዱል ሁለት ልጆች በአጠቃላይ የአስራ ስምንቱን ተስፋ አጨልመው ዘይነብ እና መሐመድ ወደ ሌላ የፍልሚያ ምዕራፍ ቤቱን ለቀው ጠፉ። በአንድ ቤት ውስጥ እንዳልኖሩና በአንድ አልጋ እንዳልተኙ፣ ልጅም እንዳልጀመሩ፣ በሁለት ጎራ ተከፋፍለው የጎሪጥ ሲተያዩ ይሁን ሲጠፋፉ ባይረጋገጥም ሚናቸውን ለዩ (ገጽ 223) ።

በታሪኩ መጨረሻም መሃመድ ዳዊትን ለመግደል ሲሞክር ዳዊት ቆስሎ ሆስፒታል ይገባል። ዶክተር ደስታ ዘይነብን ከደበቀበት ሐገር ደውሎ እንድትመጣ፣ ባለቤቷ እንደሆነ እንድታረጋግጥ ይልክባታል። ስትመጣ ሆስፒታሉ ውስጥ ራሱን የሳተውን ቁስለኛ ባለቤቷ እንደሆነ ትለያለች። መሐመድ ወንድሙ ነቅቶ ለፖሊስ እንዳይጠቁመው ስለሰጋ ወደ ሆስፒታል ይመጣል። በዚያም ዘይነብን ያገኛታል። መሃመድ ነፍሰ ጡር እንዳልሆነች ሲያይ ልጁን እንደወለደችው ሳይሆን እንዳስወረደችው ያረጋግጣል። “ከሃዲ ነፍሰ ገዳይ” በማለት በጩቤ ወግቶ ይገድላታል። አካባቢው በደም ይጨቀያል። መሐመድ ለመሸሽ ይሞክራል። እንደማይችል ሲያውቅ ራሱን ከፎቅ ይወረውራል፤ ይሞታል። ዶክተሩም ዘይነብ እስክትመለስ ህፃን ልጇ ታቅፎ ቢጠብቃትም ላትመለስ ታሸልባለች። በአንድ ጊዜም ሶስቱም ልጆቿ ያለ ወላጅ ይቀራሉ (ገጽ 282)። በዓብዱል ቤት የሆነውም እንዲሁ ነው።

እንግዲህ የማንነት ውል የታሰረው በሃይማኖት ላይ ነው የሚለውን አጠንክረን እንያዝና በዓብዱል/ሙስሊም ቤት ውስጥ የተፈጠረውን ጭፍግ ታሪክ በዳዊት / ክርስቲያን አንጻርስ እንዴት ተመሰለ? የሚለው ደግሞ በንጽጽር እንመልከት። የዳዊት ባለቤት ሳሮን እንደ ዓብዱል ባለቤት ሁለት ልጆች ያሏት ብትሆንም አላገባችም። በአንጻሩ ዘይነብ ባለቤቷን እየወደደች ከፍላጎቷ ውጭ ተገድዳ የአባት ያህል የሚበልጣትን የባለቤቷን ታላቅ ወንድም አግብታ ሶስተኛ ሚስት ሆናለች (ገጽ 226)። እምቢ ለማለት ስትደፍርም የሃይማኖት አባቶች በማስፈራራት አስገድደው አጋብተዋታል። በዚህ መንገድ የተፈጸመውን ጋብቻ ዘይነብም ሆነች ሌሎች አይደግፉትም። በዓብዱል ቤት መከራው እንዲከብድ ያደረገውም ጋብቻው ነው። ጋብቻው ከሌላ ወገን ጋር የተደረገ ቢሆን ቀውሱን ይቀንስ ነበር። ሁለቱ ቤተሰቦች አይከፈሉም፤ አይተጣጡም፤ ስጋ በስጋው ላይ አይነሳም ነበር፤ “እንዴት የወንድሙን ሚስት ያገባል?” የሚል “የምግባር”

ጥያቄ “ሃይማኖቱ ይፈቅዳል” እየተባለ እንኳ ጥያቄው አይበርድም። “ይፈቅዳል” የተባለው “ዲኑ”ን ይተቻሉ። “ዲኑ” ደግሞ ሃይማኖቱ ነው።

በልቦለዱ ውስጥ እንዲህ አይነቱ ሃይማኖታዊ ጋብቻ የእምነቱ ተከታዮችም ወደውና አምነው የተቀበሉት ሳይሆን ሳይፈልጉት የተጫነባቸው ቀንበር ሆኖ ተመስሏል። በተረፈ የአስተምህሮው ኮናኞችና ዳኞችም ከእምነቱ ውጭ ያሉ ክርስቲያኖች ናቸው። የሃይማኖት መሰረቱን እንዲያስረዳ ሆነ መልስ እንዲሰጥ አንድም ሙስሊም ዕድሉን አያገኝም። በዚህም ሁለቱ ሃይማኖቶች እኩል ስፍራ እንዳልተሰጣቸው ማሳያ ይሆናል። ይህን ሃሳብ በበርካታ የታሪኩ መልኮች እያጠናከርን እንመልከተው።

ታሪኩ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሚከተለው ዳዊትን/ክርስቲያንን ነው። ዓብዱል ግን የእግረ መንገድ ማንነት ያለው ለራሱ ሳይሆን በሌላ ራስ (agency) ውስጥ የተገለጠ ደብዛዛ ምስል ነው። ምክንያቱም ዓብዱል ከተራኪው ማስተዋወቂያ ውጭ ማንነት ያለው “ሰው” ሆኖ ሲናገርም ሆነ ሃሳቡን ሲገልጽ አናደምጠውም። ለውርርድ ያህል ሁለት ቦታዎች ላይ “ይናገራል”። የንግግሩ ጭብጥ  የተራኪውን አቋም ከመግለጽ ያለፈ አልነበረም። አንደኛው ወደ አሜሪካ እንዴት እንደሄደ የገለጸው ሲሆን በኋላም ላይ እንደምንመለከተው በግል ተጻጽፎ መሄዱ አካሉ እንኳ አገሩ ሄዶ እንዳይቀበርም ሆነ ጠያቂ እንዳይኖረው ያደረገውን ምክንያት የተናገረበት ንግግር ነው (ገጽ 11)።

ሁለተኛው ደግሞ ስለ ባለቤቱ “የሚስቴ ውበት ልገልጸው ከምችለው በላይ ነው” በማለት የገለጸው ሲሆን ዳዊትም አላዳመጠውም፤ “ዳዊትም ሩቅ አገር ተጉዞ እቤቱ ውስጥ ገብቶ በሃሳቡ ከሚስቱ እና ከልጆቹ ጋር በሃሳብ ህብረት በማድረጉ ለዓብዱል ንግግር ምላሽ አልሰጠውም። ከዓብዱል ጋር በአሜሪካ ጎዳና ላይ አይደለምና” (ገጽ 19)። ነገር ግን ዳዊት ዝም ያለው ሃሳቡ ስላልጣመው ስለመሰለው የእሱ እይታ መሆኑን በድጋሚ ይናገራል።  በአጠቃላይ ዓብዱል አይናገርም፤ ሲናገር ሲሞክርም አይደመጥም፤ ድምጽ አልባ ነው።

የዳዊት/ዓብዱል ማንነት እንዴት እንደተፈጠረ ለማወቅ የሃይል ግንኙነቱን (power relation) ማየት ያስፈልጋል። የማንነት መሰረት የተጣለው ከፍ ሲል እንደተገለጸው በታሪኩ መጀመሪያ ላይ ነው። በዳዊት አማካይነት፣ ስለ ዳዊት ጥቅም ዓብዱል ተፈጥሯል። ዓብዱል ለትምህርት ወደ ውጭ የሄደውም የዳዊትን ማንነት ለመስራት እንጂ በራሱ ለመታወቅ አልነበረም። ተራኪው ዳዊት ጎልቶ እንዲሳል አንቀዥቅዥ ወስዶ ያጋጨዋል። መኪናውም

ይገለበጣል። አሽከርካሪውን ደግሞ ዳዊት ነው፤ ዓብዱል ይሞታል፤ ከታሪክ መዝገብ ስሙ ይጠፋል። መኪና የሰው አምሳል ነው። የቴክኖሎጂ ውጤት የሰው አዕምሮ ነጸብራቅ እንደሆነ በሚት ፊጠራ ላይ መነሳቱ ይታወሳል። ይህን ሃሳብ የሚያሽከረክረው ዳዊት ደግሞ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ዓብዱል በዳዊት ሃሳብ እና ዕቅድ የሚንቀሳቀስ "ቁስ" እንጅ ማንነት የነበረው "እኔ ባይ" አልነበረም። ለምን ቁስ እንደተባለም ወደ ኋላ ላይ አስረዳለሁ።

ከአደጋው በኋላ የሞተውን አካል ወደ አገሩ ለመላክ ሲታሰብም የዓብዱል አካል ይህን ክብር አያገኝም። ኑሮውን ሳይሆን "ሞቴን በአገሬ ያድርገው" ብሎ በሚያምን ማህበረሰብ ውስጥ ያለፈው ዓብዱል ይህን ዕድል ይነፈጋል። የዳዊት ሙት አካል ግን ወደ አገሩ ይላካል። ሰው አዕምሮ/ሃሳቡ ነው የሚል መደምደሚያም ስላለው የዳዊት አዕምሮ ይተርፋል። ከዳዊት አዕምሮ እና ከዓብዱል አካል ተዋጥቶለት የቆመው ማንነት በህክምና ወቅት ዳዊት/ዓብዱል ቢባልም "ያ" ማንነት ራሱን ሲያውቅ "ዳዊት" በሚል ስም ተጠራ እንጅ "ዓብዱል" አልተባለም።

ሌላው ማሳያ "ዳዊት" ከህክምና ነቅቶ ራሱን በመስታዎት ሲመለከት የለበሰውን የዓብዱልን አካል እንደሆነ ይገነዘባል፤ በሌላ መልኩም ማንነቱን ስለተረዳ ይደነግጣል። ስለ ራሱ ያለው ትርጉም ይምታታበታል። ማንነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የሚመሰረተውም እዚህ ላይ ነው። መስታወቱ የጠፋውን ራሱን ወደ ውስጥ ገብቶ ያየበት፣ ማን ነኝ? ብሎ የጠየቀበት፣ የመረመረበት፣ እና የፈለገበት የአዕምሮ ውስጥ መንገድ ነው። ይህም ከራስ ጋር የተዋወቀበት ለማንነቱ የተገነዘበበ ስልት ሲሆን ቴዎድሮስ ገብሬ "አስተርዕዮ-ርዕስ" ይለዋል። "ያየኸው ጓደኛህ አካል የሚያስፈራ ነገር ሳይሆን በምድር ላይ እንድትኖር የረዳህ አጋዥ <u>መሳሪያህ</u> ነው" ትለዋለች (ገጽ 46፣ መስመር ከራሴ)። የመስታዎቱ አገልግሎትም "እኔን" ብሎ የሚያምነው እና የሚያስበው እንዲሁም አዋቂውን እኔ የሚለውን ማንነት ማገናኘት ነው።

ከፍ ሲል ዓብዱል ድምጽ አልባ፣ የተሞላውን የሚናገር እንጂ ራሱን የማይገልጽ መሆኑን ካስታወስን የተሰጠው ስፍራ የቁስ ያህል እንጅ ሰብአዊ ክብር እንዳልነበረው ያሳያል። እስከ ታሪኩ መጨረሻም ከአካል እና ከአዕምሮ ተዋጥቶ የተሰራ ማንነት ዳዊት/ክርስቲያን በሚል ስም የሚጠራ እንጅ ዓብዱል/ሙስሊም አልነበረም። ይህን ስም የማግኘት መብት ሊንቁው አዕምሮው (ደራሲው/ተራኪው ) ለዳዊት / ክርስቲያን ሲሰጥ ምን ያህል እንደወገነ ከቲና/ሳንድራን ታሪክ ጋር በንጽጽር ደግሞ እንመልከት።

ሳንድራ/ቲና ላይ የተደረገው ምርምር አሜሪካ ላይ ብጥብጥ በማስከተሉ ሌላ ቀውስ እንዳይፈጠር "ዳዊት" እንዲገደል ይወሰናል። በዶክተር ባርባራ አማካይነት ከአሜሪካ እንዲወጣ እና ወደ አገሩ እንዲገባ ይደረጋል። ከመጀመሪያው ሞት ቀጥሎ ከወገኑ ውጭ የሆነች ዶክተር "ታዳጊ መልዓክ" ትሆንለትና ከሁለተኛ ሞት ያመልጣል። ተዓምር በሚባል መንገድ ለአገሩ ምድር ያበቃዋል። በተለያየ ወቅት ቢሆንም አካሉም ሆነ አዕምሮው አገሩ ይገባል።

የሳንድራ/ቲና ጉዳይ የዓብዱልን ታሪክ ለመስራት እንዴት እንደዋለ እንመልከት። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት ተቃርኖ አሜሪካ ውስጥ ካለው የቀለም ልዩነት ጋር አነጻጽረን እንመልከተው። አሜሪካ ውስጥ የነጭ/ጥቁር ግንኙነት ተቃርኖ የነበረ፣ መስልጠን የሚባለው ሰብአዊ ተግባር ሳያለዝበው ዛሬም ድረስ የቀጠለ ትኩስ አጀንዳ ነው። በሳይንሳዊ ውጤቱ የጎዳና ላይ ነውጥ በመነሳቱ፤ የዘር ግጭት የቀን ተቀን እውነት፣ የአደባባይ ሚስጢር በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት የተሞከረውም በህግ ነበር።

በአንጻሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ተቃርኖ ክርስቲያን/ሙስሊም የሚሉት ግጭቶች ነፍጥጠው የወጡ ማህበራዊ ችግሮች እንዳልሆኑ እናስተውላለን። ከሃይማኖታዊ ቀኖናው ሬልቅ ማህበራዊ ትስስሩ የፈጠረው ጠንካራ ግንኙነት እንደሚያመዝን የተለያዩ ጥናቶች ሬጠቁማሉ (ሠሚራ መሃመድ 2005 )። ስለዚህ በዳዊት ምክንያት የተፈጠረው ችግር ወደ ፍርድ ቤት፣ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አላመራም። ግጭቱም የተመራው ይፋዊ በሆነ መንገድ ባለመሆኑ ኢ-ንቁ በሆነው የአእምሮ ክፍል ውስጥ ተገድቧል። ነገር ግን ኢትዮጵያን የክርስቲያን ደሴት" አድርጎ ከማሰብ ባለፈ ይህን አስተሳሰብ ለማስቀጠል ያለውን ፍላጎት ተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ላይ እንደሚታይ መሃመድ ዓሊ ይገልጻል። እንደ መሃመድ ጥናት በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት መካከል ያለው ግንኙነት በተቃርኖ የተመሰረተ ንደሆነ በገጽ 22 ያስረዳል። ይህ አስተሳሰብ ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የቀደመ ቢሆንም እስከ ዳማዊ ሐይለ ስላሴ ዘመን ለመቀጠሉ ማሳያ የሚሆኑ በአማርኛ የተጻፉ ጽሑፎችን አጣቅሶ ሳይቷል። በመረጣቸው ስራዎች ክርስቲያኖች ከፍተኛ ሙስሊሞች ግን ዝቅተኛ ስፍራ የተሰጣቸው ይመስሉ ነበር። ይህን ማህበራዊ መሰረት በ ራስ ምታት ላይም መደገሙ ስተሳሰቡ አሁን ድረስ የዘለቀ ለመሆኑ / ምንም እንኳ ልቦለዱ አንድ ቢሆንም/ ጠቋሚ ነው።

(Cavallaro 34) በማንነት ቀረጻው ወቅት አንደኛውን ወገን አልቆ ሌላኛውን ደግሞ ኮስሶ በማሳየት በኩል የተቃርኖዎች አቀማመጥ ነጋሪ እንደሆነ ትገልጻለች። በተቃርኖ (binary pposition) በሚገለጽበት ወቅትም በግራ በኩል ያለው ተጠቃሚውን ሲያመለክት በቀኝ በኩል

የሚሰለፈው ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ነው። በዚህም ዳዊት/ዓብዱል እና ሳንድራ/ቲና ተብሎ መገለጹ ለ"ዳዊት" እና ለ"ሳንድራ" የተሰጠውን ስፍራ የተጠቃሚነት መሆኑን ይጠቁማል። ስለዚህም ክርስቲያን/ሙስሊም፣ ነጭ/ጥቁር የሚሉት አንደኛውን ተጠቃሚ ሌላውን ተጎጂ በማድረግ እንዲሳሉ አድርጓል። ነገር ግን ከ"ቲና" ይልቅ ለ"ሳንድራ" ስፍራ ቢሰጣትም "ሰው" ተብላ የተጠራቸው ግን "ቲና" ነች። ስለዚህ የሚጋጩ ሃሳቦች እንደመጡ ስናስተውል "ለምን? "ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

አንደኛ የሳንድራ/ቲና ማንነት ከሚታወቅበት መንገድ አንዱ በስም መጠራት እና "እከሌ" ተብሎ መታወቅ ነው። "ዳዊት/ዓብዱል" "ዳዊት" ሲባል በአንጻሩ "ሳንድራ/ቲና" በአንድም ስም አይጠራም። ይልቁንም "ነጯ ልጅ"/ "ጥቁሯ ልጅ" በመባል በጉዳዩ ብቻ በመታወቅ እስከ ታሪኩ ፍጻሜ ዘልቋል። ስለዚህ ሰው ደግሞ ሲጠራ አቤት እንዲልበትም ይሁን እንዲታወቅበት ስያሜ ያስፈልገዋል። "እኔ እንትና ነኝ" ማለቱን ትቶ "የእንትና ነኝ" ማለት ሲጀምር የባለቤትነት (subject) ስፍራዉን እየለለቀቀ ጉዳይ፣ ነገር (object) እየሆነ ይመጣል። የሚታወቅውም በማንነቱ ሳይሆን በምንነቱ ይሆናል። ማንነት የሚታወቀው ደግሞ ባለቤት የመሆን ድርሻን በመውሰድ ነው፤ "Identities are . . . the points of temporary attachment to the subject positions which discursive practices construct for us" (Storey 79). ስለዚህ የቲና/ሳንድራ ምንነት ነጭ/ጥቁር ተብሎ በመጠራት መዝለቁ ስለማንነት ሳይሆን ስለማንነት መግለጫ እያወራ እንደሆነ ማሳያ ነው። በዚህም በጉዳይ ደረጃ ለጥቁር/ሳንድራ የተሻለውን ቦታ እንደሰጠው መረዳት ይቻላል። እንዲሁ ስለ ሰውነት ሲታሰብም የዳዊት/ዓብዱል ማንነት ቅድሚያ ይሰጣል። ይህ የሰው ማንነት የፕሮፌሰሩን ሃሳብ ሁሉ ማስለወጥ የሚችል አቅም ነበረው። የሰራውን/የፈጠረውን አዕምሮ እና የፈጣሪውን የፍች መፍጠሪያ መንገድ የሞገተ እና ትርጉሙን ከእሱ አንጻር እንዲለወጥ ያደረገ ሰው ነው። ያ "ሰው" ደግሞ በዳዊት የተወከለው ማንነት ያለው "ሰው" ነው።

እንግዲህ ሰው "አዕምሮ/አካል" ነው የሚለውን ለማሳየት "ዳዊት"ን "ዳዊት" ያሰኘው አዕምሮው ነበር። በትይዩ የ"ሳንድራ" አዕምሮ በ"ቲና" አካል ውስጥ ካለ ያ ማንነት ስያሜ ያገኝ ሊባል የሚጠራው "ሳንድራ" ተብሎ ነበር፤ ግን አልተባለም። ወይም "ሳንድራ"ን "ቲና" ካሉ "ዳዊት"ን "ዓብዱል"ን ማለት ነበረባቸው፤ ግን አላሉትም። ስያሜ ሳይሰጠው ዕውቅና ያገኘው ደግሞ የ"ቲና" ማንነት ነው። በፍርድ ሂደቱ ፕሮፌሰሩ ወግነው የተከራከሩት ለአካል/ለ"ቲና"

ነው፡፡ በተጨማሪም ለ"ቲና" እናት "ልጅሽ ናት" ሲሏት በድጋሚ ለአካል ዕውቅና መስጠታቸው ነው፡፡ በዚህም ሰው "አካል ነው" የሚል የቁስ አካላውያንን አመለካከት እናገኛለን፡፡ በተቃራኒው ጉዳዩን ከዳዊት አንጻር ካየነው ሰው "አዕምሮ ነው" የሚል የሃሳባዊያንን ርዕዮት ያሳየናል፡፡ እነዚህ ሁለት አመለካከቶች የሚቀዱት ደግሞ ፍጹም ተቃራኒ ከሆኑ የዕውቀት ስርዓቶች እንደሆነ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ከሰፈረው ሃሳብ ማስታወስ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ፕሮፌሰሩን "የሳይንሱ ዓለም አስተሳሰብ ማንጸባረቂያ ናቸው" ብለን ከተነሳን ለሁለቱ አስተሳሰብ እኩል ስፍራ በመስጠት የሚወግን የዓለም አመለካከት የለም፡፡ አሊያ ዓለማቱ አንድ ሳይሆኑ ሁለት እና ከዚያ በላይ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህን ለመለየት ደግሞ ወይ አስተሳሰብ መታረቅ አለበት፤ ወይ ዓለማቱ መታወቅ አለባቸው፡፡ ዓለሙ አንድ ከሆነ አንደኛው አመለካከት ሊቀየር ይገባል፡፡ ዓለማቱ ከተለያዩም ተለይተው መታወቅ ነበረባቸው፡፡

ስለዚህ በልቦለዱ መጨረሻ ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ ይገጥመናል፡፡ ሰው "አካል" ነው የሚለው አስተሳሰብ ይሻራል፡፡ ዳዊት ፕሮፌሰሩ በፍርድ ቤቱ ክርክር ማስረጃቸውን ቲና/አካልን አስቀድመው ሳንድራ/አዕምሮን ሁለተኛ አድርገው በቴሌቪዥን ማስረጃቸውን ሲያሰሙ እንደ መግለጫቸው "ዳዊት" ዓብዱል ነው፡፡ በንዴት ደውሎ "እኔ ማን ነኝ?" በማለት ሲጠይቃቸው ነንተማ "ዳዊት ነህ" ሲሉ ይመልሱለታል፡፡ "ዓብዱል ነህ" እያሉኝ እኮ ነው ሲላቸው፣ "ይህን ሚል ቢኖር "የአዕምሮ በሽተኛ" መሆን አለበት፡፡ እኔ እንደዚያ አላልኩም አልልምም" በማለት እርግጠኛነት ይመልሱለታል (ገጽ 255)፡፡ "ዳዊት" የሳንድራ ግልባጭ መሆኑ እና ለእሷ ተሰጠው ትርጉም ለእሱም እንደሚሰራ ሲገልጽላቸው ተራኪው በመካከል ይገባና የአስተሳሰብ መቀየሪያ ምክንያት ያቀርባል፡፡ "ግልባጩ እንደዚያ የሚናገር በመሆኑ ነገሮች ተደበላለቁበት" ማለት የፕሮፌሰሩን ሃሳብ መለወጥ ይነግረናል፡፡ ከዚያም ፕሮፌሰሩ አስቀድሞ ለብዙ ዘመን ምነት ሆኖ የቆየውን አስተሳሰባቸውን ይጠራጠራሉ፡፡ "ይቅርታ ይህን ያላስተዋልኩት ነገር ለሆነ እንዳስብበት ዕድል ስጠኝ" ይሉታል (ገጽ 255)፡፡ እንግዲህ ፕሮፌሰሩ አምነው ለፍርድ ት የሰጡትን ቃልን ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውን ሲመሩበት የቆዩበትን ፍልስፍናቸውን ድንገት ዳዊት ጥያቄ ይቀይሩታል፡፡ "'ስለ ሰው ልጅ ክቡርነት የተረዳው ዳዊት ነው፡፡ ዕውቀቴ ተረፈልኝ ነገር ቢኖር ምናልባት ሰውን እንደ ቁስ-አካል መመልከት ብቻ ሳይሆን አይቀርም?' ል ራሱን በራሱ አማረረ" ይላል (ገጽ 258)፡፡ ከዚያ ስህተታቸውን ይረዳሉ፤ ስተሳሰባቸውንም ይቀይራሉ፡፡

በአዝማሚያ መልክ እንደተገለጸው ሳይንሳዊ ውጤቱ የሽብር ተግባር ለመፈጸም ተዘጋጁና በህጋዊ መንገድ ለተቋቋሙ የመንግስት የስለላ ድርጅቶች እና ለማፊያዎች ወንጀል

መፈጸሚያነት የማዋል ፍላጎት እንዳለም ተመልክቷል። መጀመሪያ ከታሰበበት ዓላማ አፈንግጦ የተለየ አቅጣጫ ይይዛል። ማንም በሰላም ወጥቶ መመለሱን እንዳያምን ያደርገዋል። አካሉን ይዞ ወጥቶ የሚመለስ መኖሩ የወደፊት ስጋት ይሆናል። ሰው በ"ሰውነት" ክቡርነቱን ያጣና የመለዋወጫ ሸቀጥ ይሆናል፤ "human life will become more and more a technological commodity" (Anthony 298). ሳይንስንም መጣልን ሳይሆን መጣብን የሚያሰኝ መልክ እንደዲይዝ ያደርገዋል። ይህን አይነቱን ጭፍግ አቀራረብ እና አተያይም "dystopia"[9] ያሰኘዋል።

በመጨረሻም የ"ዳዊት" ማንነት የፈጣሪውን ሁሉን አወቅነት ገትቶ የማወቅን ሚና ከፈጣሪው ፕሮፌሰር ወስዷል። መጀመሪያ ላይ ህክምው ሲደረግ "ስብአዊነት" የሚል ሽፋን እንደተሰጠው ይታወሳል። ለሰው ልጆች ከፍ ያለ ግምት መስጠት የሰውን ልጆች የጤና ችግሮች በመቅረፍ የተሻለ ግምት በመስጠት… ላይ ነው (ገጽ 238) በኋላም "ሳልቀደም የዝናና ክብር ባለቤት ባደረኩት ሩጫ…" (ገጽ 258) የሚለው አባባል ስምን በምድር ተክሎ የማለፍ ፍላጎት ወደ ባቢሎን ዘመን[10] ተመልሰን ነባሩን ሚት እንድናስታውስ ያደርገናል። ባቢሎናውያን ሰማይ ለማድረስ የገነቡት ግንቡን የውስጥ መሻት እና የደረሰባቸው ቅጣት ከፕሮፌሰሩ ምኞት እና ሳይንሳዊ ውጤት ያመጣው መዘዝ በትይዩ የሚቀመጡ ይመስለኛል።

ፕሮፌሰሩ የአስተሳሰብ ለውጥ የመጣውና ስህተታቸው የታረመው ደግሞ በዳዊት ዕውቀት ተመዝኖ ነው። ስለዚህ ሳንድራ/ቲናን "ቲና ነች/አካል ነች" ያለው በግልባጩ ነበር። መፀፀታቸውና መማረራቸው ዘመናቸውን የመሩበት ዕውቀት እና የእውቀት ስርዓት ሁሉ ስህተት እንደነበርም ማሳያ ነው። በመሆኑም ወደ አዕምሯቸው ይመለሳሉ፤ የእውቀት መሰረታቸውም ይቀየራል። ሰው ቁስ ሳይሆን አዕምሮ ነው ይላሉ። ለዚህ አዕምሮ ለሆነው ሰውም እስከመጨረሻ ይሟገቱለታል። አንተማ "አንተ ነህ" ከማለት አልፎ የሳንድራ/ቲናን ጉዳይ የህግ ወይም የእናቷ ጉዳይ አድርገው አገራቸውን ትተው ዳግም ሊታደጉት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ። የዳዊትን የተጎዳ ሳምባ ሊያስቀይሩለት ይሯሯጣሉ። አንድያ ልጃቸው በማፊያዎች ታግታ ተደውሎ ሲነገራቸው መርዶውን በሰሙበት ቅጽበት ከሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር መልዕክት ይደርሳቸዋል። ይህ መልዕክት መርዶው የፈጠረውን ስሜት እኩል መክፈል ችሏል። "የምትፈልገው ተገኝቶልሃል' ሲባሉ አንድ እፎይታ በስተመጨረሻ" እንዳገኙም በልቦለዱ

---

[9]"It 'presents human life in terms of largely unrelieved bondage. Its settings feature prisons, madhouses, lynching mobs, and places of execution'" /Coupe 177/.

[10] ዘፍጥረት 11፥4 "ለስማችን መጠሪያ እንዲሆነን በምድር ላይ እንዳንበተን፣ ኑ ከተማ እና ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለራሳችን እንስራ አሉ"ይላል። ውጤቱ ደግሞ የልባቸውን መሻት ማጣት ነው - መበተን ሆነባቸው።

ተመልክቷል (ገጽ 289)። ከመርዶው እኩል እፎይታውን የፈጠረው ደግሞ የዳዊት ሳንባ መገኘት ነው። ዳዊት እንዳይሞት ሲታገሉ አንድያ ልጃቸው የመስዋት በግ ያህል ታልፉ ስትሰጥ እፎይታን ማስተናገድ የሚችል ሰዋዊ ስሜት ሊኖር አይችልም። “አባዬ ሊገድሉኝ እያስጨነቁኝ …”(298) ስትላቸው ከማዳን ይልቅ ስለሌላው የእፎይታ ድምጽ ማሰማት ክርስቶስ በሞት ጣር ላይ “ኤሎሄ፣ ኤሎሄ” ብሎ ከጮኸበት የተማጽንኦ ድምጽና (ማር፣ 34) ከአባቱ ዝምታ ጋር በትይዩ የሚቀመጥ ነው።

እንግዲህ ይህን ሁሉ ዋጋ የተከፈለለት “ዳዊት” በሦስት ማንነት የሚታወቅ አንድ ሰው መሆኑን ስናስብ አስቀድመን ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ነው ብለን ያነሳነውን ሃሳብ ይበልጥ ያጠናክርልናል። “ይህ ሰው ዳዊት ነው? ዓብዱል ነው? ዳንኤል ነው? የተረጋገጠ ነገር የለም” (ገጽ 299)። ለሁሉም ሰው እንቆቅልሽ እንደሆነም ተገልጿል። በተገለጠበት አካል ሳቢያ ዓብዱል ይሉታል። ወደ ቤተሰቦቹ ሲሄድ እና የፕሮፌሰሩን ምስጢር ለመደበቅ “ምስጢር” የሆነበት ስሙም ዳንኤል ነው። ውስጡ ባለው አዕምሮም “ዳዊት ነኝ” ይላል፤ “ነህም” ይሉታል። በሦስት ስም የሚታወቀውና በአንድ አካል የተገለጠው ይህ ማንነት በክርስትና ሃይማኖት ከሚታመንበት የሥላሴ አስተምህሮ ጋር የሚሰምር ይመስለኛል።

## 3.2. *የቢሆን ዓለም*

*የቢሆን ዓለም እንደ ራስ ምታት* ሁሉ ዋነኛው ሳይንሳዊ ርዕስ ጉዳዩ የአዕምሮ ልውውጥ ነው። የአዕምሮ ልውውጡ የተደረገው በትዕግስት ፈረደ እና በአውግስቲን እንዲሁም በትዕግስት እና በፍሎረንስ መካከል ነው። ትዕግስት ለህክምና ትምህርት ነጻ የትምህርት ዕድል አግኝታ ከኢትዮጵያ “ፊሲያ” ወደምትባል ከተማ ትሄዳለች። ፍራንኮ አውግስቲን ደግሞ “ሲሸን” ከተማ ውስጥ የሚገኘው “ዘ ኪለርስ” በሚባል የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪ ቡድን ውስጥ ዋነኛ ቦታ ያለው ሰው ነው። ፍሎረስ የ”ዜነን” ዜግነት ያላት ወጣት ሴት ነች። ታሪኩ ደግሞ እንዲህ ነው።

መስፍንና ትዕግስት በአንድ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ውስጥ አብሮ አደግ ከመሆናቸው በላይ የፍቅር ግንኙነት አላቸው። የፍቅር ግንኙነቱ መስፍን  ከግቢ እንዲባበር ምክንያት ሆኗል። “ኤሮል” ወደምትባል ከተማ ሄዶ በረንዳ ማደር ይጀምራል። ከዚያም ወደ ዋና ከተማዋ ወደ አዲስ አበባ ያመራል። በጫማ ጠራጊነት ከሰራ በኋላ ቆይቶ በሂሳብ ሠራተኛነት ይቀጠራል። ከዓመት ከአራት ወር በኋላ ትዕግስትን ፍለጋ ሲሄድ ወደ ውጭ አገር እንደሄደች ይነገረዋል። ድርጂቱ ትምህርቷን ስታጠናቅቅ ምንም እንኳ ጥሩ ውጤት ባታስመዘግብም ልጅ በመውለዷ ሞራሏን ለመጠበቅ ሲባል ዕድሉን እንዳገኘች ይነገረዋል። ያረገዘችው ከእሱ

እንደነበር፣ “ትዝታ” የምትባል ሴት ልጅ እንደወለደች ጽፋ ከተወችለት ደብዳቤ ያውቃል። ትዝታን፣ ማሳደጊያ በነበሩበት ጊዜ እንደ እናታቸው ያዩአቸው ለነበሩት ለእማማ ዘርፌ ትታ ለሰባት ዓመት ያህል የህክምና ትምህርቷን ለመከታተል እንደሄደች ይረዳል። ከዚያም ልጁን ጠይቆ ወደ ስራው ይመለሳል። በስራው ታታሪ ስለነበር ለትምህርት “ዜነን” ወደምትባል ከተማ ይላካል።

ትምህርቱ አምስት ዓመት የሚወስድ ሲሆን የመድህን አስተዳደር ይሰኛል። በከተማዋ ውስጥ ያለውን የወንጀል አይነት እሱም ከሚያውቃት ኤሮል ጋር በማመዛዘን ዓለምአቀፋዊ ወንጀለኛነትን ለማጥናት ብቸኛ ወደሆነው “ኢንተርፖል ኮሌጅ” ለመግባት ይወስናል። የኮሌጅ ትምህርቱን ሊያጠናቅቅ ሲዳረስም ወንጀለኛነትን ለማጥፋት በሚደረገው ስራ ላይ ለመሳተፍ እርዳታውን ለመደገፍና ግዳጁን ለመወጣት ወደ ሲሸን ይሄዳል። በዚያ የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎችን ይከታተል ስለነበር ማስጠንቀቂያ ይሰጡታል። በመካከል ግጭት ይፈጠርና በተደረገ የመሳሪያ ልውውጥ መስፍን እጁን ይመታል፤ አደገኛ ወንጀለኛ የሆነው አውግስቲንም ክፉኛ ይመታል። መስፍን ህክምናውንም ትምህርቱንም ጨርሶ ወደ አገሩ ሊመለስ ሆነ። በዚህ ወቅት ከትዕግስት ጋር የነበረው የደብዳቤ ልውውጥ ይቋረጣል። ትምህርት ቤቷ ሄዶ ቢጠይቅም “እረፍት ላይ ነች” ይሉታል። የመሄጃ ጊዜው ሲደርስ ደብዳቤ ጽፎላት ወደ አዲስ አበባ ይመለሳል። ትመጣለች በተባለውም ቀን ጠበቃት። ወደ አዲስ አበባ ከገባች በኋላ ግን እንደማታውቀው ትሆናለች። ግራ ይገባዋል፤ ይባስ ብሎም ለመግደል ሁለቴ ትሞክራለች። በፖሊስ ቁጥጥር ስር ትውልና እድሜ ልክ ተፈርዶባትም እስር ቤት ትወርዳለች። ግራ መጋባት ላይ የነበረው መስፍን ተመልሶ ወደ ፊሲያ እስከሄደበት ድረስ ልጃቸውን እየተመላለሰ ይጠይቅ ነበር። ስለ ትዕግስት ሁኔታ “ኒሮ ካርሎቲ” የተባለ ሰው አዲስ አበባ ድረስ ፈልጎት መጥቶ ዶክተር አንጀሎ ፍራንክሊን ለጥብቅ ጉዳይ እንደሚፈልገው እና ስለሁኔታው እንደሚያስረዳው ይነግረዋል። በዚህ መሃል ትዕግስትም ከእስር ቤት አምልጣ ትጠፋለች።

ሁኔታውን ሲያጣራም ኒሮ ካርሎቲ ይዟት ስለሄደ ሌላ አይነት ግንኙነት እንዳላቸው ይጠረጥራል። ከዚያ ወደ ፊሲያ ይሄዳል። በዚያም በሀሰት ዕጽ አዘዋውረሃል በመባል ሰባት ዓመት ተፈርዶበት እስር ቤት ይገባል። ሁለተኛው ዓመት ላይ የኢትዮጵያ ኢንተር ፖል ከሃገሪቱ ጋር ተዓፅፎ ከእስር እንዲወጣና ወደ አገሩ እንዲመለስ ይስማማሉ። መስፍን ከመመለስ ይልቅ የትዕግስትና የኒሮ ካርሎቲን ሁኔታ ለማጣራት ወዲህም የወንጀለኞችን መረብ ለመበጣጠስ የ“ዘኪለርስ” አባል ይሆናል። ከዚያ በወንጀል በሰበሰው ገንዘብም ሃብታም ይሆናል። ስሙን “ሰይድ ኦማር” በማለት የንግድ ድርጅት ከፍቶ መኖሩን ይቀጥላል።

ከአምስት ዓመት በኂላ ወደ አገሩ በቱሪስት ስም ይገባል። ልጁን ሊጠይቅ ሲሄድ እማማ ዘርፌ ኒሮ ካርሎቲ ደብዳቤ እንደተወለት ይነግሩታል። አስፈትቶ ይዟት እንደ ሄደና ስለትዕግስት ማወቅ ያለበት ነገር እንዳለ እሱንም እንደሚጠቅመው ስለገለጸለት መጨረሻውን ለማወቅ ወደ ዜነን ተመልሶ ይሄዳል። ተመልሶ ከ"ዘኪለርስ" ጋር አብሮ መስራቱን ይቀጥላል። ሃላፊነት ተሰጥቶት ስለነበር ለከፍተኛ የስራ ጉብኝት የ"ዘኪለርስ"ን ሚስጢራዊ ዋሻ እንዲጎበኝ ይሆናል። በጉብኝቱ "ዘመናዊ" ግን ዘግናኝ ሳይንሳዊ ውጤቶችን ይመለከታል። ከኒሮ ካርሎቲ ጋር ይተያያሉ። ግንኙነቱ ይፋ እንዲሆን እንዳልፈለገ ስለተረዳም በዘዴ አድራሻውን ትቶለት ይወጣል። ኒሮ ካርሎቲ ግን ሳይደውልለት ብዙ ይቆያል። ትዕግስትን በእሱ በኩል ሊያገኛት እንደማይችል ሲያስብ ቦታውን ለፖሊስ ያጋልጥ እና ሊደመስሳቸው ያቅዳል። ይሳካለትና ያጠፋቸዋል። አንደኛውን ጥያቄ አሳክቶ ለአንዱ ምላሽ አጥቶ ወደ አገሩ ሊመለስ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከኒሮ ካርሎቲ መልዕክት ይደርሰዋል። በደብዳቤው ኒሮ ካርሎቲ ሳይሆን ዶክተር አንጀሎ ፍራንክሊን እንደሚባል በመጥቀስ ስለትዕግስት እውነተኛ ማንነት ይገልጽለታል። ግንኙነታቸው እሱ እንዳሰበው የፍቅር ጉድኝት እንዳልነበረ ይልቁንም የህክምና በደል ያደረሳት እሱንም የጎዳው ሰው በመሆኑ ይቅርታውንም በመሻት ይማጸነዋል። የ"ዘኪለርስ" አባላት በበቀል ስሜት ተነሳስተው ህክምናው እንዳደረገው፣ መንስዔውም መስፍን አውግስቲንን በማቁሰሉ፣ ክትትሉንም ባለማቆሙ የዘረጉትን የማጥመጃ ዘዴ እንደነበር ይዘረዝርለታል። ትዕግስት ፍቅረኛው እንደሆነች መረጃውን ስለደረሳቸው ይይዟታል። በእሷ ለማስፈራራት ክትትሉን እንዲያቆም ያቅዳሉ። ነገር ግን አውግስቲን እንደማይተርፍ የህክምና ባለሙያዎች ሲረጋግጡ መስፍንን ሊበቀሉት ይወስናሉ። ከአውግስቲን የተወሰነ የአዕምሮ ክፍል በትዕግስት ጭንቅላት ውስጥ ያስገባሉ። ይህን ያደረጉት አንደኛ መስፍንን የሚያውቀው አውግስቲን ብቻ በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛ "መስፍንን ማግኘት የሚቻለው በትዕግስት ነው" ብለው በማሰባቸው ነበር።

በመሆኑም መስፍንን የመግደል ዓላማቸውን እውን ለማድረግ ሲሉ የአዕምሮ ቅይይሩን ያደርጋሉ። ስለዚህ ወደ አዲስ አባባ ከገባች በኂላም ልትገድለው ያደረገው ሙከራ በአውግስቲን አዕምሮ በመሆኗ እንደሆነ ይገልጽለታል። ያለ ጥፋቷ መቀጣት ስለሌለባት ከእስር እንድታመልጥ ማድረጉን ያነሳለታል። የፈጠመው ህክምና ኢሰብአዊ ድርጊት በመሆኑ በመጸጸቱ የተሻለ ነው ያለውን ህክምና ለሁለተኛ ጊዜም እንዳደረገላትና የእሷን የአዕምሮ ክፍል"ሚሞሪ" ቢያጣውም እንኳ የዜነን ዜጋ የሆነቸውን የፍሎረንስን አዕምሮ እንደቀየረለት ቁርጡን ይነግረዋል። ስለዚህ ለአንተም ሆነ ለእሷ የተሻለ ነው ያለውን ህክምና እንዳደረገላትም ይገልጽለታል። የአውግስቲን ጭንቅላት ስለወጣ እንደበፊቱ ልትሸሽም ሆነ ልትገድለው

እንደማትሞክር ይልቁንም እንደምንም ብሎ እንድትቀርበው አድርጎ ዳግም ወደ ፍቅሩ ለመመለስ እንዲጥር ተስፋ ይሰጠዋል። ነገር ግን ከአንድ ዓመት በፊት በመሆኑ አሁን ያለችበትን ማወቅ ሁኔታ ስለማይቻል የዜነንን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲያነጋግር ይጠቁመዋል። በሁኔታው ልቡ ይነካል። ግን ተስፋም ሰንቆ ወደ ሚኒስትሩ ይሄዳል።

ሚኒስትሩ ትዕግስት ያለችበትን ሁኔታ ሁሉ ያጫውተዋል። ፍሎረንስ በመኪና አደጋ ህይወቷን ስታጣ ቤተሰቦቿ አዕምሮውን ለአንድ ሆስፒታል ይሸጡታል። ዶክተሩ አዕምሮውን ከሆስፒታሉ ይገዛና ይገጥምላታል። ህክምናው እንደተጠናቀቀም ትዕግስት ወደ እነ ፍሎረንስ ቤት በቀጥታ ትሄዳለች። "ውጭ"፣ "ከቤቴ አልወጣም" የሚለው ክርክር ሲበረታ ፖሊስ ይጠራሉ። እስር ቤት እንድትቆይ ሲደረግ ዶክተር ፍራንክሊን ስለማንነቷ ለሚኒስትሩ ይገልጽለታል። የደረሰባትን ስነልቦናዊ ቀውስ በመረዳት የዜነን ዜግነት ይሰጧታል። ለቤተሰቡም ሁኔታውን ያስረዱና ወደ ቤታቸው ይዘዋት እንዲሄዱ ያደርጋሉ። ከዚም የፍሎረንስ ሴት ልጅ እንደልጇ በመቁጠር ትወዳታለች፤ በእናትነት ስሜትም ትቀርባታለች። በሁኔታው ባሏ ይደነቃል፤ ስለወደዳትም ሚስቱ ያደርጋታል። በመጨረሻም ወንድ ልጅም ወልዳ የሁለት ልጆች እናት ሆና እየኖረች እንደሆነ ያረዳዋል። መስፍን እንባውን በተስፋ መቁረጥ ያፈሳል። ሳይፈልግ ባካበተው ሃብት አገሩ ሲገባ የሚከፍተውን የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት እያሰበ ሌላ ተስፋ ሰንቆ ወደ አገሩ ይመለሳል።

በልቦለዱ ውስጥ የተነሳው ሳይንሳዊ ጉዳይ የሚያጠነጥነው በማህበራዊ ሂስ ላይ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ የምንገምታቸው ግን በስም የማይታወቁ የሕፃናት ማሳደጊያው ድርጅት ያለበት አገር እና ኤሮል የምትባል ከተማ ከመዲናዋ አዲስ አበባ ጋር በንጽጽር ቀርበዋል። የእነዚህ ከተማዎች ሌላ መልክ የሆኑ የአውሮፓ ከተማዎችም ተነስተዋል። ዜነን፣ ሲቮን፣ ፌሲያ፣ ስዊድን የሚባሉትን ከተማዎች እንገኛለን። "የኤሮል ከተማ በንግድ ትታወቃለች" (ገጽ 53)። ይህ አንድ መልኳ ሲሆን ሌላም ገጽታ አላት። የቡና ቤት፣ የሙዚቃ፣ የሰው ጋጋታ፣ ጩኸት፣ ግርግር የበዛባት ከተማም ናት። የትርምሱ አይነት ዝንቅ ነው። በራቸውን የበረገዱ ሴተኛ አዳሪዎች፣ የበዙ ጠጭዎች፣ ነጣቂዎች፣ የቁም ዘራፊዎች፣ ተደባዳቢዎች፣ ጉልበተኞች፣ በረንዳ አዳሪዎች የበዙባት፣ መንገዱ አንዳንዴ ይጨልማል፣ አንዳንዴ ብርሃን ይሆናል ብቻ ቅጥ የለውም። ቀን ያያት ማታ የማያውቃት ከተማ ነች። "አንዱ ብርድ ልብሱን መንጭቆት ይሮጣል" (ገጽ 54)፤ መስፍን ተኝቶ እያለ አንዷ ትመጣና ፣ "እየለቀሙ አሳርፈውን ነበር፤ ይሄ ደግሞ የማን ነው?" ትላለች (ገጽ 55)። ልብሱን ለመሸጥ

ወደ ገበያው ሲገባ ሻንጣውን ከፊት ሲያደርግ በገገርነት ስም ከበው በቁሙ ይዘርፉታል፣ የቀረውንም እነሱ በፈለጉት ዋጋ ይገዙታል፤ አስፈራርተው ይወስዱበታል (ገጽ 57) ።

የከተማዋ ሌላ መለዮ እሴቱ የተደበላለቀበት ኗሪ መበርከቱ ነው። የማያሳፍረው ያሳፍረዋልው፤ የሚያሳፍረው አያሳፍረውም። በእንዲህ አይነት ማህበራዊ ትርምስ ውስጥ ያለችው ከተማ በንግድ ታዋቂ መሆኗን ይዘን ወደ ሌላዋ የምትታወቅ ከተማ እናምራ- አዲስ አበባ። አዲስ አበባ ከኤሮል በህንጻ፣ በመንገድ፣ በኢንዱስትሪ ትልቃለች። በአኗኗርና በባህል ብዙ አይለያዩም (ገጽ 65)። የአውሮፓዋ ዜነን፣ ዘመናዊነት፣ ጽዳቷ፣ የህዝቡ የኑሮ ደረጃ፣ በቴክኖሎጂ ተደግፈው ለሰው አገልግሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶች ብዛትና አይነት ግሩም የተባለላት ከተማ ነች። የኢንዱስትሪውና የፋብሪካው ጭስ፣ የመኪናው ትርምስ፣ የወሮበላው ብዛትም ሌላው መልኳ ነው። “በዓለም ላይ የምትታወቅበት ሌላው ነገር የወሮበሎች ብዛት ወደር አይገኝለትም” (ገጽ 83) ። የታጠቁና በህቡእ የተደራጁ የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎች፣ ነፍሰ ገዳዮ “ዝኪለርስ” የተሰኘው ቡድንም የሚገኘው በዚህች ከተማ ነው። እነዚህ የወንጀል ቡድኖች ባለስልጣኖችን፣ ፖሊሶችን፣ ዳኞችን፣ ምሁራንን፣…በጥቅም ስለያዟቸው “ተበደልኩ” ብሎ የሚናገር ቢኖር አይሰማም፤ ፍትህ አያገኝም። የሀሰት ገንዘብ እያተሙ ስሚያሰራጩ የፈለጉትን እንዲያደርጉ አቅም ሆኗቸዋል።

በዚህ የተነሳም ከተማዋ የሚኖረው ህዝብ በሰላም ወጥቶ የመመለስ ዋስትና የላቸውም ። የዚህችን ከተማ ማህበረሰባዊ ዝቅጠት ካልተቆጣጠሩት ዜነንን እንደምትሆን ገልጿል (ገጽ 85)። ቁጥጥሩ የኢንዱስትሪ፣ የመንገድ እድገቱን፣…እንዳልሆነ ስናስተውል ጉዳዩ ማህበራዊ እሴቱ እንዳሳሰበው እንገነዘባለን። ኤሮልና አዲስ አበባም በአኗኗር፣ በባህል፣…ብዙ እንደማይለያዩ ከላይ የተነሳውን ልብ ካልንም ይኽ ወዮታ ለአዲስ አበባም ይሰራል። ተስፋ የማይታይባቸው ሰብአዊ ክብር የነጠፈባቸውን ከተሞች ለመግለጽ ባልታወቁ የከተማ ስም “ኤሮል” እና “ዜነን” ተብለው ተሰይመዋል። ይህን ዓለማቀፋዊ የወንጀል ስጋት ለመከላከል “የመድህን አስተዳደር” የሚባል ትምህርት ሊማር የሄደው መስፍን የወንጀል ጥናት ለመማር ይወስናል ።

በዚህች ሰብአዊ እሴቶች በወረዱባት ከተማ ሳይንስ ከተፈጠረበት ዓላማ ውጭ ውሏል። የአዕምሮ ልውውጥ የሚደረግበት ስፍራ ትልቅ ቋጥኝ ስር ባለ የመሬት ውስጥ ከተማ ነው። ዋሻው ውስጥ ለውስጥ የመብራት ውጋጋን ያለው በዘመናዊነቱ አስገራሚ የሆነ ከተማ ነው። በዋናነት የተለያየ ተግባር ያላቸው ሶስት ክፍሎች አሉት። አንዱ አዳራሹ ነው። በዘመናዊ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ በልዩ ልዩ ኮምፒዩተሮች፣ በሮቦቶች፣ ወ.ዘ.ተ. የተሞላ ቀዶ ጥገና የሚደረግበት ሆስፒታል ይዟል። በዚሁ ክፍል የተለያዩ የሰውነት አካላት ይመረቱበታል።

“ማምረት” ሲባልም ጤነኛ ሰዎችን አታለው፣ አስገድደው፣ “የትምህርት ዕድል እንሰጣለን” በማለት ከተለያዩ አገራት በማስመጣት ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍላቸውን እየበለቱ ያወጣሉ። የሚፈለገውን አካል ካወጡም በኂላ ሌላው አካላቸውም ይመራመሩበታል። ሁለተኛው ክፍል የኬሚካሎች ሙከራ ክፍል ነው። የተለያዩ አካሎች ልዩ ልዩ መልክ እንዲይዙ ይደረግበታል። ሆድ ተከፍቶ ይታያል። ከአንገት በላይ ያለ የሰውነት ክፍል እንዲያብጥ ከወገብ በታች ያለው ደግሞ እንዳለ እንዲሆን ተትቷል። የደረቀ ሬሳ በመሳሪያ እንዲንቀሳቀስ ይደረግበታል። ሦስተኛው ክፍል የአዕምሮ ቀዶ ህክምና ክፍል ነው። የትዕግስት ጭንቅላት የተቀያየረውም በዚህ ክፍል ነው። የሰው ዋጋ በዚህ ቡድን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ሁሉ የሸቀጥ ያህል ነው። “ዘኪለርስ” “ለስኮላርሽፕ” ብለው እስከ አምስት ሽህ ዶላር ዋጋ ከፍለው የሚያስመጧቸውን ሰዎች ብልት በታትነው ከአንድ መቶ ሃምሳ ሽህ እስከ ሁለት መቶ ሽህ ዶላር በሚያወጣ ገንዘብ ይሸጡታል። ድርጊቱን የገንዘብ ፍቅር አናታቸው ላይ የወጣባቸው የተወሰኑ ቡድኖች አመለካከት ነው ብለን እንዳናልፈው የፍሎረንስ ቤተሰቦች ያደረጉትን ማስታወስ በቂ ነው። አዕምሮዋን ተገደው ሳይሆን ፈልገው መሸጣቸው (ገጽ 278) ችግሩ አገራዊ ያስብለዋል። አልፎ ተርፎም ከሰለጠኑ አገሮች ወደ ሌሎች አገሮች እንዲህ አይነቱ ተግባር እንዳይዛመት ስጋት ይፈጠራል። ወደ ሆስፒታል ለህክምና የሄደ ሁሉ አካሉ እንደማይወሰድበት ማረጋገጫ አያገኝም። በዚህ ሁሉ የሰው ልጅ ከቁስ ቀጥሎ ሁለተኛ ስፍራ እንዳለው እንመለከታለን።

ለዚህ ሁሉ ማህበራዊ ቀውስ መፈጠር መንስዔው ደግሞ የቁሳዊ ፍላጎት አለመሟላት ነው። ዶክተር ፍርንክሊን ወደ እንደዚህ አይነት ተግባር እንዲገባ ከገፋፉት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው ተፈጥሮ እና ማህበራዊ አካባቢው ነው። በአገሪቱ በተከሰተው ወረርሽኝ ገንዘብ ካላቸው ሃብታሞች እና እንደ እሱ በዕድል ከተረፉት ጥቂቶች ውስጥ ብዙዎችን ሞት ጠራርጓቸዋል። ሞትም ለሃብታሞች ወግኖ ደሃዎችን ወስዷል። አገሪቷም ዜጎቿን እኩል አትመለከትም። ብር ያላቸው የጥቂቶች ነች። ምሬቱ በዚህ አያቆምም። ዶክተር ፍራንክሊን በብዙ ውጣውረድ ባጠናቀቀው ትምህርቱ የሚያገኘው ክፍያ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚበቃ አልነበረም። እንደ ስራው ስለማይከፈለው አምራችነቱ ተዳከመ እናም ተሰደደ። ከዜነን ወደ ፊሲያ ሄደ። የተሻለ ክፍያ ስላቀረቡለት ለ”ዘኪለርስ” ተቀጠረ። እንዳሰበውም ገንዘብ አገኘ፤ ነገር ግን ያሰበውን ደስታ ሊያገኝ አልቻለም።

በልቦለዱ ውስጥ ሰው ስነ ህይወታዊ አካል ነው። በትዕግስት አካል ውስጥ ሦስት አዕምሮ ቢቀየርም ማንነቷ አይለወጥም። ምንን እንኳ እንደ ተለያዩ ሦስት ሰዎች በተለያየ መንገድ

እያሰበች እና ሃሳቧን እየገለጸች እንደነበር ብንረዳም ያችው ትዕግስት ነች። ስለዚህ ሰው ማለት ረቂቁ ሰብዕናው ወይም አስተሳሰቡ ሳይሆን ከውጫዊው ነባራዊ ዓለም ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት አካሉ ነው። በመሆኑም የቁሳካላውያንን አስተሳሰብ እንመለከታለን።

ከዚህ በተጨማሪም ሳይንስ የሰዎችን ኑሮ ለመቀየር ሁነኛ አማራጭ እንደሆነም በተለያየ መንገድ ተገልጿል። ትዕግስት ሃኪም ለመሆን ስታስብ ዓላማዋ ሰዎችን ከስቃይ መገላገል ነው (ገጽ 8)። "የምርምር ውጤቱ ለሰው ልጅ ደህንነት ከመዋሉ ፋንታ ለሰው ልጅ እልቂት መዋል ጀመረ" (ገጽ 264)፤ "የሚያሳዝነው ሳይንስ በወረበሎች እጅ በመግባቱ ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ከማደግ ይልቅ ለሰው ልጅ እልቂት እንዲያድግም መደረጉ ነው" (ገጽ 265) በማለት "ሳይኪያትሪስቱ" ዶክተር ፍራንክሊን የሳይንስን ግብ እና ዓላማ ይገልጻል። የህክምና ሳይንስን የወከሉት የሁለቱ "ሰዎች" አስተሳሰብ የሳይንስን ግብ ያሳያል። በዚህም ሳይንስ የመጨረሻ የችግር መፍቻ ቁልፍ መሳሪያ እና የዕድገት መሰረት ነው። ሳይንሳዊ ምርምር የተደረገበት ቴክኖሎጂ በተገቢው መንገድ እስከዋለ ድረስ ነጻ (neutral) ነው።

በዚህም በልቦለዱ ለተፈጠረው ማህበራዊ ቀውስ ተጠያቂው ከዓላማው ውጭ ያደረጉት ሰዎች "አስተሳሰብ" እንጅ ሳይንስ አይደለም። የተኮነነው አስተሳሰብ የተለጠጠ ፍላጎት ሲሆን መነሻውም የሃብት መዘውሩ በጥቂት ቡድኖች ቁጥጥር ስር በመውደቁ ነው። ይህ አስተሳሰብ በኤሮልም ሆነ በዜነን እና በተጠቀሱት ከተሞች ላይ ተስተውሏል። ኤሮል በንግድ እየታወቀች የህዝቡ ኑሮ (በገጽ 59) እንደተመለከተው አይመጣጠንም። መሰረታዊ ፍላጎቶች አይሟሉም፤ ዜጎች ከትንንሽ ከተሞች ወደ ትልልቅ ከተሞች ይሰደዳሉ። መስፍን የተጋነነውን የሐረር ጥርስ መፋቂያ ማስታወቂያ ሲተች (በገጽ 58) የሚበላው ለሌለው ሰው መፋቂያ የቅንጦት ዕቃ መሆኑን ሲያመለክት ንግዱ ለመበዝበዣ መሳሪያነት እንደዋለም ይጠቁማል። ዜነንም የዚህ አስተሳሰብ ማጉያ ነች። ዜጎች ከሃብታሞች ጋር በመነጻጸር ሁለተኛ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል። ጥቂቶች ዘርፈውና ወንብደው ዓለምን ለከባድ ስጋት የሚዳርግ ተግባር ሲፈጽሙ (ገጽ 242)፣ ሙያተኞች እንደ ችሎታቸው እና እንደ ስራቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ፍላጎታቸው አይከፈላቸውም። ይባስ ብሎም ይሰደዳሉ።

በአስገራሚ ትዕንግርትነት የተገለጸው የመሬት ስር ዘመናዊ ከተማ እና በገንዘብ ዕጥረት የሚሞተው ዜጋ ዕጣ ፋንታም በትይዩ የሚቀመጡ ናቸው። ዝብርቅርቅ ዓለም- በኤሮል ከተማ ግማሹ ከተማ መብራት በርቶ ግማሹ እንደ ጠፋ፤ ቀን እና ማታ ሁለት ገጽታ እንዳላት ከተማ-ወጥ ነገር የለም። ልቦለዱ የተጠናቀቀው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እርምት በመስጠት ነው። መስፍን ረገርም ዓመት የወሰደበትን እና ፍቅሩን ያሳጣውን አስተሳሰብ

ሲያስተካክል ያቅዳል። ባልተገባ መንገድ የሰበሰበውን ገንዘብ የህጻናት ማሳደጊያ ለመክፈት እና ወላጅ አልባዎችን ለማሰባሰብ ይወስናል። ዕቅዱን በተጨባጭ ስራ ላይ ለማዋልም ወደ አገሩ ይሄዳል። ሃሳቡን ወደ ተግባራዊ ስራ ለመቀየር ይንቀሳቀሳል። ገንዘብ በጥቂቶች እጅ ሲገባ ለመመበዝበዣነት እንደዋለ ሁሉ፣ መሰረታዊ ፍላጎቱ ያልተሟላለት ሰው እንደ ማህበር አባልነቱ ሰብአዊ እሴቱን ለመመለስ በእነዚህ አስተሳሰቦች ላይ ይዘምታል። በብቸኝነት የመወሰን ስልጣኑን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን፣ ሃብቱን፣ በማከፋፈል የሥርዓቱን ማዕከል ሰውን በማድረግ ተደምድሟል።

*የቢሆን ዓለም* የሳይንስ ልቦለድነቱን የሚያስመሰክረው ከርዕሱ ጀምሮ ነው። እንዲህ ቢሆንስ? እንዲያ ባይሆንስ? እየተባለ የተደረገን ሳይንሳዊ ምርምር በተደጋጋሚ ሙከራ በልቦለዱ ውስጥ አሳይቷል፤ “we might indeed see SF as a form of thought experiment, an elaborate ‘*what if?* game, where the consequences of some or other novum are worked through” (Roberts 9). በተጨማሪም የሳይንስ ልቦለድ ገጽታዎች ተብለው የተመለከቱትን ሳይንሳዊ ኀልዮትንም በልቦለዱ ውስጥ እናገኛለን።

ነገር ግን በልቦለዱ ውስጥ ሳይንሳዊ የተባለው ጉዳይ እና ከጉዳዩ የሚመነጩ ክንውኖች በልቦለዱ ለተመሰረተው ተጠይቅ ይገዛሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ በሁለት ሃሳቦች ላይ መመዘን ያለበት ይመስለኛል። አንደኛው በትዕግስት ላይ የአዕምሮ ቅይይሩ ከተደረገ በኋላ የተፈጥሯዊና የባህል ልዩነት ያላቸውን የሁለት ሰዎች ስብዕና ተላብሳለች። በአውግስቲን አዕምሮ አማካይነት ወንድ እና ነፍሰ ገዳይ፣ በፍሎረስ አዕምሮም ሴት እና አፍቃሪ ሆናለች።

ነገር ግን መስፍን ወደ አገሩ ሲመጣ ሲል ለጻፈላት ተደጋጋሚ ደብዳቤ ምላሽ ባትሰጥም የመመለሻ ቀኗ ደርሶ ወደ አዲስ አበባ ትመጣለች። መስፍን ለጻፈላት ደብዳቤዎች ምላሽ ባትሰጥም እንዴት አንብባ ተረዳች? ፍርድ ቤት በቀረበችበት ጊዜም በአማርኛ ምላሽ እንዴት ሰጠች? የሚሉት ጥያቄዎች የግድ ይነሳሉ። ለምን መግደል እንደፈለገች ስትጠየቅ በትዕቢት “መግደል ስላስፈለገኝ” የሚል ምላሽ ሰጥታለች (ገጽ 144)። በምን ቋንቋ? ለሚለው ጥያቄ ግን መልስ አናገኝም። በአውግስቲን አዕምሮ ሆና በአማርኛ የተጻፈን መልዕክት ልትረዳም ሆነ በፍርድ ሂደቱ ልትከራከር አትችልም ወይም አስተርጓሚ አብሯት ነበር አልተባለም። እንዲህ አይነት ልዩነቶችን ባለማየቱ መስፍን እንኳ አይጠራጠራትም። በተጨማሪም ለኢትዮጵያ እንግዳ የሆነን የአውግስቲንን አዕምሮ ይዛ የባህል ወይም የአካባቢ እንግዳነት ሳይፈጠርባት የማቋረጫ መንገዶችን በመለየት ያለማንም አጋዥነት እና መሪነት ቀጥ ብላ ትሄዳለች (ገጽ 130)።

ቋንቋ፣ ዕውቀትን የሚጠይቅ አዕምሯዊ ተግባር ባህልም የዚህ መግለጫ ነው። ስለዚህ በየትኛው አዕምሮ ነው ትዕግስት በአማርኛ ደብዳቤ የምታነበው? እንዲሁም በአማርኛ የምትናገረው? ባህሉንስ አውቃ ያለ እንግዳነት በሰው አገር የምትንቀሳቀሰው እንዴት ነው? ለእንዲህ አይነት የተጠይቅ ጉዳዮች ልቦለዱ መልስ የለውም። እንዲሁም ተደጋጋሚ የመግደል ሙከራ የማድረጓን ያህል ለመጀመሪያ ጊዜ መስፍን አግኝቷት ሰላም ሊላት ሲጠጋ እሪታዋን ታቀልጠዋለች። እንደ ነፍሰ ገዳዩ አውግስቲን /ወንድ የጉልበት ስራዎችን ትሰራለች፤ ለመግደልም ትምክራለች። እንደ "ሴት"ም በመጮህ ራሷን ትከላከላች። ወንድም ሴትም ነች እንዳንል ድርጊቱን የምትፈጽመው የወንድ በነበረ አዕምሮ ሆና ነው።

ፍሎረንስን ስትሆን ደግሞ ያለምንም ልዩነት ትንሽ እንኳ ክፍተት ሳያስቀርላት ፍጹም እናት እና የዜናን ቋንቋ የምትናገር አውሮፓዊ ትሆናለች። አስተሳሰቧ በሁለት የተለያዩ ፆታዎች ማንነት ላይ ሲያርፍ ወጥ ድርጊቶች አይታዩም። እንዲሁም የድርጊት ተለዋዋጩነቱ ለምን እንደተከሰተ ልቦለዱ መልስ አይሰጥም።

የአውግስቲን ጭንቅላት ወደ ትዕግስት እንዲገባ ሲታቀድ ዓላማ የተደረገው አውግስቲን መስፍንን ስለሚያውቀው አካሉ ቢሞትም በአዕምሮው አማካይነት እየተከታተለ እንዲያጠቃው ነበር፤ ነገር ግን ትዕግስት አዲስ አበባ ስትገባ መስፍንን ብታየውም እንደማታውቀው አልፋው ትሄዳለች። በተቃራኒው "ትዕግስት" ብሎ ሲጠራት ድንግጥ ብላ ትቆማለች። ትዕግስት የሚለው ስም እኮ ለአውግስቲን አዕምሮ ሩቅ ነው። ስለዚህ ሁለቱ ጉዳዮች ተምታተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የሙያዎች ድንበር አልተለየም። የአዕምሮ ህክምና (neurology) ስነ አካላዊ ህክምና ነው፤ ሳይኪያትሪ (psychiatry) ደግሞ ስነልቦናዊ ህክምና ሆኖ እያለ በልቦለዱ ውስጥ አንድ ሆኖ ቀርቧል። ዶክተር ፍራንክሊን የሰለጠነው በሳይኪያትሪ እንደሆነ ተመልክቷል (262)። ነገር ግን የአዕምሮ ቅይይር ህክምና የሚያደርገው ደግሞ እሱ ነው። ይህ ደግሞ የሚያሳየው የሳይንሳዊ ዕውቀቱ ክፍተት የሙያ መስኮችን እንኳ ለይቶ እስካለማወቅ የሚዘልቅ መሆኑን ነው። እንዲህ አይነት ክፍተቶች ደግሞ ምርምር ሳያደርጉ ወደ ስራ ለመግባቱ ማሳያ ሲሆን የተጠየቅ ችግር እንዳለባቸው ማመልከትም የሙከራውን ደረጃ ማመልከትም ነው።

## 3.3. *የሳይንስ ራዕይ*

የሳይንስ ራዕይ በሁለት ተጻራሪ ቡድኖች መካከል በተደረገ ትግል በአንደኛው ቡድን አሸናፊነት የተጠናነቀቀን ታሪክ የያዘ ልቦለድ ነው። ትግሉ ሳይንስን በመደገፍ እና በመቃወም የተመራ ሲሆን ዋነኛ ጉዳዩም የዓለም ጥፋት ነው። ባለታሪኮቹ አቶ በልሁ ናደው፣ ታናሽ ወንድማቸው አቶ ተስፋሁን፣ ልጃቸው ኤልያስ እና ደጋፊዎቻቸው በአንድ ወገን ለሳይንስ ወግነው የቆሙ እና በኋላም ያሸነፉት ቡድኖች ናቸው። በቲሲንቲ ሮማና የሚመራው እና በአቶ ጌታ ብቻ አንበርብሬና በደብተራ ዝማሙ የሚደገፈው ደግሞ የማታ ማታ ትግሉን በሽንፈት የደመደመ ጸረ-ሳይንስ ቡድን ነው። የትግሉ ጀማሪ አቶ በልሁ ናደው አርበኛ ናቸው። ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋር ባደረገችው የማይጨው ጦርነት ተሳትፈው ድል ተቀዳጅተዋል። ጣሊያን ከ1928-33 ኢትዮጵያ በወረረችበት ጊዜ ሁሉ ይቆጩ ነበር። የቁጭታቸው መንስዔም ሽንፈቱ የመጣው ጀግንነት ጠፍቶ ሳይሆን በሳይንስ ባለመግፋታችን ነው ብለው ያምናሉ። እኛ በእግር እነሱ በሰማይ መዋጋታቸው ተሸናፊ አድርጎናል! በሚል የአርበኝነት ስሜት ይብከነከናሉ። ስለዚህም አብዝተው ይቆጫሉ። ሌላውን ለማጥቃት ሳይሆን ራስን ከጉልበተኛ ለመከላከል ሳይንስ ወሳኝነት አለው ይላሉ።

በአንጻሩ ከጣሊያን መንግስት ጋር ተስማምተው የሚኖሩት እንደ አቶ ጌታ ብቻ ያሉ ባንዳዎች ደግሞ ለእነ ሮማና አድረው ሎሌ ሆነው ሃሳባቸውን እያገለገሉ ይኖራሉ። ሮማና ደግሞ በፍጹም ንቀት ሰብአዊ ክብር ሳይሰጥ አቶ ጌታብቻን ይገዛቸው ነበር። አቶ በልሁ ስራ አስቀጥረኝ በሚል ሰበብ አብሮ አደግ ጓደኛቸውን /ጌታብቻን/ ወደ ሮማና እንዲወስዷቸው ይጠይቃሉ–ይወስዷቸዋል። ሲደርሱ ግን ሮማና ጌታብቻን በጽይፍታ "ባሪያ" ብሎ ሲሰድባቸው እና በጥፊ ሲመታቸው ሲመለከቱ በድንጋይ ይቀመስልሀ ይሉታል። ወድቆ የደም አበላ እንደዋጠው ሽጉጡን ላጥ አድርገው ይወጣሉ። እምቢ ለጠላት ብለው ዱር ካሉት አርበኞች ጋር ይቀላቀላሉ። ከአራት ዓመት በኋላም ጣሊያን ተሸንፎ አርበኛው ወደ ነጻ አገሩ ይመለሳል። አቶ በልሁም ግራዝማች ተብለው የምክትል ወረዳ ገገር ፣ አቶ ጌታብቻ ደግሞ የፈረንጅ አፍ ያውቃሉ ተብሎ ፊታውራሪ ተብለው ከፍተኛ ሹመት ተሰጣቸው። የጌታ ብቻ ሹመት ረገርም እጅ ለነበረው ለሮማና ተመቸው። በጥቅማጥቅም በመደለል ዳግም ተመልሶ የአቶ ጌታብቻን ቤት ቤቱ አድርጎ ተቀመጠ። ከዚያም ጠላቱን አቶ በልሁን አላሰራ ይላል። አቶ በልሁም ትግሉን መቋቋም ሲያቅታቸው የመንግስት ስራቸውን ያውላችሁ ብለው <u>ዓለም ገና</u> ወዳለው የአባታቸው እርሻ ይመለሳሉ።

ወንድማቸው አቶ ተስፋሁን ፓሪስ ትምህርቱን ተከታትሎ የጨረሰ ሲሆን የአገሩ ጥቃት ቆጭቶት አርበኛውን ተቀላቅሎ በሌላ ግንባር ተሰልፎ ተዋግቷል። ከድል በኋላም የሚያሰራ ቢሮክራሲ ባይኖርም ወደ አገሩ ተመልሶ የአንድ ማተሚያ ቤት ምክትል ዳይሬክተር ሆኖ መስራት ጀምሯል፤ ነገር ግን አቶ በልሁ፣ "ለምን እንደ እኔ ሹመቱን እርግፍ አድርገህ አትተውላቸውም!" ሲሉት ይልቅ ልጅህን ኤልያስን ስጠኝ ላስተምረው ይላቸዋል (ገጽ 26) ። አምጥቶም ያስተምረዋል። ጎበዝ ተማሪ ስለነበር ለትምህርት ለንደን ይላካል። በኑክሌር ፊዚክስ ትምህርት ይመረቃል። በዚህ ወቅት አቶ በልሁ ይሞታሉ።

አቶ ተስፋሁን በፍፁም የአገር ፍቅር ስራውን ቢሰራም ለመልቀቅ ይወስናል። በባለቤቱ ድንቅነሽ ምክር "የመንግስት"ን ስራ በመልቀቅ "የሳይንስ ክበብ" በሚል ስያሜ "የአገራችንን የሳይንስ ዕድገት ሊያፋጥን ይችላል ብሎ" ያመነበትን ማዕከል ያቋቁማል (ገጽ 30)። የክበቡን መመስረት ተከትሎ ኤልያስን ጨምሮ ሌሎች ኢትዮጵያዊ ምሁሮች ወደ አገራቸው ይገባሉ። እነሱም ፋሌክ አውሮፕላን አብራሪ፣ ኢዮር የህክምና ባለሙያ፣ እዝራ መድሃኒት ቀማሚ፣ ሄኖክ የማዕድን ተመራማሪ፣ ማትያስ የእንስሳት እና የአዝዕርት ልማት ምሁር፣ ራማ እና አርኣያ /ሙያቸው ያልተጠቀሰ/ እንዲሁም ሌሎች ይገኙበታል። ከዚያም በርካታ ሳይንሳዊ ምርምሮችን አድርገው ለህብረተሰቡ የሚጠቅሙ ግኝቶችን ያፈልቃሉ። እንዳሰቡት ግን ብዙ ሳይገፉ፣ ራዕያቸውን ዕውን ሳያደርጉ በእነ ሮማኖ አማካይነት የሳይንስ ክበቡ እንዲፈርስ ይሆንና ቦታው "ለቁልቋል ሆቴል" ማስፋፊያ ይሰጣል። ለሳይንስ ያልሆነች ዓለም ለእኛም አትሆንም ብለው ብዙዎቹ ይሰዳዳሉ። ተስፋሁን ግን ባላገር ወዳሉት ዘመዶቹ ይመለሳል። ሮማኖ ሊያጠፉቸው ይፈልግ ስለነበር በመሸሻቸው ይናደዳል። የመጀመሪያውን እርምጃ ተስፋሁንን ከአገር ቤት ሲመለስ ጠብቆ በመኪና ገጭቶ ይገድለዋል። ከዚያም እነ ኤልያስያን ማሳደዱን ይቀጥላል። የሰሃራ በረሃን በርሃማነት ለማወገድ ያደረጉትን ችግር ፈች ምርምር ሲሰማ ይበልጥ ይናደዳል። በርካታ ሚሳየሎችን ይተኩሳል፤ ፈንጅዎችን ያፈነዳል፤ ድማሚቶችን ይተኩሳል። ይህን ሃይል መሬት መቋቋም ያቅታት እና ትሰደዳለች። እነ ኤልያስም የሚኖሩበት ዓለም በማጣታቸው ዳግም ወደ ሌላ ዓለም ይሰደዳሉ። በመንኮራኮርም ይመጥቃሉ። በሄዱበት ዓለም አዳዲስ ሳይንሳዊ ዕውቀት ይዘው ወደ ምድራቸው ለመመለስ የሦስት ሸውን ዓመት ጉዞ በእንቅልፍ፣ በህልም እና በራዕይ መንፈሳቸውን አንቅተው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ።

*የሳይንስ ራዕይ*፣ በርካታ ሳይንሳዊ ሃሳቦች አንስቷል። የተነሱት ሳይንሳዊ ሃሳቦች የቀረቡት በህልም ወይም በራዕይ መልክ ነው። ከመጽሐፉ ርዕስ ጀምሮ በጽሑፉ ክፍል ውስጥ እናገኛቸዋለን። ማሳያ አንድ፣ የሳይንስ ክበቡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይፍረስ ሲባል ኤልያስ አባላቱ ሰብስቦ እንዲህ ይላቸዋል። "አገራችንን የሳይንስ አገር ለማስኘት ያሳየነው ጥረት አያሌ ነው። ነገርግን ጥረታችን *ከህልም ወይም ከራዕይ የተሻለ ሆኖ አልተገኘም።* እስከ መቼስ በህልም ዓለም ውስጥ እንኖራለን? እስከመቼስ በሳይንስ ራዕይ ስንባክን እንገኛለን?"[*አጽንኦቱ ከራሴ]* (ገጽ 102) ። እነዚህን ሁለት ሃሳቦች በመያዝ ለምን ህልም እንደነበሩ ደግሞ እንመልከት። እርግጥ ነው ተኝተዋል የሚልም ሆነ "ይሕ ህልሜ ነበር" የሚል ሃሳብ ቃል ባናገኝም እያለመ እንደነበር ከታሪኩ መረዳት ይቻላል። አንደኛ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ሲሰሩ አናያቸውም፤ የምርምር ውጤቱ ተጠቃሚዎችን ምስክርነትም አንሰማም። ከዚህ ይልቅ "ድምፀ-አቅርንት" የተባለው መጽሔት "እንዲህ ሆነ" እያለ እያተመ ዜናውን ከማሰራጨቱ ውጭ መረጃውን ከሳይንቲስቶቹ አንሰማም።

ማሳያ ሁለት፣ እነ ፋሌክ ወደ ሌላው ዓለም ሄደው ሲጎበኙ ከተማዋን ሲያስተዳድር በራዕይ ወለል ብሎ ይታየዋል (ገጽ 149) ። ቀይ ህንዶችም ይታዩታል። እንደገናም ድንገት ያልታወቀ ፍጥረት አጠገባቸው ሲደርስ ቀይ ህንድ[11] ነው ብለው አሰቡ (ገጽ 161) ። የቀይ ህንዶች የአፈጣጠር ታሪክ የሚቱ መሰረት ደግሞ ህልም ነው።

ማሳያ ሦስት፣ እንዲሁም በታሪኩ መጨረሻ ወደ ምድር ሲመለሱ ከረዥም ጊዜ በኋላ በመሆኑ ምድርም እንዳትረሳው ስጋታቸውን እንዲህ ይገልጻሉ።

> ናፍቆትም ስለጸናባቸው ጊዜውን በእንቅልፍ ሊያሳልፉት ፈለጉ። ይህን ሶስት ሽህ ዘመን ቢያንቀላፉትም መንፈሳቸው ከህልም ከራዕይ አልተለየም። የቴክኖሎጂ ህልም ያልሙ ነበር። የሳይንስ ቪገርን ይከሰትላቸው ነበር። …እነሱ ቢያንቀላፉ ልባቸው የነቃ በመሆኑ የሳይንስ ራዕይ ይታያቸው ነበር (ገጽ 189) ።

ምንም እንኳ እነዚህ ሦስት ምሳሌዎች እንደ ማሳያ ሆነው ቢመረጡም እንቅልፍ፣ የቁም ቅዠት፣ ህልም እና ራዕይ የሚሉ ቃላት በርካታ ናቸው። እንዲሁም የሃሳብ ቅደም ተከተላቸው አንድ ጊዜ ወደ ፊት እንደገናም ወደ ኋላ እየተመላለሰ ሲቀርብ ይገጥመናል። የቅደም ተከተሉ መዋዠቅ የኢ-ንቁ የአዕምሮ ክፍል ባህሪ ነው። አሌክሳንደር ዌልስ ፍሮይድን በመጥቀስ የሰው

---

[11] The Aborigines of Australia have a myth from northeastern Arnhem Land that recounts how, during the "dreamtime," a brother and two sisters (the Djanggawul) wandered over the earth creating plants, animals, and the ancestors of the Aborigines–the sisters were constantly being impregnated by their brother (Garry 433)

ልጅ በንቁ አዕምሮው በጊዜ፣ በቦታ፣ በባህል፣... ገደብ ምክንያት ሊደርስባቸው የማይችላቸውን የወሲባዊ ፍላጎቶቹ አንጻር የሆኑ ፍላጎቶቹን ለማርካት ህልም፣ የማስተንፈሻ መንገድ እንደሆነ ይገልጻል (ገጽ 33)። በመሆኑም የአቶ በልሁ ከፍተኛ የሆነ የሳይንስ ጥማት ረክቶ፣ ምኞታቸው ተሳክቶ፣ በድል ሲመለሱ በታሪኩ ፍጻሜ እንመለከታለን።

በታሪኩ ውስጥ የተገለጹ ባህርያት ዞረው የሚገጥሙ፣ ሙሉ ክብ የሚሰሩ ናቸው። የአቶ በልሁ ስሜት በታናሽ ወንድማቸው፣ ከዚያም በልጃቸው ዞሮ ወደራሳቸው ይመጣል። ተስፋሁን ሞቶ የህይወት ታሪኩ በተፈጠረው ግርግር ሳይነበብ ይቀራል። ስለ አሟሟቱ በቂ መረጃ ከተሰጠን በኋላ "ታሪኩ ግን ሳይነበብ ቀረ" (ገጽ 122) ። አቶ በልሁ "እንዴት ሞቱ?" ለሚለው በቂ መረጃ አናገኝም። በታሪክ መካከል ኤልያስ የሰራውን ሳይንሳዊ ፎርሙላ ከነገረን በኋላ የአርበኛው የአቶ በልሁ ልጅ እንደሆነ ድንገት ስንቅር አድርጎ ያስታውሰናል። እግረመንገዱንም እሱ ለትምህርት ለንደን እንደሄደ እንደሞቱ ይጠቁመናል። የረሳቸው ይመስላል እናም ድንገት አስታውሶ የሚነግረን ይመስላል።

በአንጻሩ የተስፋሁን መሞት ከተነገረ በኋላ ታሪኩ ሰሃራ በርሃ ላይ ሳይንቲስቶቹ በሰሩት ተራራ ላይ ይጻፋል። ይሁን እንጅ እነ ሮማኖ አሁንም ተራራውን ያፈርሱታል። ነገር ግን ጉዟቸውን አጠናቀው ለመመለስ በሰማይ ላይ በረበቡበት የመጨረሻ የድል ጉዞ ላይ የተስፋሁንን ታሪክ ይጽፉታል ሳይሆን ያሳዩታል። በድል ሲመለሱም የሦስቱም መንፈስ ሰማይ ላይ ይረባል- ሦስቱ ባህርያት ዞረው ይገጥማሉ። የታሪኩ ጅማሬ እና ፍጻሜም የሚያረጋግጠው ይህንኑ እውነታ ነው። አቶ በልሁ እውቀቱ እና ብልሃቱ ነበረን፤ የታጣው መብት ነው (ገጽ 1) ሲሉ ፍለጋው ሰይንሳዊ ነጻነት ለማግኘት እንደሆነ እንገምታለን። እውቀቱ አስቀድሞ የነበረ መሆኑን እንድናረጋግጥ የሳይንስ ክበቡ ሲቋቋም የመጀመሪያዉ የመስክ ምልከታ የአፄ ቴዎድሮስን መድፍ እንዲሁም ጥንታዊ የቴክኖሎጂ ውጥን ስራዎችን ተመልክተው ነበር። በታሪኩ ፍፃሜም ሦስት ሽህ ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰው ይሄዳሉ። ጅማሬው እና ፍጻሜው በትዝታ ዞረው ይገጥማሉ። ማንነታቸውን ወደ ኋላ ማስታወስ ደግሞ አንዱ የሳይንስ ልቦለድ ባህሪ ነው፤ "SF actually enacts a fascination with the past for which 'nostalgia' is the best description" (Roberts 24). ዞሮ መግጠምም ይሁን ክብ መስራቱ የዘለዓለማዊነት ትዕምርት እንዳለው James 227 ጠቁሟል። በልቦለዱ መጨረሻም ባለታሪኮቹ በህልም ከሄዱበት ጉዞ ዘለዓለማዊነትን ይዘው ተመልሰዋል።

ከላይ የሳይንስ ራዕይ ዋነኛ ጉዳይ የዓለም መጥፋት እንደነበር ተመልክተናል። ለዓለም መጥፋት መንስዔ የሚያደርጉት ሚታዊ ተረኮችን ሲሆን አቡቀለምሲሳዊ[12] (apocalyptic) ሚት ተብለው ይታወቃሉ። ስለዚህ በልቦለዱ የቀረቡት ሃሳቦች በአሊጎሪያዊ ቅጥ የቀረቡ መሆናቸው የሰዉ ልጅ ከውድቀት /ከገነት መባረር/ በኋላ የደረሰበትን የሞራል ውድቀት ለማሳየት እንደ ማንጸሪያነት ያገለግላሉ፤ "The allegory is thus a form of communication in a Fallen, post-paradisiacal and ultimately meaningless world" (Sedgwick 26).

አርበኛው አቶ በልሁ በሳይንስ ተበልጣ በተሸነፈች አገር ውድቀት ይቆጫሉ፣ ወደ ስልጣኔ ማን ይምራን? እያሉ ራሳቸውን ይጠይቃሉ (ገጽ 2) ። ታናሽ ወንድማቸው ይቆጨዋል። ልክ እንደ እሳቸው የሽንፈቱን አይነት እና ብዛት ብቻውን ይዘረዝራል (ገጽ 28)፤ ድምጻቸውን ሰምቶ እንበለው ሳይንስ ክበቡን ያቋቁማል። ኤልያስም የሳይንስ ክበቡ ይፍረስ መባሉን ሲሰማ በአርበኝነት ስሜት ይቆጫል። ለፈላጭ ቆራጭ ተላልፋ ለተሰጠችው አገሩ ያዝናል፤ እናም ስደት ይመርጣል (ገጽ 100)። በሶስቱ አካላት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ቁጭት እና የአርበኝትን ስሜት አንድ ነው። ሮማና አቶ በልሁ በመቱት ጊዜ የተሰማውን ስሜት ሁለቱን ሲያይና ሲያስብ በእኩል ደረጃ ይሰማዋል። በፍርድ ቤቱ ክርክር "የተስፋሁን መንፈስ ግትርነት እና የአርበኝነት አስተሳሰብ የአቶ በልሁን ጠባይና ባህርይ ሳያስታውሰው...አልቀረም"። እንዲሁም ሮማና የእነ ኤልያስን መሰደድ ሲሰማ በዋነኛነት ህመም የሚሆንበት ደግሞ የኤልያስ ጉዳይ ነው፤ " ያን ጊዜ አቶ በልሁ በድንጋይ ማሃል ግንባሩን ስለበረቀሰው ነው። አሁን ደግሞ የበልሁ ልጅ ኤልያስ በረቀቀ ስልት ማሃል አናቱን ስለበጠበጠው ነው" ይላል(ገጽ 111) ።

በሶስቱም ውስጥ ያለው የአርበኝነት ስሜት እና ቁጭት ትግል የሚገጥመው ደግሞ አካል ካለው ሰው ጋር አይደለም። ስለዚህ ሶስቱም ይቆጫሉ፤ ጠላታቸውም ሰው ሳይሆን የሚታገሉት ከምቀኝነት ጋር ይሆናል። አቶ በልሁ አገራቸው ነጻ ከሆነች በኋላ ከሮማና የወሰዱትን መሳሪያ ሸጠው ቤት ሊሰሩ ሲያስቡ አንድ ወዳጃቸው ተው! አትሽጡት ብሎ ሲመክራቸው "እኔን እየተከታተለ የሚያጠቃኝ ጠላቴ ምቀኝነት ነው፤ ምቀኝነት ደግሞ ግዙፍ ነገር ባለመሆኑ ጥይት አይመታውም" ሲሉ ይመልሱለታል (ገጽ 20) ። አንድ ብቻ የተባለው ጠላታቸው ከሞቱም በኋላ ተስፋሁን እና ኤልያስን ያሳድዳቸዋል። ምቀኝነት ተስፋሁንን ይገድለዋል (ገጽ 118)። ክትትሉ እስከ ኤልያስ ይዘልቃል። ስለዚህ ምቀኝነት ማንነት ተሰጥቶት፣ የማጥፋት አቅም እንዳለው ተነግሮን ምድርን ሲያጠፋትም በታሪኩ ውስጥ

[12] (ቴዎድሮስ ገብሬ 86)

ይገጥመናል። ምቀኛ ሰዎች ከነፍሳቸው ከምቀኝነት ጋር እስከ ሞት ድረስ አብረው ተቆራኝተው ይቆያሉ። ክበባችንን ምቀኝነት ለማጥፋት ሞክሮ ነበር፤...ምቀኝነት እኛ እንዳናጠፋው እሱ ቀደመን (ገጽ 183) ይላሉ። አሳዳጁ "ምቀኝነት" እንዲሁም ተሰዳጁ "ቁጭት" በእነ ሮማኖ እና በእነ አቶ በልሁ የተወከሉ ባህርያት ናቸው።

እንግዲህ *በሳይንስ ራዕይ* በህልም የቀረበም ቢሆን ጉዳዩ ምን አይነት የሳይንስ ልቦለድ ገጽታዎች ተነስተውበታል? የሚለው ነው። በመሆኑም አንደኛው ለዐይነ ስውራን የዐይን ምትክ መስራት ነው። የምርምር ስራው የተደረገው ተፈጥሮን በማረም ነው። አንደኛ ዐይን ካለው አስፈላጊነት አንጻር አንድ ጊዜ ከፈሰሰ የማይተካ መሆኑ፣ ያለበት ቦታም ፊት ለፊት በመሆኑ በቀላሉ ለአደጋ ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል። በተጨማሪም ብዛቱ ሁለት ብቻ በመሆኑ ከሚታየው ብዙ ነገር አንጻር ውስን ነገሮችን ብቻ እንዲታይ አድርጓል የሚል መነሻ አለው። ስለዚህ ከዐይን ጋር ተመሳሳይ ባህሪ ባለው በፀጉር ይተኩታል። ሁለቱም የቱቦ አይነት ባህሪ ስላላቸው ፈሳሽ አቁረው ይይዛሉ። ልዩነቱ ፀጉር ከአዕምሮ ጋር ተገናኝቶ ምስል የመፍጠር አቅም የለውም። ስለዚህ የቅንድብን ፀጉር መርጠው ከአዕምሮ ጋር እንዲያያዝ ያደርጉታል። ከዚያም የዐይንን ተግባር እንዲወጣ ይደርጋሉ። ፀጉር መተካት የሚችል፣ በቁጥሩም በርካታ ስለሆነ ችግሩን ይፈቱበታል። የዐይን ብርሃን ያጡትን ብቻ ሳይሆን ዐይን ያላቸውም አብዝተው እንዲያስተውሉ ያደርጋሉ።

ሌላው መስማት ለተሳናቸው የጆሮን ድክመት አሁንም በፀጉር አማካይነት ያርማሉ። ፀጉር ከአንቴና ጥበብ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከጆሮ ቅጠል ላይ የሚበቅሉትን ይመርጣሉ። እነዚህን ሁለት ችግሮች በፀጉር አማካይነት ሲፈቱ ሰዎች የተሻለ መስማት እና ማየት ከመቻላቸው ባሻገር ወደ ልዕለ አዕምሮ ይደርሳሉ (ገጽ 46) ። ይህን የልዕለ ባለአዕምሮነት ፍላጎት በሌላኛው ዓለም ውስጥም እናገኘዋለን። በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ የሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮች ምንጫቸው አንድም ፈጠራ አሊያም ምስስሎሽ (analogy) እንደሆነ ካስታወስን የፀጉርን ባህሪ ከዐይንና ከጆሮ ጋር ማመሳሰሉ የዚህ ባህሪው ማሳያ እንደሆነ እንረዳለን።

ሦስተኛው ደግሞ ስነምህዳራዊ (ecological) ተግባር አለው። እንደ ነብር እና አንበሳ ያሉት የዱር አራዊት እንደ ዋልያ እና አውራሪስ ያሉትን ብርቅዬ እንስሳት እየበሉ በተፈጥሮ ሃብት ላይ እያደረሱ ያሉትን ችግር ማረም ነው። ለዚህም መፍትሄዉ ስጋ በል አራዊትን ሳር በል በማድረግ ማልመድ ነው። የስጋ በልም ሆነ ሳር በል እንስሳትን መርጠው አዕምሯቸውን ይከፍቱታል። እንደ ምግብ ፍላጎታቸው አቅርበው እንዲሸታቸው ያደርጋሉ። ምግቡ የተለያየ

ቢሆንም የሚንቀሳቀሰው የአዕምሮ ክፍልም ሆነ ውስጣዊ መዋቅሩ ተመሳሳይ መሆኑን ይረዳሉ። በቀዶ ህክምና አንጎላቸውን ያቀያይሩታል። በሂደቱ እንስሳቱ አራዊት ለመሆን ሲፈጥኑ አራዊቱ ግን እንስሳቱን ለመሆን ዘገዩ። አሁንም ተግባራቸውን በመቀጠል በጥርሳቸው እና ምላሳቸው አካባቢ ያሉትን ዕጢዎች ማስተካከያ ያደርጉላቸዋል። ከዚያም አራዊቱ ሳር በል ይሆናሉ፤ በዚህም በአፈጣጠራቸው ሁሉም ሳር በል ሆነው እንደተፈጠሩ እና በልምድ ወደ ስጋ በልነት እንደተቀሩ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ። የተመረጡት አደገኛ አራዊት ስጋ እንዳይበሉ ዘለዓለማዊ ማዕቀብ ይጣልባቸዋል (ገጽ 50) ። ችግሩም ለዘለዓለም ይፈታል።

አራተኛው ግኝት የምግብ እጥረትን ማስወገድ ነው። መፍትሄውን ከዐባይ ደለል ከሚገኝ አፈር ያዘጋጃሉ። ለአጠቃቀሙ ምቹነት፣ ቀላልነት፣ በሚታከምበት ሁኔታ ላይ ይመራመሩና ከአፈር ድልህ ምግብን ማግኘት እንደሚቻል ያስተዋውቃሉ። ምግቡ በነፃ ስለሚታደል ረሃብተኞች ይጠግባሉ፤ ሃብታም እና ድሃ አይኖርም።

አምስተኛው ግኝት ዓለምን ከጥፋት የሚታደግ ኢትዮጵያዊ ቀመር ነው። ስያሜው የተሰጠው ሳይንሳዊ ቡድኑን በሚመራው  በአቶ በልሁ ልጅ በኤልያስ ስም ነው። “ኤልያሲዝም” ይባላል። ቀመሩ ሌሎች ባለሙያዎች ስለዓለም ፍጻሜ ከሚሰጡት መላምት ጋር በንጽጽር ቀርቧል። አንድ የአስትሮኖሚ ሊቅ ፀሐይ እንዴት እንደምትፈነዳ፣ ሌላው የጠፈር ሳይንቲስት ፀሐይ እንዴት እንደምትከስም፣ ሌላኛው የስነክዋክብት ሳይንስ እና የጠፈር ተመራማሪ ሁለት ፀሐይ በአንድ ሰማይ ላይ ሲከሰቱ ምድር እንደምትጠፋ፤ አራተኛው የጠፈር ተመራማሪ በበኩሉ ምድር ምህዋሯን ቀይራ ከፀሐይ እየራቀች በመሄድ ወደ ጅራታም ኮከብ ምህዋር እንደምትገባ ያትታሉ። የምድር ህልፈት መረጃዎች “ልዩ ልዩ ሳይንስ ነክ ዜናዎች” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፤ነገር ግን ኤልያሲዝም ከእነዚህ መላምቶች የተለየ ሆኖ ቀርቧል። የሳይንስ ክበቡ መጽሔት ያቀረባቸው የምድር ህልፈት መላምቶች መነሻ ተፈጥሯዊ ክስተት እንደሆነ ይጠቁማል (ገጽ 58)። ዜናው ሰው ሰራሽ የሆነውን የምድር ጥፋት መንስዔውን ለማወቅ ኤልያሲዝምን ይመልከቱ ብሎ ጥቁምታ ይሰጣል። ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች መፍትሄ ብለው የቀመሩት “ኤልያሲዝም” የተባለው መላምት ኢትዮጵያዊ መሰረት እንዲይዝ ተደርጓል።

> ምድር በ”አ” ጥልቀት፣ በ”ቡ” ርቀት፣ በ”ጊ” የኑክሌር ክብደት፣ በ”ዳ” የጊዜ ቀመር፣ በ”ሄ” ድግግሞሽ፣ በ”ው“ የነፀብራቅ ፍጥነት፣ በ”ዞ” የሙቀት፣ ትኩሳት አካሏን ስትመታ በሚደርሰው ንዝረትና የምት ሃይል የስበት ኃይሏን ታጣለች። ይህችው ምድር ሙት ወይም በድን ትሆንና ማግኔትነቷን ታጣለች (ገጽ 135)።

እነ ኤልያስ ዓለም እነሮማና ዓለምን በፈንጅ ከማጥፋታቸው በፊት እንዴት ልትጠፋ እንደምትችል መረጃውን ቢያሰራጩም ጆሮ አያገኙም። ምክንያቱም ቀመሩ ኢትዮጵያዊ በሆነ (አቡጊዳሄውዞ) እንጅ አልፋ፣ ኦሜጋ የሚል ባለመሆኑ ነው (ገጽ 136) ። ለኢትዮጵያውያን ዕውቀት ዝቅተኛ ግምት መስጠቱ የእነሮማና ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያንም እንደሆነ በብዙ ክፍል ተጠቁሟል። የሳይንስ ክበቡ እንዲዘጋ ሲወሰን በችሎቱ ላይ ከተገኙት ተችዎች ውስጥ አንደኛው "ሳይንስ እና ቴክኖሎጂን የሚያሳምሩት ፈረንጆች ብቻ ናቸው" (ገጽ 71) በማለት የሰጡት አስተያየት ለራሳቸው የነበራቸውን ዝቅተኛ ግምት ማሳያ ነው። በመሆኑም ማስጠንቀቂያውን ቸል ብለው የኑክሌር ደማሚቶችን፣ የአቶሚክ ጨረሮችንና ፈንጂዎችን፣ የሮኬት አረሮችን እስከ ሚሊዮን ሜጋ ፖንድ በሚደርስ መጠን ምድርን አፈነዷት። ምድር እንደ ሰው ተሰዳ በመሄድ በሌላ ምህዋር ላይ ተሰካች፤በአዲስ ስርዓትም መመራት ጀመረች።

እነ ኤልያስም መጠጊያ አገር፣ ዓለምም ስሌላቸው ዳግም ይሰደዳሉ። ወደ ሌላኛዋ የምድር ገጽ በመንኮራኩራቸው አማካይነት መጥቀው ይሄዳሉ። ስለዚህ የዓለም መጥፋት ሌላ አማራጭ እንዲያማትሩ እና እንዲፈልጉ ይሆናሉ። የሳይንስ ልቦለድ ዓላማው የይቻላል መንፈስ መስነቅ እና አማራጮችን ማሳየት የመሆኑን ያህል ይህንን እውነታ በሳይንስ ራዕይም ይገጥመናል። የተሰደዱባት ዓለም የቀድሞዋ የኤደን ገነት አምሳል፣ የተስፋ ምድር (utopia) ገጽ ነች። በአንጻሩ የተበላሸችውና ይኖሩባት የነበረችው ምድር ጸረ-የተስፋ አገር (dystopia) ማሳያም ነች። በአዲሷ ምድር ከምድር መሸጋገር ብቻ ሳይሆን የማንነት ለውጥም ይመጣል። ለጉዟቸው የተጠቀሙባት መንኮራኩር የኖህ መርከብ ምሳሌ እንደሆነች ተመልክቷል (ገጽ 136) ።

"የሰው ልጅ ክፋት መጨመርን" ተከትሎ እግዜር ሰውን በመፍጠሩ በመፀፀት ምድርን በውሃ ሲያጠፋት ለሚተርፉት ግን መርከብ ተዘጋጅቶ  ስለነበር ጥቂቶች ተረፉ (ዘፍ፣ 6)። እነ ኤልያስ በመንኮራኩሯ/ በመርከቧ ገብተው ይተርፋሉ። ኤልያስ በጥቂቶች ጥፋት ህጻናት ሳይቀሩ በመቀጣታቸው ፈጣሪን ትክክለኛ ፈራጅ አይደለም በማለት ይተቻል። "ሆኖም ደጋጎቹ ሰዎች ከጥፋት እንደሚድኑ እምነት ነበረው" ይላል (ገጽ 141)። በልቦለዱ ታሪክ "ደግ ሰው" ተብሎ የተጠቀሰ ነገር ግን በመንኮራኩሯ/በመርከቧ ያልነበረ አንድ ሰው እናገኛለን። የሳይንስ ክበቡ እንዲፈርስ ሲወሰን በፍርድ ሂደት የሳይንስን አስፈላጊነት ወግነው ሲከራከሩ ከነበሩት ውስጥ የግራ ዳኛው ስማቸው አልተጠቀሰም። ነገር ግን "ደጋጎቹ ሰዎች" ተብለው ተጠርተዋል (ገጽ 96)። ስለዚህ ኤልያስ ከጥፋት እንዲድኑ የሚማልድላቸውም ሆነ እንዳይጠፉ የሚሟገትላቸው እንደ እነዚህ ያሉ የሳይንስ ወዳጅ ለነበሩ ሰዎች ነው። ስለዚህ ሌላው

አስተሳሰብ ሁሉ ሲጠፋ ቀጣይ በምትመጣው መንግስት በህይወት የሚቆዩት የሳይንስ የሆኑት ብቻ ይሆናሉ።

ከዚያም ወዳልታወቀ ዓለም ይደርሳሉ። ወደ ምድሯ ለመድረስ የቀደሙት ፍቅረኛሞቹ ፋሌክ እና ኢዮር ናቸው። እነሱ በአዳምና ሔዋን (ገጽ 148) ፣ ምድሯም በገነት፣ የበቀለው ተክልም በገነት ዛፍ ተመስለዋል (ገጽ 147- 148)። ሜዳው፣ ቁጥቋጦው፣ የመስኩ ልምላሜ፣ የአየሩ መዐዛ፣ ይመስጣል፤ አየሩ ቢተኙበት እንደ አልጋ ይመቻል። አልጋ ደግሞ ውክልናው እረፍትን ሰላምን የሚያሳይ ሲሆን እረፍት አጥታ የተሰደደችውን ምድር እና ህዝቦቿን ያስታውሰናል። የምድሪቱ የገነት አምሳልነት በገጿ ብቻ አልነበረም። የመሬት ውስጥ ውሃ የገነትን ምድር ያጠጣት እንደነበረው የዚህች ምድር መሬት የሚረሰርሰው ከምድር ውስጥ ከሚፈልቅ ውሃ እና ከሰማይ ጠል ነው። ሳይንቲስቱ የእናንተ ምድር የተረገመች ትመስላለች ሲልም ያለ መርገም ያለቸውን ምድር ገጽታም መግለጹ ነው። በዚያ ጭንቀት፣ ርሃብ፣ በላብ መብላት፣ እንዲሁም ዝናብ አይታወቅም።

ሌላው የገነትን ፍሬ የምትመስል ዛፍ እናያለን። ፋሌክ ለመብል የምታስጎመጅ እና ሲይዋት የምታምረውን ፍሬ ለመቁረጥ ሲደፍር የብርሃን ሃይል አሽቀንጥሮ ይጥለዋል። በነባሩ ሚት "ሔዋን ፍሬዋን ቆረጠች" ተብሎ እንደተጻፈ ይታወቃል። እዚህ ላይ ግን የሔዋን አምሳሏ ኢዮር ፋሌክን/ አዳምን ትከለክለዋለች። ምንአልባትም ፍሬውን በመብላቷ የውድቀት መዘዝ ተደርጋ መቆጠሯን ለማረም /ለማስተካከል ሆን ተብሎ "ተው" ባይ ተደርጋለች። የዚህን ታሪክ ጥላ ምድር ላይ በነበረው የሳይንስ ክበብ ላይ እናገኘዋለን። የሳይንስ ክበቡ እንዲቋቋም ሃሳብ በማመንጨት፣ በገንዘብ እና በሃሳብ በመሳተፍ ብሎም በሳይንቲስትነት በማገልገል የሴቶችን ሚና የጎላ ነበር። እንደውም ሴቶች ለሳይንስ ዕድገት ባበረከቱት ድርሻ ወንዶች ባለዕዳ መሆናቸውን ለማመልከት "የሴቶች ውለታ ለክበቡ ግንባታ" በሚል ርዕስ ምዕራፍ ተሰጥቶት የቀረበው ተግባር ማሳያ ነው (ገጽ 34)።

አዳምና ሄዋን ፍሬዋን በልተው ፈርተው እንደተሸሸጉት ሁሉ ፋሌክ እና ኢዮር ፍሬዋን ለመቁረጥ ባደረጉት ሙከራ በተፈጠረው የኤሌክትሪክ ንዝረት ደንግጠው ወደ መንኮራኩራቸው ይገባሉ። ከዚያም አንድ አካል፣ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ብሎ አረጋግቷቸው "አይዟችሁ፣ አትፍሩ" ብሎ አጽናንቷቸው ይሄዳል። የዚህ አካል ንግግር እና ስንብት በነባሩ ሚት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋን ካነጋገረበት እና ከተሰናበተበት መልዕክት ይለያል። "ሰላም ለእናንተ ይሁን" እና "አይዟችሁ!" የሚለው ድምጽ "ወዴት ናችሁ?" ከሚለው የባለቤትነት

ድምጽ እና “እንዲህ በማድረጋችሁ እንዲህ ትሆናላችሁ!” ከሚለው ትዕዛዝ ይለያል። አንደኛ በነባሩ ሚት አስቀድሞ ህግ ተቀምጧል፤ ህጉ ሲጣስም ቅጣት እንዳለ ስምምነት ነበር (ዘፍ 1)። ስለዚህ አስቀድሞ የመንግስት እና የህዝብ ወይም የገዢነት እና የተገዢነት ስምምነት ተደርጓል። ይህ ደግሞ የመንግስትነት ባህሪ ነው። “ከዚህ አትለፍ” የሚል የግዛት ድንበር፣ “አድርግ አታድርግ” የሚል የአስተዳደር ህግ እና “እንዲህ ካደረክ እንዲህ ትሆናለህ” የሚል የኀይል ሚዛንን አካቷል። እንዲህ በመሆኑም የሰው ልጅ ከነበረው ስፍራ እንደተፈናቀለ በነባሩ ሚት ተረኩን እናገኛለን። እዚህ ደግሞ አስቀድሞ የተናገረም ሆነ የተስማሙበት ውል ባለመኖሩ መንግስታዊ አስተሳሰብ እንደሌለ ቆይተንም እንመለከተዋለን። ስለዚህ የዚህ አካል ድምጽ የህዝብ ድምጽ ነው። የበላይ እና የበታች የሚል የመደብ ልዩነት የማይታይበት የጓድነት ድምጽ ነው።

ይህ አካል የሰው መልክ፣ እጅ እና እግር ያለው፣ በላባ የተሸፈነ፣ ቁመቱ ዝግባ የሚያክል እንደሆነ ተገልጿል (ገጽ 166)። ፊቱ የሰውን ባህሪ፣ እጁ ዕውቀቱን /ጥንካሬውን፣ ላባው ጥበቃውን እንደሚወክል በህልም ወቅት የሚታዩ ነገሮች ምን ትዕምርቶች እንዳላቸው (James 220) ይጠቁማል። ስለዚህ በሰው ገጽ የተሳለው እንግዳ ፍጡር የሰው አምሳል መሆኑን እንረዳለን። ይህ ሰው ራሱን የሚጠራውም “ሳይንቲስት ነኝ” ብሎ ሲሆን የቦታውን ስያሜም “የሳይንስ ክበብ” ነው ይላል።

በዚህ ያሉት ሳይንቲስቶች ብዛት 101,010,101,010,101,010,101 ያህል ሲሆን በግዕዝ ምእት፣ እልፍ፣ አእላፍ፣ አእላፈ-አእላፍ፣ ትእልፊት፣ ትእልፊታት፣ ትእልፊተ አእላፋት፣ ምእልፊት፣ ምእልፊታት፣ ምእልፊተ አእላፋት ላይ የተናጋሪውን አንድ ሰው ሲደመር ያህላሉ። እነ ኢዮርን ከሰዎቹ ብዛት እኩል የሳባቸው እና ያስደነቃቸው የግዕዝ አሐዝ ይህን ያህል ቁጥር መግለጹ ነበር። አንድም የግዕዝ ቋንቋ የሰማይ ሳይንቲስቶቹም ቋንቋ መሆኑ እንደገናም ሌላው ቋንቋ የገለጸውን ያህል ግዕዝም መግለጽ መቻሉ ነበር። በሌላ መልኩም በሰማይ ሳይንቲስቶች መታወቁ ብቻ ሳይሆን ለስልጣኔ አለመራቃቸውን ማሳያም ነው።

ሌላው ያስደነቃቸው ጉዳይ ሳይንቲስቶቹ በቁጥር ብዙ ቢሆኑም መልካቸው አንድ አይነት በመሆኑ ሁልጊዜ የሚያናግራቸው አንድ ሰው ይመስላቸው ስለነበር ነው። የሚመስሉት ደግሞ በመልክ ብቻም ሳይሆን አንደኛው የጀመረውን ጉዳይ ሌላኛው ቀጥሎ መወያየት መቻላቸውም ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አካላቸው በአዕምሮ የተሞላ በመሆኑ ነው። መልዕክት ለመለዋወጥ በ“ቴሌፓሲ” አማካይነት ይሰማሉ፤ በ”ቴሌርዕይ” አማካይነት ያያሉ። ሁለቱ

የአዕምሮ ተግባሮች የሚከወኑት በቦታ መገኘት ሳያስፈልግ እና የቃል ልውውጥ ሳይደረግ በአዕምሮ አማካይነት ውስጥ ለውስጥ በመገናኘት ነው።

እነ ኤልያስ በሳይንስ ክበቡ ለማድረግ የፈለጉት በዚህ ሰው ልክ እና ደረጃ ለመድረስ ነበር። ልዩነቱ በምድር ላይ የነበረው ሰው ማንነት አካል ብቻ ሲሆን አዕምሮው ያለው ጭንቅላቱ ውስጥ ብቻ ነበር። በመሆኑም አርቆ ለማየት እና መጥቆ ለማሰብ አይችልም። በሁለቱ ዓለማት ውስጥ ያለው የሳይንስ ዕውቀት እና የእውቀት ስርዓቱ  በጣም ይራራቃል። የጊዜ አቆጣጠሩ አንድ ሰዓት እንደ መቶ ዓመት ነው። ሰዎቹም አይበሉም፤ አይጠጡም። ምግባቸውን የሚያገኙት “ምእዘት” በሚባል አመጋገብ ስልት ነው። ማስፈጨት፣ መፍጨት የሌለበት በጥቅሉ በአመራረትና በአመጋገብ ስልቱ ሁሉ የተለየ ነው። ምግቡን የሚያሰናዱትም ሆነ የሚመግቡት ዕፅዋቱ ናቸው። ዕፅዋቱ ይህን ተግባር በሚገባ እንዲወጡ በከፍተኛ ሳይንሳዊ ዘዴ የሰለጠኑ ሲሆን በመዐዛ መልክ ረቂቅ ተናኝ ምግብ ያዘጋጃሉ። ከመመገብ ውጭ የማጽዳትም ስራ ያከናውናሉ። በ“ኢንፊውዢን” መልክ የሚወጣው ምግብ በቆዳ አልፎ በደም ውስጥ ይዘዋወራል። የሰጡትን ሰጥተው የተቀረውን ራሳቸው ይጠቀሙበታል። ለራሳቸው የሚፈልጉትን ምግብ ወደ ሃይል የሚቀይሩላቸው ”ጀነሬተሮች” ደግሞ ሰዎች ናቸው። የተፈጥሮ ትስስሩ ጥብቅ በመሆኑ የአንዱ መኖር ለሌላው ወሳኝ ነው።

በምድር ላይ የነበረው የምግብ ስርዓት አመራረቱ አድካሚ ውጣ ውረዱም ብዙ ነበር። ሰው ለመብላት፣ ለማድቀቅ የሚያስፈልጉት አካላት እንደ ማሽን በመሆናቸው በቶሎ ይደክማሉ፤ ረዢም ዕድሜም ለመኖር አይችሉም። እነ ፋሌክ ዕፅዋቱ በምድር ካሉት ሰዎች ዕውቀት እንደሚመጥቁ ይረዳሉ (ገጽ 170) ። በዚህም ለምድራቸው ተስማሚ የሆነ የምግብ ስልተ ምርት ”ባዮአግሮሎጅ” ብለው የሰየሙትን አዲስ ዕውቀት ለመተግበር ዕቅድ ይይዛሉ።

ዕጽዋቱ የሚፈጽሙት ተግባር፣ ከሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተና የማያቋርጥ በመሆኑ፣ የአንድ አቅጣጫ ያልተከተለ መሆኑ በሌላ መልኩም ክብ የሚሰራ ግንኙነት አላቸው። በተጨማሪም ከሰዎች ጋር ያላቸው የጋራ ባህርያት እና ለባህርያቱ የሚሰጡት ምላሽ/መስጠት፣ መቀበል የግንኙት ቅጥ ላኪ፣ ተቀባይ፣ መልዕክት፣ ግብረመልስ እንዳለው ማስተዋል ይቻላል/ ከመገናኛ ቁጥጥር (cybernetics) ሃሳብ ጋር እንደሚሰምር እንረዳለን፤ “In Bateson’s view, all systems had some properties in common. For example, the elements in dynamic systems react through feedback and to feedback from other elements in the system” (Hylland 74). ስለዚህ በእንስሳት ላይ ያደረጉት የአዕምሮ ልውውጥ የበይ እና የተበይ ወይም የአንድዮሽ (linear) እንዳይሆን

አስተሳሰቡን ማጥፋት ነው። በመጨረሻም ወደ ምድር ሲመለሱ ይዘውት የተመለሱት ስልተ ምርት አስተሳሰቡ ማሳያ ነው።

በሳይንቲስቶች ዓለም ገዥም ሆነ ተገዥ የለም። ግንኙነታቸው ሰው በሰውነቱ እኩል የሆነበት የወንድማማችነትና የጓደኝነት ነው። ለመጨቆኛ የሚያገለግሉ እንደ ቋንቋ፣ መንግስት ያሉ መሳሪያዎች በዚያ የሉም። ቋንቋ መግባቢያ የመሆኑን ያህል ለግጭት የሚጋብዝ፣ የእኛ እና የእነሱ ተብሎ ድንበር ማበጃ እና የተለየነትን ማሳያም በመሆኑ "ቋንቋ የለንም" ሲሉ የሚግባቡት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የዓለምን ክፍል በአዕምሮ ቀርጸው መመልከት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ አስተሳሰብ ከላይ በሳይንሳዊ ስያሜው "ቴሌፓሲ" ተብሎ ተጠርቷል።

ሌላው መንግስት የኀይል የበላይነትን የሚይዝ አካል ነው። በአንድ ፊቱ አንድነት የማስጠበቅ ጠባይ እንዳለው ሁሉ የመከፋፈያ መሳሪያም ሆኖ እንደሚውል በአቶ በልሁ እና በአቶ ተስፉ ላይ የተፈጸመው በደል እና በነባሩ ሚት የፍጥረት ጅማሬ ታሪክ ማሳያ ነው። አቶ በልሁም እውቀት ከችሎታ እያለ መብት ማጣታቸውን በቁጭት ሲያነሱ እንዲህ አይነት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን መንቀፋቸው ነው። በመሆኑም ሳይንስ ህልው እንዲሆን ሁሉም እኩል የሚተዳደሩበትን ፀረ-አድሏዊ (egalitarianism) ስርዓት ያስፈልጋል የሚለው ሃሳብ በሰፊው ተቀንቅኗል፤ "When the parrot eats, the toucan also eats (an expression of egalitarianism– all people have equal political economic and social rights" (Waldau, 358).

የተሰደደችው ምድር በአዲሱ ምህዋሯ ላይ ተረጋግታ እየኖረች እንደሆነ ቅጂዋ በሆነችው ምድር ያረጋግጣሉ (ገጽ 185)። ያች ምድር ሲወጡ እንደነበረችው ባለ ማንነት አትጠብቃቸውም፤ ተለውጣለች። የእነሮማኖ ተንኮል ለራሳቸውም ሳይበጅ ይዟቸው ጠፍቷል። የ"ኤልያሲዝም" የዓለም ህልፈት ቀመር እዚህ ላይ ይገጥማል። አሳሳቢው የዓለም ህልፈት ሰው ሰራሽ እንደነበር የተገለጸው የምቀኝነት አስተሳሰብን ለመጠቆም ነበር። በዚህም "በአቡጊዳሄውዞ" (በጥንታዊ ኢትዮጵያ ስልጣኔ) ይመታል። "ምድር የያዘችውን "ግስንግስ" ሁሉ አጠንክራ መያዝ ያቅታታል፣...በመሆኑም ሁሉም ነገር ይበታተናል። ማናቸውም በምድር የማግኔት ኀይል ተጠፍሮ የተያዘው "ጓዝ እና ጉዝጓዝ" ሁሉ አውሎ ነፋስ እንደበተነው አዋራ ይሆናል" (ገጽ 135)። ልቦለዱ ረቂቅ ሃሳቦችን ለመግለጽ ሰዎችንና ቁሶችን እንደተገለገለ ካየን ዋናው ግቡ ባህሪን ለመግለጽ እንደሆነም ቃሎቹ ጠቋሚ ናቸው። "ግስንግስ" የማይጠቅም ግን የበዛን ነገር፣ "ጓዝ እና ጉዝጓዝ" የነበረ ወይም ከሌላ ቦታ የመጣን ግን ፈጥኖ መውጣትን የሚገታ፣ ወደ ኋላ

የሚስብን ነገር ያሳያል። ምድር ከተሰደደችበት ያረፈችውና የተረጋጋችው ደግሞ በውስጧ አምቃ ይዛው የነበረውን ነገር ሁሉ ከለቀቀች በኋላ ነው። ዳግም ትንሳዔዋን ያገኘችው የሚሞቱት ሞተውላት ነው።

ታሪኩ ደግሞ የተወጠረው ሳይንስን በሚደግፉ እና በሚቃወሙት መካከል ነው። ከበቡንም ይፍረስ ሲሉ ሳይንስን ከፈረንጅ ውጭ ሌላው እንዳይጨብጠው በመቃወምም ነው። ሳይንስን የደገፉትም የሳይንስ ጥበብ ጅማሬ የዓባይ ስልጣኔ ነው፣ የአፍሪካ፣ የግብጽ፣ የኢትዮጵያ ነው በማለት ነው። በዚህ የሃሳብ ፍትጊያ "የሳይንስ" ነን ያሉት ጅማሬያቸውን ሊመልሱ ወደ ሦስት ሽህ ዘመን ጉዞ ጀመሩ። የተቃወሙትም አሟሟታቸው ከፍቶ መታሰቢያቸው ቀረ። ወደራሳቸው ውስጥ ጉዞ ያደረጉም ከሄዱበት ሲመለሱ ማንነታቸው ተቀይሮ የቀደመውን ያለ "ሃጥያት" ወደ ነበረው አዳም/ ሳይንሳዊ ዕውቀት ወደታጠቀ ሳይንቲስትነት ተቀይረዋል። በለቅሶ ወጥተው ነዶ ሰብስበው በድል ለመመለስ ተዘጋጅተዋል። ዘለዓለማዊ፣ አካባቢውን/ገነቱን የሚጠብቅ እና የሚንከባከብ የተፈጥሮ ጓደኛ ሆነው ይመለሳሉ። አቶ በልሁ ዓለም ገና ብለው እንዳልተሰደዱ ሁሉ ዓለም ጤና /ዓለም ሠናይ ብለው ጠላት በሌለባት ዓለም ሰማይ ላይ ሰፈዋል። በአጠቃላይ ገዢና ተገዢ የሌለባት፣ የመደብ ክፍፍል የማይኖርባትን፣ ተጨቋኞች የሚመሯትን ዓለም በመመኘት፣ ተምኔታዊ ኮሚዩኒዝምን ለማስፈን በመናፈቅ ልቦለዱ ተቋጭቷል።

## 3.4. ኤማንዳ

የኤማንዳ ዋነኛ ጉዳይ የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ዕጣ ፋንታ መወሰን የሚችልን መረጃ መፈለግ ነው። መረጃው የሰፈረው በአክሱም ሃውልት ላይ ሲሆን የተጻፉትን ምስጢራት ለመረዳት ደግሞ የመፍቻ ካርታዎች ያስፈልጋሉ። ሁለቱም የመረጃ ምንጮች ከኢትዮጵያ ተዘርፈው ወጥተዋል። ይህን የሚያውቁ አገራትም ምስጢሩን የግላቸው ለማድረግ በየስለላ ድርጅቶቻቸው መረጃውን ለማግኘት ይሯሯጣሉ። ሰነዱ በሁለት ታላላቅ አገሮች እጅ የወደቀ ሲሆን ኢትዮጵያም እንደ ሌሎች አገሮች በፍለጋው ተሰማርታለች። ፍለጋው በተለያዩ አገሮች የተደረገ ቢሆንም ባለቤቷን ኢትዮጵያን በአንድ ወገን፣ አገራቸውን ለማሳደግ ዓላማ ያደረጉ የግብጽ፣ የጣሊያን፣ ቻይና፣ የጃፓን፣ የራሽያ፣ የአሜሪካ፣ የእስራኤል፣ የእንግሊዝ፣ የሳውድ አረቢያ፣ የህንድ የስለላ ድርጅቶች ይፋጠጣሉ። ኢትዮጵያም "ኤማንዳ 2050" በሚባለው የስለላ ድርጅቷ አማካይነት በኮምፒዩተር ቁጥጥር በመታገዝ ጦርነት አከል ፍልሚያ ታደርጋለች።

ፈላጊዎቹ ተተኪውን ትውልድ የሚወክሉ ምሁር ኢትዮጵያውያን ናቸው። ዓላማውም በሃውልቱ ላይ የተጻፈውን ምስጢር ለመፍታት የሚያስችለውን ሰነድ እና ካርታ በእጃቸው በማስገባት የኢትዮጵያን ገናና ስም ማስመለስ፤ ከዚህ አልፎም ኢትዮጵያን የዓለም የስልጣኔ ቁንጮ ማድረግም ነው።

የፍጥጫው መንስዔ ከ1500 ዓመት በፊት ጣሊያናዊ አሳሽ በአክሱም ሃውልት ላይ የተጻፈውን መረጃ ይፋ በማድረጉ ነው። ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር የከጀለችውም ምስጢሩን የግሏ ለማድረግ በመፈለጓ እንጅ ለቅኝ ግዛት አልነበረም። ምክንያቱም የጦሯን ሃያ ከመቶ አርኪኦሎጅስቶች አድርጋ የአክሱም ሐውልትን ነቅላ ስትወስድ የዳቪንቺ አገር የሃውልት እምሮት ኖሯት ሳይሆን ለመረጃው ጥቅም ስትል ለማድረጓ ሁለቱ ጉዳዮች ማሳያዎች ናቸው። ሐውልቱን ወስደውም ለአንድ ዓመት ምርምር ሲያደርጉ ቆይተው ካርታውንም ተርጓሚ በማጣታቸው ስውር ቦታ ደብቀውታል፤ ሐውልቱንም አደባባያቸው ላይ አቁመውታል። ተጨማሪ ሰነዶችም "በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ አሉ" ስለሚባልም ምስጢሩን ለማወቅ ሁሉም በየፊናው ይሮጣል።

የኢትዮጵያ የስለላ ድርጅት "ኤማንዳ 2050 " በጣሊያን እና በኦስትሪያ መካከል በምትገኝ በብሬነር ኢንስሩብሩክ ተቋቁሟል። ዓላማው የቴክኖሎጂ ማዕከል በማቋቋም፣ ኢትዮጵያዊ ምሁሮችን አሰባስበው ዘመናዊ የሳይንስ ዕውቀት ማስታጠቅ ነው። ይህን እውን ለማድረግም "የኦስትሪያን የወይን ፍላጎት ለማርካት" በሚል ስልት ከመንግስት ሰፊ የእርሻ ቦታ ተረክበው ስራ ጀምረዋል። በምግብ እጥረት ለምትሰቃየው አገራቸው ምርጥ ዘሮችን በማዳቀል ችግሩን በመጠኑ መቅረፍም አንደኛው ተግባራቸው ነው። ሌላው የሰው ሃይል ልማት ላይ በማትኮር ከአገር ውስጥ እና በሌሎች አገሮች የተበተኑትን ኢትዮጵያውያን በማሰባሰብ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂያዊ አቅም ማዳበር ነው። ቤተ-ሙከራው የዓለምን ቅርጽ የያዘ እና ክብ ሲሆን ግድግዳውና ኮርኒሱ በአንድ ላይ በተያያዘ የኮምፒዩተር መስታወት ተሰርቷል። ከኮርኒሱ ጀምሮ የሚወርዱ 198 ያህል አገሮችን የሚያገናኙ መስመሮች አሉት። የመገናኛ መረቦቹ እጅግ ፈጣን ከመሆናቸውም በላይ ሊጠለፉም ሆነ በቫይረስ ሊጠቁ አይችሉም። ኮምፒዩተሮቹ ላይ የተጫኑት ሶፍትዌሮች የጠላትን ወይም የሚፈለግን ዳታ ቤዝ የመስበር አቅም አላቸው። አገልገሎቱን ለማግኘትም በመጀመሪያ በኤማንዳ 2050 ሰርቨር ውስጥ መግባት ያስፈልጋል። ከዚያም አድራሻ እንዳይታወቅ ስለሚገባ የሌላ አገር ሰርቨር ይሰበራል። ከዚያ የኢትዮጵያን የአካባቢ ቁጥር በማስቀደም ‹‹፰፲፴፯፱፱፱፴፩›› የሚል አሃዝ በመጨመር ወደ ሰርቨሩ ይገባል (ገጽ 113) ።

የግንኙነት መስመሩ በእንዲህ መልክ ስለሚዘረጋ ሌላኛው አካል እውነተኛውን አድራሻ ማግኘት ያቅተዋል። በሌላ አባባል “ይሸውዳሉ” ወይም “ያታልላሉ”።

ተጨማሪም የሌሎችን የመረጃ መረብ ሰብረው እንደመግባታቸው የእነሱ ተሰብሮ ሊገባም ሆነ ሊጠለፍ አይችልም። በዚህም አቶ ጋዲሳ የኮምፒዩተር ኢንጂነር ዳይሬክተር፣ ታሪኩ በኋላም “ኤማንዳ” (የዕድገት መንገዴ” ማለት ነው) የኮምፒዩተር ባለሙያ ስራ አስኪያጅ፣ ዶክተር ትንሳኤ አርኪኦሎጅስት የማዕከሉ ማዕዘን፣ ባንቾ ይርጋ፣ ጥላሁን፣ እስማኤል፣ ተስፋሁን፣ ዶክተር አዎት … ከአቻዎቻቸው ጋር ይፋለማሉ። ግብጽ በሌላ ወገን “የወደፊት ተስፋችን” በሚሉት አብዱልጋኒ አማካይነት ለአምስት መቶ ዓመት የፈለገችውን መረጃ ለማግኘት ስልቷን ትቀያይራች። ሲያስፈልግ ኢትዮጵያዊያንን፣ ራሽያንን፣ ቻይናንን በመጠቀም የግሏ ለማድረግ ትጥራለች። ቻይናም በልቿንግ አማካይነት ሮም ላይ ያለውን የአክሱም ሃዉልት አናት ለመቁረጥ ከመሞከር  ካርታውን እስከ መስረቅ ትደርሳለች። አሜሪካም በስለላ ልምዱ “አጅሬ”  እየተባለ የሚጠራውን ፒተር ሃንስን ኢትዮጵያ በመላክ መረጃዎቹን የግል ለማድረግ ትሞክራለች። ኢትዮጵያም ሮም፣ ቻይና ድረስ በመሄድ የባለቤትነቷን ያህል ትጋደላለች። ሌሎቹም እየተጣመሩና የሃይል ሚዛን ወዳደላበት እያዘነበሉ ጦርነቱን ተቀላቅለዋል። በመጨረሻ ኢትዮጵያ እነዚህን ታላላቅ አገራትን በመጠቀ የቴክኖሎጂ አቅሟ በመታገዝ በእጇ ታስገባለች። የኖህ መርከብ በመሆን ለዓለም ታዳጊ ትሆናለች። እንዴት? እና በምን? የሚለውን ደግሞ እንመልከት።

ምስጢራዊ ሰነዱ “2050” የሚል የምስጢር ቁጥር የያዘ ሲሆን ሌሎች ምስጢራዊ ቁጥሮች  ይህን ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ይታወቃሉ። ጣሊያናዊው መምህር ጆቫኖ ካፔሎ ተማሪያቸውን ዶክተር ትንሳዔን ወደ አክሱም ይዘውት ሄደው ሐውልቱ ስር ባገኙት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ የተጻፉትን ቁጥሮች ሲያገጣጥሙት “2050” የሚል ምስጢራዊ ቁጥር፣ ዘንባባ እና የእሳት ነበልባል ምልክቶችን አብረው ይመለከታሉ። የቁጥሩን ትርጉም “ተማሪ ስለሆንክ ራስህ ፈልግ” በማለት ሲዘሉት ምልክቶቹ ግን ይተረጉሙለታል (ገጽ 67)። ጎልቶ የሚታየው ዘንባባው ረገርም የስልጣኔ ዘመን ያመለክታል። የእሳት ነበልባሉም ለጥቂት ጊዜ በችግር ታሳልፋለች በማለት የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፋንታ ይነግሩታል። ዶክተር አብዱልጋኒም እንደ ዶክተር ትንሳዔ ሁሉ በልጅነቱ አስተማሪው ስለኢትዮጵያ እና ሃውልቶቿ ምስጢር በነገሩት መሰረት እስከመጨረሻው ፍለጋውን ይቀጥላል። ዶክተር ትንሳዔ የሃውልቶችን ቴክኖሎጂያዊ ፋይዳ እስከ ዶክትሬት ዲግሪው ድረስ አጥንቷል። በምርምር ሂደቱ ምንም እንኳ

ፍቻቸውን ለጊዜው ባያውቅም “24፣ 160፣ 2050” የሚሉት ምስጢራዊ ቁጥሮችንም አግኝቷል። “ኤማንዳ 2050” የቴክኖሎጂ ሙከራቸውን የቻይናን የስለላ ድርጅት አከርካሪ በመምታት ጀምረዋል። ቻይናውያን ሮም ላይ ያለውን የአክሱም ሐውልት አናቱን ለመቁረጥ እንዳቀዱ መረጃዉ ሲደርሳቸው ወደ ጣሊያን ያመራሉ። ዶክተር ትንሳዔ በኮንትራት ሰራተኛነት ተቀጥሮ ኢንስብሩክ ከሚገኘው የኤማንዳ ቴክኖሎጂ ቤተ-ሙከራ የመረጃ ማሰራጫ ሳተላይት ጋር በማገናኘት መረጃውን ያሾልክባቸዋል።

የቻይና የስለላ ድርጅት ዶክተር ትንሳዔ መረጃውን እንደላከ አውቀው ሲከታተሉት የኤማንዳ የሳተላይት ቁጥጥር ያለበትን ክፍል ከሌላ ጋር በማያያዝ መገኛ ቦታውን እንዳያገኙት ያደርጉባቸዋል። ትንሳዔ ሲያመልጣቸው ኮምፒዩተሩን ትቶ ስለሄደ ቻይናውያን ኮምፒዩተሩን ይከፍቱታል። ትንሳዔ “ኤማንዳ” የሚባለው ኢትዮጵያዊ የስለላ ድርጅት አባል እንደሆነ ያውቃሉ። ስለኤማንዳ መኖር የሰሙትን ጭምጭምታ ያረጋግጣሉ። በቴክኖሎጂ ምጥቀታቸው ንቀታቸውን እዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ግርምት ቢኖራቸውም የቴክኖሎጂ ውድድሩን ግን ይረዳሉ። የአክሱምን ሃውልት አናት ቆርጠው ለመውሰድ ያደረጉትም ሙከራ በኢትዮጵያውያን ይከሽፋል። ሄሊኮፐተራቸው ይጠለፋል፤ አንደኛውን ሄሊኮፐተር ያበር የነበረው እና እንደ ልቿንግ በሌላ በኩል ያለውን ተልዕኮ ይመራ የነበረውን ቻይናዊ “ሊ”ም ይገደላል። ገዳዩ ኤማንዳ ሲሆን ከዚህ በፊት የትንሳዔን ሚስት እና ሁለት ልጆች እንዲገደሉ በማድረጉ ዋጋውን ይሰጠዋል። እንዲህ አይነቱ ድርብርብ ሽንፈት ለታላቂቱ ቻይና የሚዋጥ ስላልነበር ልቿንግ ይባረራል።

ሁለተኛውን ተልዕኳቸውን በጣሊያን መንግስት ላይ በማድረግ የቴክኖሎጂ ምጥቀታቸውን አሳይተዋል። ተልዕኮውን ለመወጣት የጣሊያንን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ልጅ ይጠልፋሉ። ከዚያም የኮሎምቢያን የሳተላይት መስመር በመጥለፍ የኤማንዳ 2050 የሳተላይት ምህዋር  ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ጋር ያገናኙታል። ስልኩ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ውስጥ ካለው ሳተላይት ጋር ስለተገናኘ ከኮሎምቢያ እንደተደወለው ይሆናል። ለመከታተልም ሆነ ለመጥለፍ ቢፈልጉ ትክክለኛውን አድራሻ ሊያገኙት አይችሉም። በመቀጠል በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ውስጥ በተተከሉት ካሜራዎች አማካይነት የሳተላይት ቅኝት በማድረግ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይደውላሉ። ከዚያ የልጃቸውን ምስል ያሳዩአቸውና ወደ ድርድሩ ያመራሉ። ሞሶሎኒ ከኢትዮጵያ ዘርፎ ያመጣቸውን ምስጢራዊ ሰነዶችን እንዲመልሱላቸው ይጠይቋቸዋል (በዚህ ወቅት ሃውልቱ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ነበር) ።

ከአራት ዓመት በፊት ልቿንግ ሁለቱን የእምነበረድ ካርታዎች ሰርቆ ስለወሰዳቸው የልጃቸው አጋቾችም የቀረውን ሰነድ ለመውሰድ የከጀሉ ቻይናውያን እንጅ ኢትዮጵያውያን አይመስሏቸውም። በንቀታቸው እነ ኤማንዳ ይናደዳሉ። የደህንነት ሚኒስቴሩ "ሊሆን አይችልም" ብለው በመቃወማቸው የሊቢያን ጎሳዎች የጨፈጨፉበትን መረጃ ምስል ያሳዩአቸዋል። ነገር ግን የማይሰጧቸው ከሆነ መረጃውን ለዓለም እንደሚያሰራጩት ሲነግሯቸው ይበልጥ ይደነግጣሉ። ለልጃቸውም፣ ለደህንነታቸው ሲሉ መረጃውን ይመልሳሉ። ከዚያ የቀረውን ሁለት ካርታ ለማምጣት ወደ ቻይና ይሄዳሉ። ከልቿንግ ጋር የሞት ሽረት ትግል ያደርጋሉ። ጣሊያን ላይ ካርታዎችን ለማዘረፍ ባደረገው ትግል ሁለት እግሮቹን ያጣው ሏቿንግ በተኩስ ልውውጡ ህይወቱንም ያጣል። ከሁለቱ ካርታዎች ጋር ለአስራ አንድ ዓመት ስለ አክሱም ሃውልት ያጠናውንም ጽሑፍ ጨምረው ይዘው ወደ አገራቸው ይገባሉ።

በካርታዎቹ ላይ የተጻፉትን ምስጢራት መፈለጋቸውን ይቀጥላሉ። እንደ ኦስትሪያው የተሟላ ባይሆን አዲስ ቤተ-ሙከራ ከፍተው ስራቸውን ይቀጥላሉ። ስለዚህ የኦስትሪያውን ቤተ-ሙከራ ነቅሎ ለማምጣት አብዱልጋኒ ግብጽ በሳተላይት ስለሚከታተላቸው መንግስቱን ለማስወገድ ያቅዳሉ። በኢንተርኔት ብቻ የሁስኒ ሙባረክን የስልጣን ዘመን ለማሳጠር የወቅቱን የአገሪቱን ህዝባዊ አመጽ ሊጠቀሙበት ይወስናሉ። ስለዚህ የግብጽን የኢንተርኔት መረብ ሙሉ ሙሉ ይቆጣጠራሉ። የእያንዳንዱን ግብጻዊ ግላዊ የመገናኛ ቁጥሮችን በእጃቸው ያስገባሉ። ከዚያም በተቃውሞ መልዕክት በእያንዳንዱ አድራሻ ያስገባሉ። ጅምሩ እሳት ይቀጣጠልና ሁስኒ ሙባረክ ከስልጣን ይወርዳሉ። ከዚህ በተቃራኒም ለስድስት ዓመት ያህል በመድከም ኢትዮጵያ በመረጃ ቁጥጥር ጦርነት እንዳትጠቃ አዲስ ሶፍትዌር ይፈጥራሉ። ኢትዮጵያዊ የሆኑና ኢትዮጵያዊ ስም ያላቸው ሁሉ ስማቸውን ከኢንተርኔት በመውሰድ "እርኩስ" በሚል ቫይረስ ይቀይሩታል። ዓለም ቫይረሱን ስለሚፈራ ስሞቹን አይመርጣቸውም፤ በመሆኑም ከመረጃ ስርቆሹ ይጠበቃሉ።

በግርግሩ ኦስትሪያ የነበረው ቤተ-ሙከራ መጥቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ይገጠማል። በካርታው መሰረትም ሙከራ ይቀጥላል። ከ335 የሙከራ ጊዜ በኋላ ለውጥ ያያሉ። ከተራራው ስር ከተገጠሙት ኮምፒዩተሮች ጋር የተያያዙት በ120 ዲግሪ ርቀት ያሉት መረጃዎች ምስሎች ብዥ ብለው መታየት ይጀምራሉ። በጋማ ጨረር አማካይነት 6400 ኪ.ሜ. ወደ ከርሰ ምድር ዘልቆ በሚገባው ግዑዝ ነገር አማካይነት የሚቀጥሉትን 35 ዓመታት ዓለምን ቀጥ አድርጎ የሚይዝ የነዳጅ ክምችት እንዳላት ይመለከታሉ። እያንዳንዱን የኢትዮጵያ ካርታ

በኮምፒዩተራቸው ላይ ሲጫኑ በመጠን፣ በጥራት፣ በጥልቀት ለይቶ ያስቀምጣል። ከዚያም የሩቅ ምስራቅ አገሮችን መረጃ ከሳተላይት መስመራቸው ጋር በማያያዝ ለመመልከት ሲሞክሩ ወደ ከርሰ ምድር ስለማይዘልቅ አፈራቸውን ብቻ ያያሉ።

ከዚያም በ2050 በኒክሌር በመመታቸው፤ 90 ከመቶ የሩቅ ምስራቅ አገሮች በመሬት መንሸራተት ይወድማሉ፤ 84 ከመቶ የአውሮፓ መሬት በእሳተ ጎመራ፣ በከፍተኛ ቅዝቃዜ እና በረዶ እንደሚጠቁ መረጃው ያገኛሉ (ገጽ 193)። ራሽያ በ60 ዓመት፣ ቻይና በ30 ዓመት የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዳደረጉ ሁሉ ኤማንዳ 2050ም ኢትዮጵያን በ45 ዓመት የቴክኖሎጂ ባለቤት ያደርጋታል" ብለው ያቅዳሉ። ለዚህም በ2006 ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ምርምር የሚገቡትን ኦስትሪያ ውስጥ የሚሰለጥኑትን 560 ልዩ ችሎታ ያላቸው ወጣት ተማሪዎች ዋቢ ያደርጋሉ። በዚህም በ2050 ዓ.ም. "አዋሽ-2050" በየአምስት ዓመቱ አስተማማኝ የሆነ የአየር ሁኔታ ቅድመ መረጃ የሚገልጽ ሶፍትዌር ለመፍጠር፣ "ካራማራ-2050" የሚባል ሳተላይት ወደ ጠፈር ለማምጠቅ ያቅዳሉ። ይህን ራዕይ እውን ለማድረግም የተወሰኑት ሳይንቲስቶች ኦስትሪያ ሌሎችም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥናታቸውን እንዲቀጥሉ ይወስናሉ።

የኤማንዳ ዋነኛ ሳይንሳዊ ጉዳይ የቁጥጥር ስልት ሲሆን በሁለት መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። አንደኛው ዘረ-መል ቴክኖሎጂ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኮምፒዩተር መረጃ ቁጥጥር ነው። በሁለቱም ጉዳዮች ውስጥ የማንነት ጥያቄ ይነሳል፤ አዲስ ማንነትም ይገኛል ወይም እንደገና ይሰራል። በቅድሚያ የኮምፒዩተር ቁጥጥሩን አስቀድሜ የዘረ-መል ቴክኖሎጂውን መተንተኔን እቀጥላለሁ።

በቀዳሚው የአክሱም ሃውልት ቴክኖሎጂና በኢንስብሩክ የተቋቋመው የቴክኖሎጂ ማዕከል ተግባር የመረጃ ማዕከልነት ነው። በሁለቱም ድንበርን የማስከበር ፍልሚያ ተገርጓል። በአክሱም ዘመን የነበረው ሐውልት ላለማስደፈር የመርከብ መቆጣጠሪያ የሚይዙ ሰዎች ነበሩ "በወቅቱ አክሱማዉያን መርከቦቻቸውን በባህር ላይ ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት ልዩ ምስጢራዊ ቁስ ነበር። ...እነዚያን የመርከብ መቆጣጠሪያ ግዑዝ ነገር የያዙ ግለሰቦች የት እንደደረሱ እስከዛሬ አይታወቅም" (ገጽ 14)። በኢንስብሩክ የመረጃውን ሉዓላዊነት ለመጠበቅና እንዳይሰበር በሚስጢር ቁልፍ ቆልፈውታል። በአክሱም ዘመን በሰው ሃይል በዘመናዊው ቴክኖሎጂ ደግሞ በኮምፒዩተር ቫይረስ ተዋግተዋል። በአክሱም ሃውልት ላይ የተጻፈውን መረጃ ለማስተረጎም ካርታዎቹ እንዳስፈለጉ፣ ካርታዉ ላይ የተጻፉት አራት አንቀጾች የያዙት የተለያየ ግን በጋራ ሲሰባሰቡ የሚያስገኙት አንድ ፍች የግንኙነቱን ስርዓታዊነት ያሳያል። ኢንስብሩክ ላይ

የተዘረጋው ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ማዕከል ውስጥ ያሉት 198 መስመሮች ወደ አንድ የመረጃ ቋት ውስጥ ሲገቡ የሚያስገኙት ፍች ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም መረጃዎች የያዙአቸው መለያ ቁጥሮች ትርጉም የሚያስገኙት አብረው ሲመጡ ነው። ያለ ካርታው ሃውልቱ ድንጋይ ነው፤ ያለ ኮምፒውተሩ ውስጣዊ ስርዓት (software) ፣ የመረጃ መቀበያ ሳጥኖቹ (hardwares) ወይም በተገላቢጦሹ እንዲሁ ነው። ሁለቱም የዓለም ጉዳይ የራሳቸውም ነው። መረጃዎችን ሸምነው የሚያቀርቡበት ቅብብሎች እንዲሁ ተመሳሳይ ነው። ስለ ቤተ-ሙከራው ቅርጽ የተገለጸውም የዚህ ማሳያ ነው። የዓለምን ቅርጽ ወይም ክብ መሆኑ የማንኙነቱን መጀመሪያ እና መጨረሻ ወይም የማቆሚያ መአዘን እንደሌለው ሲያመለክት የትስስሩን ጥብቀት እንደሚያሳይም ከዚህ በታች ያለው ሃሳብ ያስረዳል፤ “Cybernetics is the elucidation of the circuitry of the world, and how that circuitry can best be appreciated and maintained for the future existence both of human societies and their relation to the natural environment” (Rapport, Nigel 102) .

እንዲሁም ሁለቱም ማንነትን ለመፍጠር ትልቅ ድርሻ አበርክተዋል። የሰለጠነ፣ ያልሰለጠነ፣ ነጩ፣ ጥቁሩ፣…ሁሉም በእኩል ፈልገውታል። መረጃው በእጃቸው እያለ የነበራቸው ስም እና ማንነት በአንድ ወገን ይቆማል። እንዲሁም መረጃው ከእጃቸው ሲወጣ እና ሃይላቸውን ሲነጠቁ ነበራቸው ስም በአዲሱ ቴክኖሎጂ አማካይነት የተሰጣቸው ስም እና የማንነት ለየብቻ መታየት አለበት። ስለዚህ የማንነት ትርጉሙ እየተሰራ መፍረስ፣ እየፈረሰ መሰራት፣ የሚል ክብ የሚሰራ የማንነት ቀለትን ያሳያል። ከላይ በትንተና ላይ እንደታዩት ልበለዶች ጉዳዩን ወደ ሰው ብንወስደው ሰው አካል/አዕምሮ ነው የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ለመረጃው ባላቸው ወሳኝነት፣ ቀዳሚነት አንጻር ወሳኙ የሰው ወይስ ቴክኖሎጅ የሚለው አካል/አዕምሮ ከሚለው ጋር ይተሳሰራል። ስለዚህ ሰውና ቴክኖሎጂ በየራሳቸው የሚታወቅ ቢሆኑም ለመረጃው ያላቸው ቅርበት ግን እኩል እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በመሆኑም በእነዚህ የመረጃ ማግኛ ስርዓቶች አማካይነት እንዴት ማንነት መሰራት እንደሚቻል ወደ ሰዋዊ ጉዳዩ በማምራት እንመልከት። በቅድሚያ መረጃ በሃይልነቱ ከዓለም የመነጠል እና የማስተሳሰር አቅሙ እንዳለው አስታውሰን ይሆናል። ስለአክሱም ዘመንና ሃውልት ቴክኖሎጂ ሲነሳም ስሜቱ ከእዚህ እኩል ነው። የመረጃው ባለቤት መሆንም ተፈላጊነት ይጨምራል። የዋጋውን ውድነት ባለቤቱ ብቻ ሳይሆን ከመረጃው ውጭ ያሉት ተቀናቃኞችም እንዲናገሩ የመረጃው ጉልበት ያስገድዳቸዋል። ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ በዓለም

ስልጣኔ ቀዳሚ እንደነበረች ግብጻዊው የዶክተር አብዱልጋኒ መምህር (ገጽ 120)፣ ጣሊያናዊው የዶክተር ትንሳዔ መምህር (ገጽ 67)፣ ቻይናዊው ሰላይ (ገጽ 64) ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

በተቃራኒው ሃይሏን ያጣቸውን የዛሬዋን ኢትዮጵያ ሉቿንግ፣ የጣሊያኑ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የደህንነት ሚኒስትሩ  በዓለም ርሃብተኛ፣ ድሃ፣ ደደብ፣ ተቀጣሪ፣ የአዕምሮ ርሃብተኛ ፣ …እያሉ በንቀት ጠርተዋታል። እንዲህ አይነት ስሞች እና ማንነቶች የኢትዮጵያ መታወቂያ እና ታሪክ ሆኑ። በዚህም ታሪኩ፣ ኤማንዳ "የዕድገት መንገዴ" ማለት መሆኑን ካታወስን  ስም ከማንነት እና ከሚሰጥ ተልዕኮ አንጻር ግንኙነት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ስማቸው የተለወጠላቸውን ሰዎች ማስታዎስ ይቻላል። አብራም/አብርሃም፣ ሦራ/ሳራ፣ ያዕቆብ/እስራኤል፣ ሳውል/ ጳውሎስ ፣ … የተባሉትን ሰዎች ስማቸው ሲቀየር የማንነት ለውጥ እንዳመጡ ሁሉ "ታሪኩ" የሚለው ስም ያለፈን ታሪክ ማስቀመጫ ሰነድ ነው። ኤማንዳ በአንጻሩ "የእድገት መንገዴ" ዕድገት ወደፊትን የሚያሳይ ነው፤ ስለዚህ በስሙ ውስጥ ትንቢት አለ። የማደግ፣ የመለወጥ፣ የመሰልጠን ተስፋ ያመለክታል። የኤማንዳን የስለላ ድርጅት ያቋቋመውም እሱ መሆኑን ሲታወስ የዛሬው ኤማንዳ  የትናንቱ ታሪኩ ነበር። በኤማንዳ ስም ውስጥ ያለው ተስፋ በመጨረሻ ላይ የተገኘው ነዳጅ የአገልግሎት ዘመን ይህን የሚያረጋግጥ ነው። በከርሰ ምድሩ ሃብት ዓለምን ለሰላሳ አምስት ዓመት ቀጥ አድርጎ የሚይዝ ነው። ሰላሳ አምስት ደግሞ ተስፋን የሚወክል ቁጥር ነው (James 235) ። ለዚህም ነው ኢንስብሩክ ውስጥ የተቋቋመው የቴክኖሎጂ ቤተ-ሙከራ የአክሱም ሃውልት ሌላ መልክ ነው የተባለው።

ሁለተኛው የዘረ-መል ቴክኖሎጂ የኢትዮጵያን የምግብ እጥረት ለመፍታት ሲባል ምርጥ ዘር ማዳቀል ነው። የሚዳቀሉት አዝርዕት የተለያዩ ቢሆኑም በሂደቱ አዲስ ዘር ይገኛል። የአንዱ መኖር ለሌኛው እኩል እንዳስፈለገ ሁሉ አዲስ የሚገኘውም የመጀመሪያዎቹ የሁለቱ የጋራ ማንነት ውጤት ይሆናል። ለአዲሱ ማንነት መፈጠር የተለያዩ አዝርዕት እንዳስፈለጉ ሁሉ የእያንዳንዱ ድርሻ የጥገኝነት ሳይሆን ሙሉነትን የመፍጠር ነው።

እነዚህን ሁለት ቴክኖሎጂያዊ ዉጤቶች ስለማንነት የሚሰጡት ፍልስፍናዊ ፍች የሁለትዮሻውያንን አመለካከት ያሳየናል። በዴካርት አገላለጽ መሰረት ሰው/ቴክኖሎጂ የሚል ተጣማሪዎችን  የእኩል ግንኙነት ድርሻ ማውጣት ይቻላል። ግንኙነታቸውም በሁለቱ መካከል ባለው የመረጃ ቅብብል እና መረጃዎቹ በአኗኗር ፣ በአስተሳሰብ ፣…ላይ በሚፈጥሩት ግንኙነት እና በምላሹ የነገሮችን ወሳኝነት ማስቀመጥ ይቻላል። በዚህም ኤማንዳ በሁለትዮሻውያን

ፍልስፍና ተቃኝቶ የተጻፈ ሲሆን ስለማንነት ግን ሁለት የተለያየ ምላሽ ሰጥቷል። ኢትዮጵያ የስለጠነች አገር ነበረች ሲባል የቴክኖሎጂ ውጤት ሆኖ የሚጠቀሰው የአክሱም ሃውልት ነው። የስልጣኔ ፈር ቀዳጅ ነች ስትባልም የሚጠቀሰው ይኸው ተግባሯ ነው። በዚህ ተግባሯ ደግሞ ዓለም ዕውቅና ሰጥቷት ማንነቷን በዚሁ ልክ ሰርቶ መጠሪያዋን አበጅቷል። ባንቀላፋችበት ዘመንም የድህነት እና የርሃብ መታወቂያ በመስጠት ማንነቷን ገልብጦታል።

ነገር ግን የትንሳዔ ዘመን ሲመጣ እና ቴክኖሎጂውን ስትጨብጥ የኢትዮጵያውያኑም ዓላማ ገናን የነበረውን የጥንት ክብሯን መመለስ ነው። ስለዚህ በቴክኖሎጂያዊ ተጽዕኖው አማካይነት የመጣው አዲስ ማንነት ሳይሆን የተመለሰው የነበረው ነው። በአዝርዕቱ ውህደት የተገኘው ደግሞ አዲስ ማንነት ነው። የተለያዩ ማንነቶች ወደ አንድነት ሲመጡ ከሁለቱ የተለየ ሌላ አዲስ ማንነት ብቅ ይላል። ይህ አዲሱ ማንነት ድቅያ (hybrid) እንጅ የመጀመሪያውን ማንነት ሊይዝ አይችልም።

## ምዕራፍ አራት፤ ማጠቃለያ

ጥናቱ "የአማርኛ የሳይንስ ልቦለድ ሙከራዎች፣ በተመረጡ ልቦለዶች ማሳያነት" በሚል ተደርጓል። ልቦለዶቹ በአማርኛ ቋንቋ በተጻፉ አራት ረዥም ልቦለዶች ሲሆኑ ይዘታቸውን መሰረት በማድረግም ትንተና ተሰጥቶባቸዋል። ዓላማ ያደረገውም በሳይንስ ልቦለድ ውስጥ የሚነሱ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች የተቃኙበትን የፍልስፍና መሰረት በመለየት ማንነትን ለመፍጠር፣ ለመገንባት እና ለመግለጽ እንዴት እንደዋሉ ማሳየት ነበር። በተለይም የሳይንስ ልቦለድ ተዛማች ዘውግ በመሆኑ የተለያዩ ሳይንሳዊ ኀልዮት ማንሳቱም አይቀርም። አዲሶቹ ኀልዮት በባህል መዳፍ ስር ሲወድቁ የተቀባዩ ባህል እንዴት? እና ለምን ተግባር ያውላቸዋል? የሚለውን መመርመር ሌላው ጉዳይ ነበር።

በመሆኑም የሳይንስ ልቦለዶቹ ከሳይንሳዊ ጉዳዮች ባሻገር ስለ ማንነት ምን አይነት ምላሽ ሰጥተዋል? የሚለውን ፈትሿል። የማንነት ፍች ከሚታወቅባቸው መንገዶች ውስጥ "እኔ ማን ነኝ?" "ከየት መጣሁ?" እና "ወዴት እሄዳለሁ?" የሚሉትን ፍልስፍናዊ /ሚታዊ ጥያቄዎች ልቦለዶቹ እንዴት መለሱት? የሚሉት ናቸው። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ልቦለዶቹ የተለያዩ የማንነት መፍጠሪያ ስልቶችን ተገልግለዋል። ምላሻቸውንም እንደሚከተሉት ርዕዮት እና የፍልስፍናዊ ዕውቀት መሰረት አድርገዋል። በነደደ ፍላጎት አማካይነት ነው? ወይስ ትዝታን መሰረት አድርገው ነው? የሚለውም ተመልሷል።

በዚህም *የራስ ምታት* እና *የቢሆን ዓለም* "ሰው ማን ነው?" የሚለውን አካል/ አዕምሮ በሚሉት ተቃርኖዎች ሸምነው አቅርበዋል። ምንም እንኳ ሁለቱም ዘረመል ምህንድስና (genetic engineering) ላይ ተመስርተው የአእምሮ ልውውጥ ላይ አትኩረው ተመሳሳይ ሳይንሳዊ ጉዳይ ቢያነሱም ለማንነት የሰጡት ምላሽ ግን የተለያየ ነው።

*የራስ ምታት* ሰው "አዕምሮ ነው" የሚል አንድምታ ስላለው በሃሳባውያን ፍልስፍና ተመርቶ እንደተጻፈ ተመልክቷል። በአንጻሩ *የቢሆን ዓለም* "ሰው አካል ነው" ወይም ስነ-ህይወታዊ ማንነት አለው" የሚል አንድምታ ያለው በመሆኑ በቁስ አካላውያን ፍልስፍና ተቃኝቶ እንደተጻፈ መደምደም ተችሏል። በሁለቱም ልቦለዶች ሳይንሳዊ ውጤቱ ባስከተለው ጠንቅ ማህበራዊ ቀውስ ይፈጠራል። ጭፍግ፣ ዝብርቅርቅ ዓለም /dystopia/ ይፈጠራል። የማንነት ጉዳይም ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

ውጤቱን ተከትሎ የሰጡት ምላሽ እንደ ፍልስፍናዊ ቅኝታቸው ሁሉ ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ያላቸው አመለካከትም ይለያያል። *የራስ ምታት* ሳይንሳዊ አስተሳሰቡን በመኮነን ለተበላሸው ማህበራዊ ህይወት ቴክኖሎጂውን ተጠያቂ ያደርጋል። *የቢሆን ዓለም* በበኩሉ ማህበራዊ ስርዓቱ እንደተበላሸ ያሳያል። ለዚህም ተጠያቂው ሳይንስን እጁን በመጠምዘዝ ከዓላማው ውጭ ለማዋል ያሰበውን የሰውን አስተሳሰብ ይኮንናል። በመሆኑም ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ከሰው ጋር ባለው ግንኙነት ገለልተኛ (neutral) አድርጎታል።

ሁለቱም ልቦለዶች ተመሳሳይ ሳይንሳዊ ኀልዮት አንስተው በማንነት ላይ ባላቸው አመለካከት ግን ተለያይተዋል። በ*የቢሆን ዓለም* "ሰው ስነ-ህይወታዊ ማንነት አለው" የሚለው የቆስ አካላውያንን መላምት መሰረት በማድረግ በአዕምሮ ልውውጡ ማንነት ሳይቀየር ይዘልቃል። በማንነት መፍጠሪያ ስልቶች *የራስ ምታት* ሆነ *የቢሆን ዓለም* ውስጥ የታየው አዲስ ማንነት ከነደደ ፍላጎት የመነጨ እንጅ ምንም አይነት ማህበራዊ መሰረት እንደሌለውም በጥናቱ ተመልክቷል።

*የሳይንስ ራዕይ* እና *ኤማንዳ* በአንጻሩ "የዘረ-መል ቴክኖሎጂ" እና "የቴክኖሎጂ መረጃ ቁጥጥር" የሚሉትን ሳይንሳዊ ኀልዮት በዋናነት አንስተዋል። ምንም እንኳ *የሳይንስ ራዕይ* ስድስት ያህል ሳይንሳዊ ኀልዮት ቢያነሳም በሁለቱ ውስጥ የሚጠቃለሉ መሆናቸው አብረው ታይተዋል። የማንነት ፈጠራ መንገዱንም በሁለትዮሻውያን ፍልስፍና ተቃኝተው ቀርበዋል። በማንነት ፈጠራ ስልቱም ትውስታ ላይ የተመሰረቱ ሲሆን የሚፈጠረውም ማንነት የቀደመውን እንደገና መስራት ወይም ማስመለስ ላይ ትኩረት አድርገዋል። ታሪካዊ መረጃዎችን፣ አፋዊና ቁሳዊ ባህሎችን ዋቢ በማድረግ አቅርበዋል። ታሪኮቹ የሚደመደሙትም ባገኙት አዲስ ማንነት እና ሳይንሳዊ ድሉ በሚረጨው ተስፋ አማካይነት ብሩህ /utopia/ ነው። በመሆኑም ሳይንስ መጣልን እንጅ መጣብን አይባልም። ሳይንስና ሰው እኩል ደረጃ በመያዝ የአንዱ መኖር ለሌላው ተስፋ ሆነው ቀርበዋል። ነገር ግን የቴክኖሎጂያዊ መሰረተ ሃሳባቸው የተለያየ ነው። *ኤማንዳ* ቴክኖሎጂውን አገር በቀል ዕውቀት ላይ የመሰረተ እና ኢትዮጵያዊ መነሻ ያለው ያደረገ ሲሆን ለሌላው ዓለምም የኢትዮጵያ ስልጣኔ መሰረት ነው የሚል ማጠቃለያ አለው። *የሳይንስ ራዕይ* ምንም እንኳ የአርበኝነት ስሜት ተጭኖት ሳይንሳዊ ተግባራቱ የተከወኑ ቢሆንም የምዕራባውያን ሳይንሳዊ ዕውቀት እያጣቀሰ አቅርቧል። ግቡም ተምኔታዊ ኮሚዩኒዝምን ማስፈን በሳይንስ አማካይነት ማሳየት ነው።

በጥቅሉ ሁሉም ልቦለዶች በሶስት ጉዳዮች ተመሳስሎ አላቸው። አንደኛ፣ የሳይንስ ልቦለዶች ዘመናዊ ትምህርት ለሳይንስ፣ ስልጣኔ መሰረት ነው። ትምህርት የሚገኘው ደግሞ ከምዕራባውያን ነው የሚል አንድምታ አላቸው። በዚህም ሳይንሳዊ ምርምሩን የሚያደርጉት ምሁራን ነጻ የትምህርት ዕድል እየተሰጣቸው ወደ ውጭ አገር ሄደው ሳይንሳዊ እውቀት ነበይተው እንዲመጡ ሆነዋል። ሁለተኛ፣ የሳይንስ ልቦለድ ዘመናዊ ሚት ከሚፈጠርባቸው ዘውጎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ተነስቷል። አዲሱ ሚት የሚመሰረተው በነባሩ ላይ መሆኑም እርግጥ ነው። ለጥናት በተመረጡት በአራቱም ልቦለዶች ውስጥ ይህ ጉዳይ ተንጸባርቋል።

ሦስተኛ ሁሉም ልቦለዶች ማለት ይቻላል በመረጃ ቁጥጥር ስልት ተቃኝተው የተጻፉ ሊሆን ዘረ-መል ምህንድስና የሁሉም የሳይንስ ልቦለዶች ርዕሰ ጉዳይ ነው። ምንአልባትም ኢትዮጵያዊ ከመሆን ጋር የሚያይዛቸው የጋራ ነገር ይኖራቸው ይሆን? የሚለው የሚፈተሽ ቢሆንም የመንግስት የኢንዱስትሪ ሰነድ ግን እንዲህ ይላል፤ “የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ማጥናት እና መምረጥ የሚገባ ቢሆንም በዚህ ረገድ በቅድሚያ ሊጠቀሱ እና ከወዲሁ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ቴክኖሎጂዎች፣ የመረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂዎች (አይ-ሲ-ቲ) የባዮ ቴክኖሎጂዎች ናቸው” ይላል (ገጽ 331) ።

በመጨረሻም የእኛ አገር የሳይንስ ልቦለዶች በሙከራ ደረጃ የሚቀመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ለዚህም ቁጥር፣ ጥራትና ጊዜ የሚሉትን መለኪያዎች መነሻ አድርጓል። አንደኛ ከሌሎች ዘውጎች ጋር ሲነጻጸር ታትመው ገበያ ላይ የተገኙት የሳይንስ ልቦለዶች ቁጥራቸው እና በልቦለዶቹ ውስጥ የተነሱት ሳይንሳዊ ኀልዮት ጥቂት መሆናቸውን ነው።

ሌላው በአገራችን ረዥም ልቦለድ መጻፍ ተጀምሮበታል ተብሎ የሚታመነው አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አንድ ተብሎ ሲቆጠር በመጀመሪያ የሚገኘው የሳይንስ ልቦለድ የቢሆን ዓለም (1983 ዓ.ም.) መሆኑ ዘግይቶ መምጣቱም ተጨማሪ ምክንያት ነበር። ሦስተኛው ልቦለዶቹ የተፃፉት በሳይንሳዊ ምርምሮች ታግዘው ነው? ወይስ ቀመሩ ስለሚታወቅ ብቻ ነው? የሚለው ሲሆን በጥናቱ እንደተመለከተውም የጥናት ጉድለት ያለባቸው ስራዎች እንዳሉም ተመልክቷል። እንግዲህ የእኛ አገር የሳይንስ ልቦለዶች በጅምር ላይ ያሉ ቢሆንም በፋንታሲ ንዑስ ዘውግነት የሚሰለፉትን እንደ የስለላ፣ የወንጀል፣ አስማታዊ ... ያሉትን ልቦለዶች ሰብስቦ በማጥናት የኢትዮጵያን የሳይንስ ልቦለድ ታሪክ እንዲሁም ፀሃፊዎችን የሚሳስባቸው ሳይንሳዊ ጉዳይ ምንነት ለማወቅ ይቻላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሳይንስ ልቦለድ ታሪክ በመለየት የአገራችንን የሳይንስ ልቦለድ መልክ ለይቶ ለማውጣት ይቻል ይሆናል።

## ዋቢ ጽሑፎች


መሃመድ ዓሊ እንድሪስ። *እስልምና እና ሙስሊሞች በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ*። አዲስ አበባ፣ አልበንያ ሊሚትድ፤ 2004።

መሳይ ፅጌ። "የሳይንስ ራዕይ እና የቢሆን ዓለም ልቦለዶች ከሳይንስ ልቦለድ ባህርያት አንፃር ትንታኔ"። ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1993።

*መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ሰሚራ መሃመድ። "ጡሩሲና የሙስሊም ገዳም አመጣጥ እና በገዳሙ የሚከወኑ በዓላት ስርዓተ ክዋኔ"። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2005።

ቴዎድሮስ ገብሬ። *በይነ-ዲሲፕሊን የሥነ ጽሑፍ ንባብ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001።

አስፋው ዳምጤ። "የአማርኛ ልቦለድ ጉዞ ከ1900 እስከ 1999"፣ *መድበለ ጉባኤ፤ የምዕተ ዓመቱ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ዕድገት የንባብ ባህል ይዞታ እና የመጭው ክፍለ ዘመን ፈር*። አዲስ አበባ፣ 2000 ። 107-130።

ኤፍሬም አሰፋ። "በዳኛቸው ወርቁ *አደፍርስ* ውስጥ የሚታዩ ሣይንሳዊ አገላለጾች ሂሳዊ ምልከታ"። የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አስራ ሶስተኛው ዓመት ጉባዔ ላይ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1994 ። 63-77።

ዘሪሁን መለሰ። *ኤማንዳ፣ ሳይንሳዊ ልቦለድ*። አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኀ.የተ.የግ.ማህበር፣ 2004።

*የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ*። ማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መመሪያ፣ 1994።

ዮናስ አድማሱ እና ሌሎች /አዘጋጆች/። "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ" /ያልታተመ/። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ቀ.ኀ.ስ. ዩኒቨርሲቲ፣ 1966።

ደስታ ተክለወልድ /አሳታሚ/:: *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*:: አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948::

ደጉ ቂምቢ:: *የቢሆን ዓለም*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ::

ጳውሎስ ዘማርያም:: "የኹለት ዓለማት ጉዞ በዜና እስክንድር እና በገድለ ዞሲማስ ውስጥ"፣ ቴክስታዊ ትንተና:: የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2006::

ፍቅረድንግል በየነ:: *የሳይንስ ራዕይ*:: አዲስ አበባ፣ (?) ፣1986::

(?) :: *ራስ ምታት፤ ሳይንሳዊ ምርምር ውጤቱ እና መዘዙ *ሰው ማን ነው?* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ፣ 2003 ::

Anthony, Phillip O'hara (Ed). *Global Political Economy and the Wealth of Nations: Performance, Institutions, Problems and Policies*. London and New York: Rutledge, 2004.

Barnard, Alan and Jonathan Spencer (Eds). *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology*. London and New York: Rutledge, 2002.

Bassett, Caroline et al. "Better Made Up: The Mutual Influence of Science fiction and Innovation". University of Sussex Nesta Working Paper No. 13/07, (March 2013): 1- 35.

Baxter, Brian. *A Darwinian Worldview: Sociobiology, Environmental Ethics and the Work of Edward O. Wilson*. Scotland: the University of Dundee, 2007.

Berman, Michael (Ed). *The Everyday Fantastic: Essays on Science Fiction and Human Being*. Cambridge: Cambridge Scholars Publishing, (2008): 1- 25.

Birx, H. James (Ed.). *Encyclopedia of Time: Science, Philosophy, Theology and Culture*. New York: Sage Publications, Inc. 2009.

Brian, Stableford (Ed). *An Encyclopedia of Science Fact and Science Fiction.* London and New York: Rutledge, 2006.

Broderick, Damien. *Reading by Starlight: Postmodern Science Fiction.* London and New York: Rutledge, 1995.

Bunnin, Nicholas and Jiyuan Yuthe. *Blackwell Dictionary of Western Philosophy.* Malden: Blackwell Publishing, 2004.

Cavallaro, Dani. *Critical and Cultural Theory: Thematic Variations.* London New Brunswick and New Jersey: Athlone Press, 2007.

Chernyshova, Tatiana. *Science Fiction and Myth Creation in Our Age.* Science Fiction Studies, Vol. 31, No. 3, (2004): 345 -357.

Coupe, Laurence. *Myth.* 2nd ed. London and New York: Rutledge, 2009.

Creaven, Sean. *Marxism and Realism: A Materialistic Application of Realism in the Social Sciences.* Rutledge: London, 2000.

Culler, Jonathan. *Literary Theory: A Very short Introduction.* New York: Oxford University Press, 1997.

De Fina, Anna. *Identity in Narrative: A Study of Immigrant Discourse.* Amsterdam: John Benjamin Publishing Company, 2003.

Dupre, Louis. *The Enlightenment and the Intellectual Foundations of Modern Culture.* New Haven and London: Yale University Press, 2004.

Edgar,Iain R. *guide to Image Work: Imagination-based Research Methods.* London and New York: Rutledge, 2004.

Garry, Jane and Hasan El-Shamy (Eds ). *Archetypes and Motifs in Folklore and Literature: a Handbook.* New York: M.E. Sharpe Inc, 2005.

Godfrey, Peter Smith. *Models and Fictions in Science.* Proceedings of the 2008 Oberlin Colloquium in Philosophy. Philosophical Studies 143 Harvard University, 2009. 101-116.

Grayling, A.C. *The Ideas that made the Modern World: the People, Philosophy, and History of the Enlightenment."* Scotland: Encyclopedia of Britannica Robinson, 2008.

Hylland, Thomas Eriksen. *What is Anthropology?* London: Pluto Press, 2004.

James and Ann Goll, Michal. *Dream Language: the prophetic power of dreams, revelations, and the spirit of wisdom.* Shippensburg, Destiny Image Publishers Inc, 2006.

Jenks, Chris. *Culture.* London and New York: Rutledge, 2001.

Joe, Moran. *Interdisciplinarity.* London and New York: Rutledge, 2002.

John, Rieder. *"On Defining Science Fiction, or Not: Genre Theory, SF, and History."* Science Fiction Studies. (2010): 191-210.

Johnson, Richard *et al. The Practice of Cultural Studies.* London, Thousand Oaks and New Delhi: Sage Publications, 2004

Klarer, Mario. *An Introduction to Literary Studies.* London and New York: Rutledge, 1995.

Lovejoy, Arthur O. *Reflections on the History of Ideas.* Journal of the History of Ideas, Vol. 1, University of Pennsylvania Press, (1940): 3-23.

McGuigan, Jim. *Cultural populism.* London and New York: Rutledge, 1992.

Mckee, Alan. *Textual Analysis: a Beginner's Guide.* London: Sage Publications, 2003.

Muthukumaraswamy, M. D. and Kaushal Molly (Eds). *Folklore, Public Sphere and Civil Society.* New Delhi: Indira Gandhi National Centre, 2004.

Raman, Selden et al. *A Reader's Guide to Contemporary Literary Theory.* 5th ed. Harlow: Pearson Longman, 2005.

Rappaport, Roy. *Ritual and Religion in the Making of Humanity.* Cambridge: Cambridge University press, 1999.

Rapport, Nigel and Joanna Overing. *Social and Cultural Anthropology the Key Concepts.* London and New York: Rutledge, 2000.